አራት ዓመት ከሰባት ወራት (ከዕሁድ በስተቀር) ለሁለት ሰዓታት ያህል የሚቆይ ነበር። ይህ ፕሮግራም በጣም የሚከበርና የሚወደድ ጊዜ ነበር፣ በቤት ውስጥ ሲኖሩ ጸሎቱን የሚመራው ዶ/ር ብርሃኑ ሲሆን እርሱ በማይኖርበት ጊዜ እኔ እሆናለሁ።

ምናልባት ሁለታችንም ባንኖር በቤት ውስጥ ያለ በመንፈሳዊ ሕይወት ቀደም ያለ ሰው ይመራዋል። ስለፕሮግራሙ አካሄድ ሪፖርት ስለሚቀርብ ከአቅም በላይ ካልሆነ በስተቀር በምንም መልኩ ፕሮግራሙ አይቋረጥም። ይህ ጸሎት ለሕይወታችን ዕድገት፣ ለብርሃኑ አገልግሎት ጸጋና ምሪት፣ ለሚያጋጥሙን ተግዳሮቶች መፍትሄ ትልቅ አስተዋጽኦ ያደረገ ከመሆኑም በላይ ከሕመማችን የምንፈወስበት፣ ከኀዘናችን የምንጽናናበት በአጠቃላይ ብዙ በረከቶችን ከእግዚአብሔር የተቀበልንበት መድረክ ነው። ስለዚህም በረከት ጌታን አመሰግናለሁ።





# 9. ጨለማው ሲገፈፍ ጥሪዉ ደመቀ

## *9.1. ጨለማው ነጋ*

**እግዚአብሔር ይመራኛል፣**
**እግዚአብሔር . . .**
**እግዚአብሔር ይሸሽገኛል፣**
**እግዚአብሔር . . .**
**ከአንበሣ ግሣት - ከጠላት ጡጫ፣**
**እግዚአብሔር አለዉ መዉጫ።**

*(የብርሃነ ወንጌል ቤ.ክ መዘምራን፤ 1972)*

በ1983 ዓ.ም እግዚአብሔር ታላቁን ተራራ በጠጠር/በጠጠሮች ሲንደው የደርግ መንግሥት አከተመለት። ይፋዊዉ የስደት ምዕራፍ ተዘጋ። በየቀበሌው፣ በየሰፈሩ፣ በየዱሩና በጫካው በትናንሽ ቡድኖች ተሰባስበው ክፉዉን ዘመን ያሳለፉት ሕብረቶች ከሞላ ጎደል ወደ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያንነት አድገዉና ተስፋፍተዉ ብቅ አሉ።

በእብደት ሩጫዉ የፈረሱ፣ የተዘጉና የተወረሱ ቤተ ክርስቲያናት በፍጥነት ተከፈቱ። ቢሮክራሲዉ ወይም ልዩ ሁኔታዎች ባልፈቀዱበት ሁኔታ አዳዲሶች ህንፃዎችና አዳራሾች ተሠሩ። በቤት ውስጥ ማለት በጓዳና በሳሎን ተወስነው የነበሩት ሁሉ ወደ ትላልቅ ድንኳኖች ተለወጡ። በገጠር በተለይም በደቡብ ኢትዮጵያ በጫካና በዋሻ ውስጥ የነበሩት እልፍ ሆነው እየዘመሩ ወደ ሚያማክሏቸው ከተሞች ተመለሱ።

የጀማ ስብከተ ወንጌል ለማድረግ ስታዲዮሞች፣ ታላላቅ አደባባዮች እና ሰፋፊ ገላጣ ሜዳዎ በራቸውን ከፈቱ። በታላላቅ የመንግሥት እና የግል ሆቴሎች፣ በዩኒቨርሲቲ አዳራሾችና በማሕበረሰብ ተቋማት አዳራሾች፦ ሴሚናሮች፣ ዐውደ ጥናቶችና የተለያዩ ሥልጠናዎች ተሰጡ። የስደቱን ዘመን ዘወር ብለው በአውሮፓና አሜሪካ ያሳለፉ ታዋቂ አገልጋዮች ይህንን የእግዚአብሔርን ማዳን በዓይናቸው አይተው ለመመስከር ወደ አገራቸው ጎረፉ።

አገልጋዮች ከምሥራቅ እሲያ፣ ከአሜሪካና አውሮፓ እየተጋበዙ ጀማውን አደመቁት። በተነፃፃሪ ሁኔታ የተሻለ ድርጅታዊ መዋቅርና የሰው ኃይል የነበራቸው የወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን መካነ ኢየሱስና የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያናት ጋር «አብረን እንሥራ» የሚሉ የውጪ አገር ረድኤት ድርጅቶች ተበራከቱ።

ኮሚዩኒዝም በመፈከር ጡጦ የገነባው የተስፋ ጎተራ በድንገት ባዶ የሆነባቸው ሰዎች ወደ ወንጌላዊያን አብያተ ክርስቲናት ሽዐና ሺህ ሆነው ፈለሱ። የቀድሞ የፓርቲ አባላት፣ ካድሬዎች፣ ባለ ሥልጣናት፣ የቀይና የነጭ ሽብር ቅሬታዎች፣ ወታደሮች፣ መኮንኖች፣ ሴቱ፣ ወንዱ፣ ወጣቱና አረጋውያኑ የተስፋ ምንጭ የሆነዉን አምላክ ፍለጋ ወደ ቤተ ክርስቲያን ጎረፉ። ከእነዚህ መካከል *‹አብዮታዊ መዓዛቸው›* ሳይለቃቸዉ የተጠመቁና የቤተክርስቲያን አባል መሆን የቻሉት ጥቂት አልነበሩም።

እዚህም - እዚያም ዝማሬና ስብከተ ወንጌል፣ ኮንፈረንስ፣ የ‹መንፈስ ቅዱስ ሙላት› ፕሮግራም፣ የፈውስ ፕሮግራም፣





እንዲሁም ከዚያ በፊት ተሰምተው የማያውቁ መንፈሣዊ ዝግጅቶችና ልምምዶች ያለ ገደብ፣ ያለ ከልካይ መካሄድ ጀመሩ። ምዕመኑም «እንዲያና እንዲህ ያለ ነገር በዚህ ቤተ ክርስቲያን ተፈፀመ» ሲባል ሲሰማ የሰማውን ለማየትና ለመለማመድ ሲል መግተልተልን የዘወትር ሥራው አደረገው።

የመከራው ዶፍ ድንገት ወርዶባት የነበረችቱ ቤተ ክርስቲያን ንጋቱም የደረሰባት ድንገቱን እንደ ነበር ሁሉ ይህ የአደባባይ አገልግሎቷ ጥድፊያና ወከባ የተሞላበት ሆነባት። ሁሉም ነገር *ከራሱ «ከፍጥነት ሂደት»* በላይ ፈጠነ። ሌላ አብዮት መሰለ፤ «መንፈሣዊ አብዮት!!» ይህም የቤተ ክርስቲያናትን የአገልግሎት ዳር ድምበር በጣም አምበረቀቀው። ይኼ ነገር ዉሎ አድሮ የቤተ ክርስቲያንን አየር የሚበክል «*የነፃነት ግርሻ*» ወረርሽኝ ያስነሳ ይሆንን? በማለት ስጋትና ጥርጥር ያደረባቸዉ ግን እጅግ ጥቂት አስተዋዮች ብቻ ነበሩ።

## 9.2. ጥሪዉ ደመቀ

በነፃነቱ ማግሥት የቀድሞዉ ፀረ - ሃይማኖት ርዕዮተ ዓለም የፈለፈላቸው ፖሊሲዎች፣ መመሪያዎችና ደምቦች ከሰሙ። ማንም ሰው የፈለገውን ሃይማኖት የመከተልና ሥርዓተ አምልኮውንም የመፈጸም መብት እንዳለዉ በይፋ ተነገረ። ከላይ እንደ ተብራራው ቤተ ክርስቲያን ወደ አደባባይ ተገለጠች። ይህም ዶ/ር ብርሃኑ *ያ በስምያን ምሣሌነት* የተገለጠላቸው የመፅናናትና የመጎብኘት ዘመን የመምጣቱ ምልክት ይሆንን? እንዲሉ አበቃቸዉ።

ሃሳቡን በልባቸዉ እያብላሉት ሳለ በሐምሌ ወር 1983 ዶ/ር ብርሃኑ ሃብቴ በቤተ ክርስቲያን ህቡዕ ዓመታት በነበራቸው ሰፊ አገልግሎትና ዕውቅና ·ምክንያት በአንድ ዓለም አቀፍ የወንጌል ሥርጭት ጉባዔ እንዲሳተፉ ተጋብዘው ወደ እንግሊዝ አገር ተጓዙ። ጉባዔውን ለመካፈል ሲሄዱ አዲሱ መንግሥት ገና የዘጠና ቀናት ዕድሜ አላስቆጠረም።

በጉባዔው መካፈላቸዉ በኢትዮጵያ ሊመጣ ስላለዉ የእግዚአብሔር መጎብኘትና የወንጌል ተሐድሶ ራዕይ በተለዬ ሁኔታ እንዲሰንቁ አነቃቃቸው። ከመነቃቃት ባለፈም ስለ ወንጌል አገልግሎታቸዉ በተናገሩ ቁጥር. አዘዉትረዉ የሚጠቅሱትን መገለጥ የተቀበሉበት ልዩ አጋጣሚ ሆነላቸው። ያም አጋጣሚ ለሃያ ዓመታት ያህል በልባቸው ተሸክመው ሲያብላሉት የከረሙትን የወንጌል ጥሪ እግአዚብሔር እንደገና የቀሰቀሰበትና አብራርቶ ሲገልፅላቸው የራሱን ቀጠሮ የያዘበት ሰሞን መሆኑ ነበር። ሁኔታው የሚከተለውን ይመስላል።

ጉባዔው የተካሄደው ብራይተን በምትባል የባህር ዳርቻ ከተማ ነበር። ጉባዔውን የተሳተፉት በሙሉ የመንፈስ መታደስና በጸሎት ሆነው ነበር። በዚያ ታላቅ ጉባዔ ላይ በተነሡት አጀንዳዎችና የተለያዩ ንግግሮች፣ የጥናት ወረቀቶችና የልምድ ልውውጦች በጣም ተመስጠው ነበር። ከሚያዩት፣ ከሚሰሙትና ከሚያነቡት ቁም ነገሮች አንድም ቃል እንዳታልፋቸው ማስታወሻቸዉ ላይ በጥንቃቄ ይመዘግቡ ነበር። በዚህ ሁኔታ የተከታተሉት ጉባዔ ሊጠናቀቅ ሰሞን





ራሳቸውን በፍጹም የመንፈስ ቅዱስ መመሰጥ ውስጥ አገኙት።

መንፈስም አላቸው *‹‹ወደ ባህሩ ዳርቻ ውጣ!››።* ታዘዙና በእርጋታ እርምጃ ወደ ከተማይቱ የባህር ዳርቻ ወጡ። እንግሊዝ አገር ለዶ/ር ብርሃኑ አዲስ አይደለችም። የኩላሊት ሕክምና የስፔሺላይዜሽን ትምህርታቸውን በስኮትላንድ በተከታተሉበት ወቅት በደንብ ያውቋታል።

በመሠረቱ የታላቋ ብሪታኒያ መላ ግዛቶች በውኃ የተከበቡ ናቸዉ። ዳርቻዎቹም ሁሉ እንደ ኤደን ምሣሌ የለሙ - የለመለሙ መሆናቸዉን ያውቃሉ። ከባህሩ ዳርቻ ወዲያ እስከ አድማሱ ወሰን ድረስ የተንጣለለው የውኃ አካልም ከዘፍጥረት አንስቶ የነበረ መሆኑንም ያዉቃሉ። ስለሆነም የባህር ዳርቻ ፓርኮች ለእሳቸው ብርቅ ነገር ባልሆነባቸዉ ነበር። በዚያች የጌታ ቀን ግን የተንጣለለዉ ባህርና ተፈጥሮአዊዉ ትዕይንት ለእይታቸው ልዩ ሆነባቸው። ምክንያቱም የእግዚአብሔር ድምፅ እንዲህ ሲል መጥቶላቸዋልና፡- *‹‹ውኃ ባህርን እንደሚከድን ምድር እግዚአብሔርን በማወቅ ትሞላለች››*።(ኢሳ 11፡9)

እንግዲህ የኢትዮጵያን ካርታ በራዕይ በማሳየት በ1964 ዓም ለመጀመሪያ ጊዜ የተቀበሉት ራዕይ የበለጠ ሰክኖ፣ የበለጠ ደምቆና የበለጠዉን ሰፍቶ የመጣላቸው በዚህ ልዩ አጋጣሚ ነበር። ከዚያ ወዲህም በበለጠ ትጋት፣ የጸሎት ተጋድሎ፣ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ሙሉ ጊዜአቸዉን ሰጥተዉ ለማገልገል በቁርጠኝነት መሰናዳት ጀመሩ።

ይሁን እንጂ አሁንም ጥቂት እግዚአብሔር ያብራራላቸዉ ዘንድ የሚጠብቋቸው መረዳቶች ነበሩ። ይህ መቸም አብሯቸዉ የዘለቀ ባህርይ ነው። ዶ/ር ብርሃኑ ሳይገባቸዉ እርምጃ ለመዉሰድ አይቸኩሉም፣ አይጣደፉም። ‹‹ምድር ማለት የትኛዋ ነች? የኢትዮጵያ ምድር? አፍሪካ? አውሮፓ? ኤስያ?! ... የኔስ ድርሻ ምንድነው? ከየት ነው የምጀምረው? የአገልግሎቱ ዳር ድንበርስ እስከ የት ነው?. . . የሚሉ ጥያቄዎችን ይዘዉ በጸሎት የእግአብሔርን ፊት ፈለጉ። ጥሪያቸዉን ከማወጅ ተቆጥበዉ ዘመኑንና ሁኔታዎችን መመርመርና ማጥናትን መረጡ።

ይሁን እንጂ በቤተ ክርስቲያናቸውና በወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ የተከፈቱላቸውን በሮች በጥንቃቄና በአግባቡ ለመጠቀም ወደ ኋላ አላሉም ነበር። ለምሣሌ፡- በዓለምና በአገር አቀፍ ደረጃ በሚካሄዱ የወንጌል ሥርጭት ፕሮጀክቶች ውስጥ በአባልነትና በኃላፊነት እየተሳተፉ፣ የአገልግሎት ባልደረቦቻቸውን የሚያስገርሙ ቁልፍ የወንጌል ስርጭት ስልቶችን የነደፉት የእግዚአብሔርን ግልፅ ምሪት በሚጠባበቁት በእነዚህ ወራት ነበር። በተለይም፡-

- በወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ሕብረት የወንጌል ስርጭት ኮሚቴ ሰብሳቢነት (1984) ዓ.ም፤
- በ1986 ዓም በዲላ ከተማ በተካሄደው ‹ወንጌል ለሁሉም ሁሉም ለወንጌል› አገር አቀፍ የመሪዎች ጉባዔ፤





- በ1987 ዓ.ም በኮሪያ በተካሄደው ዓለም አቀፍ የወንጌል ምክክር ውስጥና በሌሎችም መድረኮች ኹነኛ አስተዋፅዖ

እንዲያበረክቱ ከእግዚአብሔር ዘንድ የተከፈቱላቸውን እነዚህን በሮች ሁልጊዜም የሚያስታውሷቸው በምስጋና ተሞልተው ነዉ።

እግዚአብሔር ስለ ሰጣቸው የአገልግሎት በሮችና መከናወኖች ሲያመሰግኑ ደግሞ የደረሱበትን የስኬት ጫፍ ብቻ እየተመለከቱ አልነበረም። ወደ ኋላም - ወደ ፊትም፤ የአሉበትንም - የተነሡበትንም ለራሳቸው እያስተነተኑ እንጂ።

አባባሉን በአንድ ምሣሌ ማስረዳት የተገባ ነው። ከብራይተን የባህር ዳርቻው መገለጥ እንደ ተመለሱ በወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ጠቋሚነት ‹‹የAD 2000 and Beyond Movement›› የብሔራዊው ቅንጅት አስተባሪ ሆነው ተመርጠው ነበር። መቼም እንዲህ ያለ ሞገስን ለመጎናጸፍ የማይመኝ የለም። ለሥጋም ለመንፈስም መረማመጃ የሚሆኑ ነገሮችም አይጠፉበትም። የብራይተኑን ዓይነት መገለጥ የጨበጠ ደግሞ በሰውም በህሊናውም ፊት ‹‹ሊቼንሳ›› እንደ ተቆረጠለት ራሱን - ሌሎችንም ማሳመን አያቅተውም።

ዶ/ር ብርሃኑ ግን ቆም ብለው አሰቡ። ‹‹እግዚአብሔር ሆይ የተሰጠኝ ኃላፊነት ገና ልትገልጠው ላልከው የወንጌል ጥሪ ልታዘጋጀኝ ያልክበት መንገድ ይመስለኛል›› አሉ። ከዚያም በጽሞና መንፈስ ወደ ኋላ ሄደው ያለፉባቸውን እርከኖች አስታወሱ። ጥር 11 ቀን 1984 ዓ.ም በጸሎት መንፈስ ሆነዉ

በግል ማስታወሻቸው ላይ የሚከተሉትን ነጥቦች ጽፉና ለእግዚአብሔር አምላካቸው አስነበቡ፡፡

*‹‹ኃላፊነቱ ከባድ ነው፤ ልቤ ግን በጣም ተነሳስቷል፡፡ ዘመኔንና ሕይወቴን ወደ ኋላ ተመልሼ ሳይ እግዚአብሔር እያዘጋጀኝ እንደ ነበረ አስተዋልሁ፡፡*

- *በ1962 ዓም በአቃቂ ጸሎት ቤት በእንግድነት ተገኝቼ አንዲት ነቢይት እጅ ጭና በመጸለይ ስለ ሚጠብቀኝ አገልግሎት ግዙፍ ግዙፍ ትንቢቶች ተናገረች፡፡ እኔ ግን ‹ይኼ ትልቅ ነገር ለእኔ አይገባም› ብዬ አሳለፍሁት፡፡*

- *በ1964 ዓ.ም ‹‹ብሔራዊ ጥሪ አለብህ፤ ከበደል ራቅ›› የሚል ራዕይና መገለጥ አየሁ፡፡*

- *በ1974 ዓ.ም በመጥምቃዊት ወንጌላዊት ማሕበር (መወማ) ተመርጬ ከ1976 ጀምሮ በመወማ በኩል የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ሕብረት (ወአቤክሕ) መሳተፍ ጀመርኩ፡፡*

- *ከ1981 አንስቶ በኢትዮጵያ ሁኔታ ላይ ጾምና ጸሎት ያመጣውን ለውጥ በመገንዘብና በእርሱም በመበረታታት የአገርን ሸክም በዕለታዊ ጸሎቴ መሸከም ጀመርኩ፡፡*

- *በሐምሌ 1983 ዓ.ም በእንግሊዝ አገር የወንጌል ጉባዔ ለመካፈል ሄጄ በኢሳ11፡9 ቃል የወንጌል ሥራ ራዕይ ተቀበልኩ፡፡*

- *ይህ የብራይተኑ ጉባዔ የሕይወቴን አቅጣጫ ገርቶት ስለ ነበር ከዚያ ስመለስ ‹‹አሥራ ሁለት አእማድ ለዓለም አቀፍ የወንጌል ስርጭትና ደቀ መዝሙርነት›› በሚል ርዕስ የዴቪድ ስሊብሊን ትምህርት ተመርኩዤ ጽሑፍ አጠናቀርኹ፡፡*

- *ከዚያ ወዲህ የሕክምና ሥራዬ እንዲያው መዋተት እየመሰለኝ መጣ፡፡*





- *ይንን ታላቅ ኃላፊነት ስወስድ የስድስት ቀናት ሙሉ የጸሎት ጊዜ ወሰድሁ፡፡ ጌታ እግዚአብሔር፡-*

  - ✓ *ሞገስ ይሆንልኝ ዘንድ*
  - ✓ *አብረውኝ የሚያገለግሉትን ሰዎች ልብ ይሰጠኝ ዘንድ፤*
  - ✓ *አገልግሎቴም በአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ተቀባይነት ያገኝ ዘንድ፡፡*

እንደ ተመኙት፣ እንደ ጸለዩትም ተከናውኖላቸዉ ጊዜ ሳይቀድማቸዉ ለነፍሳቸዉ ጥሪ ተግባራዊ ምላሽ ሰጥተዉ *እንዲያዉ መዋተት* ካሉት ሕይወት ይገላገሉ ይሆንን?!

# 10. እንደገና በዕምባ ጭጋግ

**ይነጋል - ይመሻል፣**
**ይመሻል - ይነጋል፣**
**ሌሊቱ ወደ ቀን - ቀኑም ወደ ማታ፣**
**አዲስ እንቀቅልሽ**
**በአዲስ ዘዬ ይዞ - አርጌው ሲፈታ፣**
**አባክህ ጌታ ሆይ - እፎታዬን ስምጣ፡፡**

*(ደ.ዘ ቃለ ሕይወት መዘምራን፣ 1985ዓ.ም,*

## *10.1. ሁሉም በዘመን ጥላ ሥር*

በቅድመ ነፃነት በነበሩት ትንንሽ ሕብረቶች ቁጥር እና ስፋት መጠን፦ ብዙ ዓይነት መንፈሣዊ ልምምድ፣ የተለያዩ ባህርያት ያላቸው አርአያዎችን (ሮል ሞዴሎችን)፣ የተለያዩ ‹አርበኞችን›፣ ... ወዘተ ይዞ የወጣው ምዕመን ባህርይው፣ ዐመሉና በአጠቃላይ *ማሕበራዊ - ሥነ ልቡናዉ* እጅግ ዝንጉርጉር ነበር፡፡ በተለያዩ ሞግዚቶችና በተለያዩ የአስተዳደግ ዘይቤ የአደጉ የአንድ አባትና እናት ልጆች እንኳን ተመሳሳይ ባህርይ እንደ ማይኖራቸዉ ሁሉ ይህ ዝንጉርጉርነት የሚጠበቅ እንጂ የሚያስገርም አልነበረም፡፡

የሚገርመዉስ ጉዳይ ቤተ ክርስቲያን ይህን ዝንጉርጉር መነሻና የጀርባ ታሪክ (ዳራ) እንደ ርግብ ላባ ሕብረ - ቀለም ለጌጥነት ለመጠቀም አለመቻሏ ነዉ፡፡ በተቃራኒዉ በአንድ ጣሪያና ግድግዳ ሥር፣ በአንድ የአምልኮ ሥነ ሥርዓት፣ በጋራ አመራር ስር ተቻችሎ አንድ እግዚአብሔርን ለማምለክ ያለመታደሉ ጉዳይ አስደንጋጭ ክስተት ነበር፡፡ በመዘዙም፦





መደማመጥ፣ መከባበር፣ የልብ ስፋት እየጠፋ - በትንሹ በትልቁም መወጋገዝና መተቻቸት ነገሠ፡፡

በሌላ በኩል ባልጠበቀው ሰዓት የኮሚዩኒዝም ቀምበር የተሰበረለትና አደባባይ የወጣው ምዕመን በተጋነነ ተስፋ ‹‹ኩፍ ያለ›› (ያበጠ) ነበር፡፡ ስለሆነም ድንገት በተጎናፀፈው ነፃነትና *የተጋነነ ተስፋ* በዜማ ሰክሮ እንደ እምቦሳ ጥጃ መፈንጠዙን እንጂ በመለያየት ወረርሽኝ እየተወረረ መሆኑን ሊያጤነዉ አልቻለም ነበር፡፡ ከቶም ፈንጠዚያው ልኩን አለፈና ልቡን ነሣው፡፡

ሌላም የሚጠቀስ አንድ የወቅቱ እዉነት ነበር፡፡ በለውጡ ማግሥት በጅምላ ወደ ቤተክርስቲያን የፈለሰው ትውልድ በቅድመ ስደትና በስደቱ ዘመን የነበረውን ነባር የክርስቲያን ማሕበረሰብ የመንፈሳዊ ብስለት፣ የሥነ ምግባርና ሥነ ልቡናዊ *የአቋም* ... ጥንቅርን ወይም ሚዛን ክፉኛ አዛብቶት ነበር፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ፦

- ከአጠቃላዩ ሕዝበ ክርስቲያን የሚመነጨውን ሁለንተናዊ ለዛና ጣዕም ለበጎ ወይም በጎ ባልሆነ ቅኝት ቀየረው፡፡ በመሆኑም፦
- በቤተ ክርስቲያናት ዙሪያ የተለመዱ አደራረጎችና እሴቶች (Norms & Values) ረግተዉ በማይሰነብቱ ***ተለዋዋጭ አደራረጎች*** ተተኩ፡፡
- በሌላ አገላለፅ የክርስቲያኑ ማሕበረሰብ እሴቶች፣ ፋይዳዎች፣ ሥርዓቶች ምስቅልቅላቸው ወጣ፡፡

ቀድሞውኑም አነስተኛ ድርጅታዊ ተቋም፣ የአሰራር መዋቅሮች፣ የሥራ ማኑዋል፣ አንድ ወጥ ፖሊሲ እንዲሁም

መርሆና በሳል መሪዎች ያልነበራቸዉ ቤተ ክርስቲያናት ይህን አዲስ የመጣባቸዉን መለዋወጥ ከቶም በዕውቀት ሊያስተናግዱት አቃታቸዉ። ከዚህም የተነሣ ትንንሽ ጉዳዮች ዋና መነታረኪያ እየሆኑ፤ ትልልቅ አጀንዳዎች በምናምንቴዎቹ እየተዋጡ መከፋፋቱን፣ መገፋፋቱንና መለያየቱን አጋጋሙት።

ክፉዉን ዓለም ሸሽተዉ በአዲስነት ከመጡቱ አንዳንዶቹ ‹‹እንዲህ ከሆነማ ለምኔ?!›› እያሉ ወደ ገዛ ፈቃዳቸው ተመለሱ። ሌሎችም ቀደም ሲል የተነገራቸዉን የተጋነነ ተስፋ በጨለማ ውስጥ እንደ ተሰወረች ጥቁር ድመት በዳባሳ ለመፈለግ ከአንዱ ቤተ እምነት ወደ ሌላው ባዘኑ።

ከፊሎቹ ደግሞ በማይታመን ቅልጥፍና ወደ መሪ አገልጋይነት፣ ነብይነት፣ ‹‹ሐዋርያነት›› . . . ወዘተ ተረማምደዉ በአንዱ ወይም በሌላው የጥል ቡድን ውስጥ አጋፋሪ ለመሆን በቁ። የአብዛኛው የአጋፋሪነት ሚናው አወንታዊ ያለ መሆኑ እንዴት የሚያሳዝን ነበር!! ይህም በስደቱ ዘመን በትንንሽ ሕብረቶች፣ በጸጥታና በእርጋታ መንፈስ ምዕመናንን ሲያገለግሉና ሲገለገሉም የነበሩ መሪ አገልጋዮች፣ ወንጌላውያን፣ መጋቢያንንና ጭምት ምዕመናንን ግር ማሰኘት ጀመረ።

ከነባር አማኞቹ መካከል ግማሾቹ በአግባብም - ያለአግባብም የቤተ ክርስቲያንና የእግዚአብሔር *ጠበቃና ዋቢ* መሆንን መርጠው በህቡዕ ቀይታቸው የተላበሱትን መንፈሣዊ ጸጋ፣ ክብርና ሞገስ ጠርጎ በሚያስጥል ንትርክ ውስጥ ተጠምዶ መክረም ዕጣ ፈንታቸው ሆነ።





እነዚህና የመሳሰሉት ሁኔታዎች ተደማመሩባትና ቤተ ክርስቲያን ገና የምስጋናውን ሕብረ ዜማ ሳታጣጥም መንፈሣዊ በሚመስል የነውጥ ምዕራፍ ውስጥ ዘቀጠች። አንድ *በሰላምና ግጭትን በማስወገድ* ዙሪያ የተሰማሩ ባለሙያ የዚያን ዘመን ትዝብታቸዉን የገለጹት በሚቆጠቁጡ ቃላት ነበር፤ እንዲህ ሲሉ፦

> *‹‹የቤተ ክርስቲያንን የውስጥ ያለ መግባባት በኢትዮጵያችን ውስጥ እጅግ አስቸጋሪ የሚያደርገው አንዱ ነጥብ ሂደቱን የሚዘውሩት ሰዎች ወይም ቡድኖች አጀንዳዉንም ሆነ አድራጎታቸዉን በጌታ ስም ስለ ሚጀቡኑት ነው። በአለመግባባት ዉስጥ የተጠመዱ ወገኖች ‹ጌታ ተናግሮኛ ነዉ! . . . መንፈስ ቅዱስ ገልያልኝ ነዉ! መገለጥን ተቀብዬ ነዉ! የሚል ምክንያት ያቀርቡ ነበር። ለመሆኑ እንዲህ ያለ ምክንያት ከአንደበታቸዉ ከወጣ ወዲያ የመጽሐፍ ቅዱስ ወይም የሕግና የመተዳደሪያ ደንብ በመጥቀስ ማስማማት ይቻላልን?››*

ከዚያማ ወዲያ አሁን ዘወር ብለው በስክነ አዕምሮ ሲታዘቡት በሚያሳፍራቸው መንፈሣዊ የአመራር ማጥ ውስጥ ወደቁ። የውስጡ ነውጥ የፈለፈላቸው አንዳንድ ቡድኖች *የፍጥረትን ሩጫ በሚያጠፉ መሣሪያ* (አንደበት) ክፉኛ ተጨራረሱ። ይህም የቅዱሳንን ልብና ስሜት በሚያሸማቅቅ ሁኔታ ለዓለሙ ሁሉ ትዝብት ድንገቱን ተገለጠ።

እንግዲህ የእነ ዶ/ር ብርሃኑ ሀብቴ ትውልድ አባል የነበሩት የመሪ አገልጋዮች አብዛኛዎቹ ይህን በሚመስል የቤተ ክርስቲያን መከራና ምስቅልቅል፤ እንደገናም ደስታ፣ ምስጋና፣ ዉሎ ሲያድርም በእርቅና በሰላም እንደገናም ግርሻና መፋረስ ውስጥ ነበር ያለፈው። የዶ/ር ብርሃኑን ዩአገልሎት ጥሪ እና

ውጣ ውረዱን ታሪክም ስናወራ ይህን መሰሉ እዉነታ ከጀርባው የማያጠላበት ምንም ፈለግ የለም፣ ሊኖርም አይችልም። ይሁን እንጂ ደስ የማያሰኙት ቀኖች - ትዝታዎች በልባችን ውስጥ ከመጠን በላይ ፋፍተው ደጋግ ትውስታዎቻችንን እንዳይውጡብን ልንጠነቀቅ ይገባናል። ምክንያቴም እያንዳንዱ ዘመንና ትውልዱ የየራሱ ክፉና ደግ አሻራዎች አሉትና!

## 10.2. የማይረሱ ቀናት

1973 ዓ.ም መጨረሻ ድረስ የብርሃነ ወንጌል ቤተ ክርስቲያን ምዕመናን ቤተ ክርስቲያናቸው እንደ ተዘጋች ትቀራለች ብለው አልገመቱም ነበር። ካድሬዎቹ ግን ጨከኑ።



ዶ/ር ብርሃኑ ከነብርሃን ወንጌል ቤ/ክ ሽማግሌዎች

ከዛሬ ነገ ይፈቱ ይሆናል ተብለዉ ሲጠበቋቸዉ የነበሩት አገልጋዮቻቸዉም እስር ቤት ሰነበቱ። በብዙዎችም ዘንድ የተስፋ መቁረጥ ምልክቶችም ታዩ። እግዚአብሔር ልባቸውን





ያበረታላቸው ግን ተነሳሱና ‹ሩሃማ› የሚባል ኮሚቴ መሥርተው ምዕመናን በቤት ውስጥ ሰብስበው የአምልኮ ቡድኖች ማደራጀት ቀጠሉ።

(የሩሃማ ቡድን ቤተ ክርስቲያን ከመዘጋቱ በፊት የነበረው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ኮሚቴ ቅጥያ መሆኑን ያስታውሱ) የሩሃማ አባላት አብዛኛዎቹ ወጣት አገልጋዮች ነበሩ። ለእስራትና ለሞት እንዳይጋለጡ ሲባል ከሽማግሌዎች በስተቀር ማንም እንዳያውቃቸው ተደረገ። ነገር ግን በየዋህ ክርስቲያኖች በቅንነት በተሠራ ስህተት ምስጢሩ አመለጠ። ኮሚቴውም እንዲበተንና ሌላ ስልት እንዲቀየስ ተደረገ።

በዚህ ጊዜ ዶ/ር ብርሃኑ ከስኮትላንድ መጥተው ስለ ነበር በመሪ አገልጋዮቹ የስልት ቅየሳ ምክክር ተሳታፊ ሆኑ። ወዲያውም ሁለት የሕቡዕ አገልግሎት አስተባባሪ ኮሚቴዎች ተቋቋሙ። አንደኛው እሳቸው የሚመሩት ‹የቤት ለቤት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት አስተባባሪ ኮሚቴ› ሲሆን ሌላው አቶ ሰይፉ ሲዳ የሚመሩት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት አዘጋጅ ኮሚቴ ነበር። እንደ ፊተኞቹም ሁሉ የእነዚህም የኮሚቴ አባላት ስም ለማንም እንዳይገለጥ ተደረገ።

ኮሚቴዎቹ በራሱ ጊዜና ሂደት ለታሪክ የሚበቃ ሥራ አከናወኑ። የቤተ ክርስቲያን አምልኮ ጣቢያዎች በየዞኑ ተደለደሉ። በጠቅላላው አንድ ማሕበረ ምዕመን አቅፋ የነበረችቱ አጥቢያ ስልሳ ያህል በሚደርሱ ትንንሽ የቤት ውስጥ ሕብረቶች ተደለደለች። አገልጋዮች ተሰየሙ። ከሥርግ፣ ከአደባባይ ዝማሬና ከመሳሰሉት የአዳራሽ ሥነ



ዶ/ር ብርሃኑ ከኑብርሃን ወንጌል ቤ/ክ ሽማግሌዎች

ነርዓቶች በስተቀር ይህ ቀረሽ የማይባል አግልግሎት ረረሳቸው:: ታላቅ መጽናናትም ሆነ:: በስደቱ ሳቢያ ኀሰቆለዉ የምዕመናን ልብ፣ የስሜት ቁስልና የመንፈስ ሃዘን ኮጠገነ፣ ስብራታቸው አገገመ::

ዮስ በቀስም መሪዎቿ የቤተ ክርስቲያን ዘለቄታዊ አሰራሮችን ወደ ማስረፅ ተሸጋገሩ:: አንዱም የቤተ ክርስቲያኗን መተዳደሪያ ደምብ እንደገና ከልሶ ማርቀቅና በጠቅላላ ጉባዔ ማፅደቅ ነበር:: ጠቅላላ ጉባዔ የሚካሄደው በወቅቱ የልተዘጉትን ቤተ ክርስቲያናት ትብብር በመጠየቅ ነበር::

ነገር ግን ከወቅቱ ክፉት የተነሣ ለእንዲህ አይነት ስብሰባ ነራቸውን ለመክፈት የሚፈቅዱ ቤተ ክርስቲያናት ማግኘት ዮሳል አልነበረም:: ስለሆነም የቤተ ክርስቲያናቱ መሪ ነገልጋዮች በተሳተፉበት ጉባዔ ብቻ የመተዳደሪያ ደምቡ ነደቀ:: የመተዳደሪያ ደንቡ በቅርፅና በአገልግሎት አወቃቀር ነገድ ትልቅ ለውጥ ተደርጎበት ነበር:: አንደኛው መሠረታዊ ነውጥ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አመራር ‹‹ከዲያቆናት ነሚቴ ወደ ሽማግሌዎች ኮሚቴ›› መዛወሩ ነበር ይላሉ አቶ ነይፉ ሲዳ በአሁኑ ወቅት የዲኖሚኔሽኑ የአስተዳደርና ኑይናንስ ኃላፊ::

ዚህንን ደንብ መሠረት በማድረግ በ1975 ዓ.ም በህዳር ወር ኤስ.አይ.ኤም. ዋና ጽህፈት ቤት በተደረገው የጠቅላላ ጉባዔ ’ቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ተመረጡ:: በዚህ ወቅት ነበር ዶ/ር ብርሃኑ ሀብቴ በሽማግሌነት የተመረጡትና በኋላም ’ሽማግሌዎች ጉባዔ ሰብሳቢ የሆኑት::





በመተዳደሪያ ደንቡ መሠረት የሽማግሌዎች ምርጫ በየሁለት ዓመቱ መደረግ ነበረበት:: ለዚሁም ተብሎ በ1977 ዓ/ም ምዕመናን በሉተራውያን ቤተ ክርስቲያን ለጉባዔ ተጋበዙ:: የወቅቱ ሁኔታ ግን በስጋት የተሞላ ስለ ነበር ተግባራዊ ማድረግ አልቻሉም:: ምክንያቱም ማን - ምን እንደሆነ በጥልቀት ለማወቅ ያዳገተበት ወቅት ስለ ነበር ምዕመናን የቤተ ክርስቲያናቸውን አመራር በፍፁም ልባቸዉ እምነት ለማይጥሉበት ወይም ላልተፈተነ ሌላ ሰው አሳልፎ መስጠትን ስላልደፈሩ ነበር::

ስለሆነም ተሰብስበዉ መከሩበትና በሥራ ላይ ያለው የሽማግሌዎች ኮሚቴ እንዲቀጥል ወሰኑ:: ዶ/ር ብርሃኑ ቤተ ክርስቲያኗን ለአሥራ ሁለት ዓመታት የመሩበት መነሻ ከእነዚህ አጠቃላይ ተጨባጭ ሁኔታዎች የመነጨ ነበር:: መከራዉ በአባራ ማግሥት ግን በአለመግባባት ወይም በቅራኔ ቀንበር ሥር የመቆየት መራራ ፅዋን የቀመሱት እነዚያዉ የቤተ ክርስቲያን የቁርጥ ቀን ልጆች ሆኑ:: ቅራኔዉስ? እነዚያን በአንድ ልብና በአንድ መንፈስ ሆነዉ ያሳለፏቸዉን መልካም ቀናት ጭጋግ አልብሶባቸዉ ይሆንን? አጠቃላዩን ገፅታ ከዚህ መጽሐፍ ዝግጅት ዓላማ አንፃር ብቻ በሚቀጥሉት ገጾች ደረጃ በደረጃ እንዳስሰዋለን:: ሊረሱ የማይገባቸዉ ቀናት ተረስተዉ ወይም አልተረሱ እንደሆነ የሚመዝነዉ ግን የአንባቢዉ ህሊና ይሆናል::

## 10.3 ደረቅ ሌሊቶች

*‹‹እግዚአብሔር ሆይ! አንተ አምላኬ ነህ፤ አንተን ከልብ እሻለሁ፤ ውኃ በሌለበት፣ በደረቅና በተራቆተ ምድር፣ ነፍሴ አንተን ተጠማች፤ ሥጋዬም አንተን ናፈቀች፡፡›› (መዝ 63:1)*

እዉነትና ፅድቅ ይገለጥባት ዘንድ በተመረጠችዉ የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ዉስጥ ለዚያዉም በቅዱሳን መካከል የሚነሱ ቅራኔዎች ለጊዜዉም ቢሆን የክርሰቶስ ጸጋ ካልሸፈናቸዉ በስተቀር ራቁታቸውን ሲያፈጡ ቀኑን ያጨልማሉ፤ ሌቱንም ያደርቃሉ፡፡ ቅራኔዎቹ አልፈዉ ‹‹ተረት›› ከሆኑ በኋላ እንኳን በቅራኔ ዉስጥ ተጠምደዉ ደረቅ ሌሊቶችን ላሳለፉት ወገኖች ቀርቶ ለታሪክ ታዛቢ ትዉስታም ይከብዳሉ፡፡ ሆኖም ለትምህርታችን ይሆኑን ዘንድ ከፍርድ በፀዳ ህሊና በጥቂቱ መመርመሩ ክፋት የለዉም፡፡

ቤተ ክርስቲያን በነፃነት ማግሥት ድንገቱን በፍርርቅ የተከሰቱባትን ድሎችና ሽንፈቶች፣ በረከቶችና መርገምት - ዓይነት እዉነቶችን፣ በአጠቃላይ ‹የመሆንና ያለመሆን› ክስተቶችን ከቶም በሌላት አቅም ለማስተናገድ እጅጉን ባተለች፡፡ በቅድሚያ ማለትም በ1984 ዓ.ም የኹከቱና የቀውሱ ዕጣ ፈንታ ከዳሰሳቸዉ የወንጌላውያን ቤተ ክርስቲያናት መካከል አንዷ የብርሃነ ወንጌል ቤተ ክርስቲያን ሆነች፡፡

ይህ ጸሐፊ ከአጠቃላይ እውነታዎች በስተቀር የቤተ ክርስቲያንን የውስጥ ችግሮች በዝርዝር ለመተንተንና የትኛውንም ወገን ለውጭኛው ዓለም ፍርድ አሳልፎ የሚሰጥ አተራረክ ለመጠቀም ህሊናው አይፈቅድለትም፡፡ ነገር ግን





አንድ ታሪክ የሚፈጸመዉ በተወሰነ ጊዜ፣ ቦታ፣ ሁኔታዎችና አጠቃላይ ዐዉድ ዉስጥ በመሆኑ ብቻ ከዶ/ር ብርሃኑ የሕይወት ጉዞ ጋ በጥብቅ የተገናኙትን ክስተቶች በጥንቃቄ መርጦ ከመጥቀስ ግን ማምለጥ ያለመቻሉን እንደገና ማስታወስ ይወዳል፡፡

ጥቂት ዓመታት ወደ ኋላ እንመለስ፡፡ ከነሐሴ 1 እስከ 3 ቀን 1984 ዓ.ም የብርሃነ ወንጌል ቤተ ክርስቲያን በወቅቱ ዓመታዊ የግምገማና የዕቅድ ስብሰባ ተካሂዶ ነበር፡፡ በወቅቱ የነበሩ ሰዎች እንደሚመሰክሩት የቤተ ክርስቲያንን አሠራርና አመራርን የተመለከቱ ጉልህ ጥያቄዎች በግልፅ አልተነሱም ነበር፡፡ ነገር ግን በሽማግሌዎችና በመጋቢያን መካከል ያለ መግባባት ዘር መብቀል ጀምሮ እንደ ነበረም እኒሁ ታዛቢዎች ጨምረዉ ይናገራሉ፡፡ ይህም ቢሆን አዳዲስ አጥቢያዎችን በብዛት ስለ መክፈት ወይም ስለ አለመክፈት፣ በተለያዩ መስክ የተሰማሩ አገልጋዮችን በተለያየ የአገልግሎት ስያሜ መሰየም ይገባቸዋል የሚሉና ስያሜዉ ይዘግይ… ወዘተ የሚሉ ዓይነት ቀላል ልዩነቶች እንጂ መሠረታዊ የሚሰኝ ያለመግባባት አልነበረም፡፡

ነገር ግን ‹‹እንደገና በዕንባ ጭጋግ›› በሚለው ርዕስ ሥር በዝርዝር እንደ ተገለጸው በወቅቱ በሰፈነው ማሕበራዊ ሥነ ልቡና፣ በጅምላ የማሰብ ዝንባሌና በሁለቱም ወገኖች ዘንድ የአዳዲስ ‹አርበኞች› መከሰትና መጉላት፣ የነባር/የዋነኞች እርምጃ ጊዜዉ ከሚጠይቀዉ ፍጥነት ጋር ያለማዋሃድ እንዲሁም ተረድተዉትም ሆነ ሳይረዱት ቅራኔንና ተቃራኒዎችን አጅበዉ በጭብጨባ የሚያጋግሉ ሰዎች

መበራከትና በመሳሰሉት ምክንያቶች ሁኔታዎች ያለቅጥ ተካለቡ።

ከበርካታ የቅራኔዎች አፈታት ፅንሰ ሃሳቦች መረዳት እንደሚቻለው ደግሞ *በግልብ መነሻ ላይ በበቀሉ መከፋፋቶች የተጠመዱ የንትርክ ተዋንያን (በቀኝ ወገን ቢሰለፉ - በግራው) ጣቶቻቸውን አነጣጥረዉ የሚቀስሩት ወደ ግለሰቦች እንጂ በግለሰቦቹ አመለካከት ወይም ባመነጩት ሃሳብ ላይ አይሆንም።* ለምን? የሚወራበት ጉዳይ ተተንትኖ ቢጨመቅ ጭብጥ የሚሞላ ፋይዳ ስለማይወጣው›› ይላሉ፤ አዋቂዎቹ።

ወደ ብርሃነ ወንጌል እንመለስ። አሁንም ቢሆን አንባቢ ልብ ይበል። ስር በሰደደና መሠረታዊነት ባለዉ የሥነ መለኮት፣ የአስተምህሮ፤ የፍልስፍና ወይም የአደራረግ ዘይቤ ልዩነት ላይ የተመረኮዘ ቅራኔ በመካከላቸዉ ነበር ብሎ በድፍረት መናገር አይቻልም።

ከዓመታዊ የግምገማና የዕቅድ ስብሰባ ተደርጎ ብዙም ሳይቆይ መጋቢያኑ ከሽማግሌዎች ጋር ይፋዊ ዉይይት ሳያደርጉ ወይም ሳያማክሩ ቤት ተከራይተው የአምልኮ ፕሮግራም ጀመሩ። በመደበኛ ጉባኤዎች እንደ ሚደረገዉም መባ መሰብሰብ ቀጠሉ። በዚህ ወቅት ነበር በሽማግሌዎችና በመጋቢያን መካከል የነበረዉ መሸካከር ተባብሶ ለቤተ ክርስቲያኒቱ መከፋፈል ምክንያት የሆኑት የመገፋፋት ምልክቶች በግልፅ መታየትና ሁለቱንም ወገኖች የሰላም እንቅልፍ የነሱ ደረቅ ሌሊቶች መቆጠር የጀመሩት።





ሁለቱ ወገኖች በጉዳዩ ላይ ለመነጋገር ለመጀመሪያ ጊዜ በይፋ የተሰበሰቡት መስከረም 21 ቀን 1985 ዓ.ም ነበር። በስብሰባዉ ላይ መጋቢያኑ ያላቸው ዋና ቅሬታ በዶ/ር ብርሃኑ አመራር ላይ እንደ ሆነና እንቅስቃሴቸዉ ላይም ተፅዕኖ እንደሚያደርጉባቸዉ ገለፁ። ስብሰባዉን አስመልክቶ ዶ/ር ብርሃኑ የያዙት ማስታወሻ ደግሞ እንዲህ ይነበባል፦

> *‹‹ተቃውሟቸዉ ቢወርድብኝም ሁኔታዉ ቅንጣት ታክል አልረበሸኝም። . . . በግለት መናገራቸዉን ቀጠሉ። በዚህ ሁኔታ ብዙ ሰዓት ቆይተን እልባት ላይ ሳንደርስ ተለያየን። ከመለያየታችን በፊት ግን መጋቢያን በተናጠል ስብሰባ መጀመራቸው አግባብ አለመሆኑን አመኑ። ሆኖም የተጀመሩት ስብሰባዎች እንዳይቋረጡ ከፍተኛ ውትወታ አደረጉ። (ዐዉደ ዕለት)*

ጥያቄአቸዉ ግን ለወዲያው ተግባራዊ ምላሽ አላገኘም፤ ይልቁንም ሽማግሌዎች በመስከረም 23 ቀን 1985 ዓ.ም ተሰብስበው በመጋቢያን የተጀመሩት ስብሰባዎች እንዲቋረጡ በመወሰን ዉሳኔዉንም ለአባላት ለማስታወቅ በጉባዔ የሚነበብ ጽሑፍ አዘጋጅተዉ በተኑ።

በጥቅምት 10 ቀን 1985 ዓ.ም ከመጋቢያን ጋር ሁለተኛ ስብሰባ ተደረገ። መጋቢያኑ *‹‹ቤተክርስቲያንን በአንድ ቦታ ማሰባሰብ ትክክል ያለ መሆኑን›› በማመልከት፣ ሃሳባቸዉም የጌታን ሥራ ለማስፋፋት ይጠቅም ዘንድ ‹‹አጥቢያዎችን በየቦታው ማቋቋም እንደሆነ››* ገለጹ።

ሽማግሌዎች ደግሞ ከ1983 ዓ.ም ጀመሮ እዉን የሆነውን የቤተክርስቲያን ወደ አደባባይ የመገለጥ ጉዳይና በወቅቱ ተመካክረዉ የደረሱበትን ውሳኔ መሠረት በማድረግ ‹‹*ለጊዜዉ*

*በአንድ ማዕከል መሰባሰብ መቅደም እንዳለበት፣ ከዚያም ብስለትና ልምድ ሲገኝ ቅርንጫፎችን ማቋቋም እንደሚቻልና ለወደፊት እንደሚታሰብበት››* አስገነዘቡ። *መደማመጥና መስማማት ግን አልተቻለም*።

በጥቅምት 15ቀን 1985 ዓ.ም ሽማግሌዎች ተብስበው የተነሣውን ሁከት ለማቆም ውሳኔ ለማስተላለፍ ጊዜዉ አሁን ነዉ ሲሉ አመኑበት። ቀጥሎም፦

- ቤተክርስቲያን በአንድነት እንድትሰባሰብ፣
- ዶ/ር ብርሃኑ በመሪነት እንዲቀጥሉ፣
- ‹‹መጋቢ›› በሚለው መጠሪያ ላይ በእግዚአብሔር ቃል የተመሠረተ ውይይት ተደርጎበት ተግባራዊ እንደሚሆን የሚገልጽ ውሳኔዎች አስተላለፉ።

ዉሳኔዉም ጥቅምት 21 ቀን 1985 ዓ.ም በጉባዔ ተነበበ። ውሳኔው ሁኔታውን አላረገበውም፤ ጉዳዩ እየተካረረ ሄዶ ጥር 9 ቀን 1985 ዓም የሽማግሌዎቹና የመጋቢያኑ መለያየት ይፋ ይሆናል ብለው የገመቱ ግን ጥቂቶች ብቻ ነበሩ። ከዚያም ወዲህ የመጥምቃውያን ሕብረት ቀጥሎም የኢ.ወ.አ.ሕ. እንዲሁም አንዳንድ ዕውቅና ያላቸው ግለሰቦችም ጉዳዩን ለማርገብ ጣልቃ ገቡ። ችግሩ መፍትሔ ሳያገኝ 1985 ዓ.ም አለቀ። በአንድ ዓመት ቆይታ የችግሩ ቅርፅና ይዘት ምን ያህል እንደ ተለዋወጠ ባለ ጉዳዮቹ አይስቱትም።

በ1986 ዓ.ም በእንቁጣጣሽ ማግሥት ለምዕመኑ አልፎም ለመላው የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት የተረፈ ዋዘኛ ዜና ተሰማ። ያም የመጥመቃውያን ወንጌላዊት ማሕበር





ቦርድ ስብሰባ አድርጎ ‹‹ብርሃነ ወንጌል ቤተ ክርስቲያን ስለ ፈረሰች እንደገና ለማቋቋም መነሣቱንና ለዚሁም አደራጅ ኮሚቴ መሰየሙን፣ ሽማግሌዎቿ መሻራቸውን፣ ዶ/ር ብርሃኑ ከቤተ ክርስቲያን አባልነት መሰረዛቸውንና ሌሎች ተገዳዳሪ ይሆናሉ ተብሎ የተገመቱ ነባር አባላት ከአገልግሎት መታገዳቸዉን የሚገልፅ ባለ ስምንት ገጽ ደብዳቤ መበተኑ ነበር።

ደብዳቤዉ እሁድ መስከረም 2 ቀን 1986 ዓ.ም ለአምልኮ ለተሰበሰበዉ ማሕበረ ምእመን ተነበበ። ይህ ደብዳቤ ስለ ቀድሞም ቢሆን የችግሩ መነሻ ምን እንደሆነ በጥልቀት ለመረዳት ሁኔታዎቹ ያልፈቀዱለትን የእግዚአብሔርን መንጋ ልብ አናወጠዉ። በሌላ በኩል ጉዳዩን በተመለከተ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ በቁንጽሉ አለዚያም እጅግ በተጋነነ ሁኔታ የተረዳዉ ምዕመንም ራሱን በአንዱ ወይም በሌላዉ ወገን ስር ለመመደብ መንፈሱንና ስሜቱን ክፉኛ አንገላታ። በጊዜዉ የብዙዎችን አባላት አእምሮ የያዙት ጥያቄዎች፦

- *ብርሃነ ወንጌል ቤተ ክርስቲያን ሆኖ መቀጠል የሚችለው ወገን ማኅበሩ እውቅና የሰጠው ወገን ብቻ ይሆንን?*
- *ለመሆኑ ማኅበሩ ይህን ማድረግ ሥልጣን አለዉን?*
- *ከዚህ በኋላ ወደ አንድነት መምጣት ይቻላቸዉ ይሆንን?*
- *ቢለያዩስ? እውነተኛዋ ብርሃነ ወንጌል የትኛዋ ነች? ጎተራ አካባቢ ያለችው? ወይስ ጎፋ አካባቢ ያለችው?*
- *ትክክለኞቹ እነማን ናቸዉ?*

- *እዚህ ወይም እዚያ ብሄድ እነማን ምን ይሉኝ ይሆን? የሚሉትና የመሳሰሉትነበሩ።*

በአንዳንድ ሰዎች አስተያየት፡ ከመጥመቃውያን ወንጌላዊት ማሕበር የተላከዉ ደብዳቤ የምዕመኑን ኅሊና ከመረበሹም በላይ ሁለቱም ወገኖች የበለጠውን እንዲያመሩና በተፃራሪ ጫፍ እንዲቆሙ አደረጋቸዉ።

መስከረም 6 ቀን 1986 ዓም ቤተ ክርስቲያኗ በእውን የመከፈሏ ነገር ለዓለሙ ተገለጠ። ይህም የሆነው ዶ/ር ብርሃኑን ጨምሮ በሽማግሌዎች የሚመራው ወገን መስከረም 5 ቀን አግዳሚ ወንበሮችን ከጎፋ ሰፈር ጸሎት ቤት ወደ ጎተራ ጸሎት ቤት ሲያዛውር የተነሣውን ግብግብ ተከትሎ ነበር። ግብ ግቡ የተፈጠረዉ ደግሞ የመጥምቃውያን ወንጌላዊት ማሕበር ጽህፈት ቤት ‹‹የንብረቶቹ ባለቤት እኔ ነኝ›› በማለት ወንበሮቹን ሲያጓጉዙ የነበሩ ሦስት ሰዎችን በፖሊስ በአሳሰረበት አጋጣሚ ነበር።

ወንበሮቹን ሲያጓጉዙ የነበሩት አገልጋዮች ፖሊስ ጣቢያ መታሰራቸው ሲሰማ ዶ/ር ብርሃኑን ጨምሮ ሽማግሌዎችና ሌሎች በርካታ አገልጋዮች በፖሊስ ጣቢያ ተገኙ። በዚህን ጊዜም ከመጥምቃውያን ወንጌላዊት ማኅበር በኩል ጉዳዩን የሚከታተሉት ሰዎች ወንበሮቹን እንዲያጓጉዙ ያዘዙት የሽማግሌዎቹ ሰብሳቢ ዶ/ር ብርሃኑ መሆናቸዉን በመጠቆም በተጠያቂነት መታሰር አለባቸው ሲሉ ለፖሊስ አመለከቱ። ፖሊስ አቤቱታዉን ተቀብሎ ዶ/ር ብርሃኑ እንዲታሰሩ ወሰነ። ዶ/ር ብርሃኑም ያለ ምንም ማንገራገር ራሳቸዉን ለእስር አዘጋጁ።





ነገር ግን ከሽማግሌዎቹ አንዱ የነበሩት አቶ ገብረመድህን ኪዳኔ ‹‹በዶ/ር ብርሃኑ ምትክ እኔ እንድታሰር ፍቀዱልኝ›› በማለት ለፖሊስ አመለከቱ። የጉዳዩን ክብደትና ቅለት ያገናዘቡት ፖሊስ አዛዥ የአቶ ገብረመድህንን ጥያቄ ስለ ተቀበሉት እሳቸው አራተኛ ሰዉ ሆነው ታሰሩ።

የሁለቱ ወገኖች መከፋፋት ከቅዱሳን ምክርና ተማፅኖ አልፎ የቤተ ክርስቲያንን የዉስጥ ገበና ለቀበሌ መስተዳደር፣ ለፍርድ ቤትና መገናኛ ብዙኃን አራጋቢነት ለዓለማዊዉ ዓለም መገለጥ የጀመረው ከዚህ ግርግር በኋላ ነው።

ወቅት የተባለው ጋዜጣ በታህሳስ 20 ቀን 1986 ዓ.ም እትሙ ***‹‹በቤተ ክርስቲያናት ላይ የሚካሄደው ዘረፋ አሁንም ተጧጡፏል››*** ሲል ገበናዉን ዘራዉ። አዲስ አድማስ የተባለዉ ሌላዉ ጋዜጣ ደግሞ በታህሳስ 24 ቀን እትሙ ***‹‹ቤተ ክርስቲያንን ሲዘርፉና ሲያዘርፉ የተገኙት ጥር 12 ቀን 1986 ፍርድ ቤት ይቀርባሉ››*** በማለት መላውን የክርስቲያን ማሕበረሰብ ስሜት ያሸማቀቀ ወሬ አተመ።

በጋዜጦቹ ክፉኛ ስማቸው የተብጠለጠለው የዶ/ር ብርሃኑና የካፒቴን ወጋየሁ ቅስም እንዳይሰበር የሰጉ የቅርብ ሰዎች ስልክ በመደወል፣ በአካል በመምጣትና ደብዳቤ በመጻፍ ያፅናኗቸው ነበር። ይህ ጸሐፊ ከመካከላቸው ጥቂቶቹን አግኝቶ አነጋገራቸው። እንዲህም መሰከሩለት፦

> *‹‹ይህ እግዚአብሔርን ሳገለግል ልከፍለው የተገባኝ ዋጋ ነው። ደስ እያለኝ እከፍላለሁ። አንደኛ ሆኖ ከማሸነፍ ይልቅ እውነተኛ መሆን ይሻላል አለኝ።›› (የቤተ ክርርስቲያን መሪ)*

*‹‹አንድ የፀሎት ሕብረት ፕሮግራም ላይ ለመካፈል በሄድኩበት አጋጣሚ ከእኔ ቀድመዉ የተገኙ ሰዎች ጋዜጣዉን እያነበቡ ሲቆዝሙ ደረስኩ:: ወዲያዉ ወደ ጸሎት አመራን፤ አንዳዳንዶችም ጋዜጣዉን በእግዚአብሔር ፊት ዘርግተዉ እንባ እያፈሰሱ ይጸልዩ ነበርና ወረቀቱ በእንባ ራሰ::*

*ከጸሎቱ በኋላ የተሰማዉን ስሜት እንዲገልጽልን ጠየቅነዉ:: አንገቱን ጋደል አድርጎ ጥቂት ፈገግ አለና ‹መልካም - መልካም ነዉ!› የሚል ቃል ብቻ ተናገረ:: በዚህን ጊዜም ስለ ዓይን - የዓይን ዓይነት ምላሽ ለመስጠት የተዘጋጀዉ ሰዉ ሁሉ ጸጥ አለ::›› (ሲስተር እቴነሽ ዳምጠዉ)*

የሚከተሉት ደግሞ ከመሥሪያ ቤታቸዉ ባልደረቦች የተደመጡት አስተያየቶች ናቸዉ፤

- *የሕክምና ፋኩሊቲ ተባባሪ ዲን በጋዜጦቹ ላይ የወጣውን ጽሑፍ አስመልክቶ የተናገረዉ በአጭሩ ‹‹Nonsense (እንቶ ፈንቶ) ነው›› በማለት ነበር::*
- *የማሕፀን ክፍል ኃላፊዋ ጋዜጦቹን ‹‹Gutter paperes›› አለቻቸው::*
- *አንዲት የኩላሊት ክፍል ነርስ ‹‹እንዴት ይህን ለማለት ደፈሩ?›› አለች::*

ዶ/ር ብርሃኑ ከየካቲት ወር 1986 ዓ.ም አንስቶ የሕክምና ፋኩሊቲዉ የዲፓርትመንት ኃላፊ ሆነው የተሾሙት በዚያው ሰሞን እንደ ነበር ያስታወሱት የአንድ አገልጋይ አስተያየት ደግሞ ለየት ይላል::





*ሁኔታው ሰይጣን በሽሙጥ መልዕክት በማስተላለፍ ዘይቤ (satire) ቤተ ክርስቲያንን (ብርሃኑ ወንጌልን ብቻ ማለት አይደለም) ለማንጓጠጥ ያደረገው አይመስልምን?!*

## *10.4. መለያየት*

የመጥመቃውያን ወንጌላዊት ማሕበር የላከዉ ደብዳቤ የአሳዘናቸዉና ቤተ ክርስቲያኒቱንም አደገኛ ሁኔታ ውስጥ እንደከተታት የተገነዘቡት ሽማግሌዎች መስከረም 4 ቀን 1986 ዓ.ም ተሰብስበው ስለ ወደ ፊቱ ዕጣ ፈንታዋ መክረዉ ነበር:: የዕለቱ ዋነኛ አጀንዳቸዉም ባይሆን ወንበሮቹ እንዲጓጓዙ በእግረ መንገድ የወሰኑት ምናልባት በዚሁ ዕለት ሳይሆን አይቀርም:: የእግረ መንገዱ ዉሳኔ የመስከረም 6ቱን ግርገግር ያስከትላል ብለዉም አይገምቱ ይሆናል::

ለማንኛዉም በመስከረም 4 ቀን ስብሰባቸዉ የደረሱበትን ረቂቅ የዉሳኔ ሃሳብ መስከረም 8 ቀን የአገልጋዮች ጉባኤን ጠርተዉ አካፈሉና ሰፊ ዉይይት አደረጉበት:: ከዚያም ‹‹የብርሃን ወንጌል ቤተ ክርስቲያን ከመጥምቃውያን ወንጌላዊት ወጥታ ራስዋን ችላ በአገር አቀፍ ደረጃ ተቋቁማ እንድትሠራ በአንድ ድምጽ ወሰኑ:: የደረሱበትንም ዉሳኔ መስከረም 9 ቀን 1986 ዓ.ም ከሰዓት በኋላ ለጠቅላላዉ የአባላት ጉባኤ አቀረቡ::

በዚህ መሠረት ለመጨረሻ ጉባኤ ጉዳዩ ለጠቅላላ አባላት ቀረበና ጸደቀ:: ጊዜ ሳያጠፉም ቤተ ክርስቲያኒቱን በሚመለከተዉ የመንግሥት አካል ለማስመዝገብ ተንቀሳቀሱ:: በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ጥቅምት 10 ቀን 1986 ዓ.ም በመንግሥት ተመዝግባ ሕጋዊ ሰውነት አገኘች:: ይህንን ሂደት በቅርብ የተከታተሉና በሽምግልናም የተሳተፉ ሰዎች

እንደሚሉት ‹‹እንደ አዲስ የተመዘገበችዉ ብርሃነ ወንጌል ከስሟ በስተቀር ግን የቀድሞዋ ብርሃነ ወንጌል አይደለችም። ይልቁንም የቀድሞዋ *ብርሃነ ወንጌል* ለሁለት ተከፍላ በሁለት የተለያዩ አመራሮች ራእይ ስር ሆነች፤ የሽማግሌዎቹ ወገን የቀድሞ ስሟን ወረሰ። የመጋቢያኑ ወገን ደግሞ *ብርሃነ ክርስቶስ ተሰኘ፤›› ማለቱ ይሻላል።

አጠቃላይ ሂደቱ እዚህ መድረሱ ግን ቢያንስ በሽማግሌዎች ወገን ለቆሙት አባላት ትልቅ እፎይታና መረጋጋት ፈጠረ። በመጋቢያን በኩል ያለዉም ወገን ማድረግ የሚገባዉን እንዲያደርግ በቁርጥ እንዲነሳ አደረገዉ። የዚያን ዘመኑ የቤተ ክርስቲያን መያዣ መጨበጫዉ የአደናገረዉ የደብረዘይት ቃለ ሕይወት በ/ክ የመዘምራን ቡድን 1985 ዓ.ም፦

**ይነጋል - ይመሻል፣**
**ይመሻል - ይነጋል፣**
**ሌሊቱ ወደ ቀን - ቀኑም ወደ ማታ፣**
**አዲስ እንቅቅልሽ**
**በአዲስ ዘዬ ይዞ - አርጌው ሲፈታ ...**

ሲል እንደ ዘመረዉ ነግቶ እንደ መሸ - መሽቶም እንደ ነጋ ዶ/ር ብርሃኑ እፎይታ ከሚያሳጣ ሌላ ክስተት ጋር ተጋጠሙ። ይኼዉም የሽማግሌዎች ወገን የወሰደዉን እርምጃ ተከትሎ የመጣባቸዉ ‹‹*የመነቀል ጊዜ*›› ነዉ። እንዴቱን በአጭሩ እነሆ!





## 10.5. የመነቀል ጊዜ

ጥቅምት 10 ቀን 1986 ዓ.ም በመንግሥት ተመዝግባ ሕጋዊ ሰውነት የአገኘችዉ ብርሃነ ወንጌል ቤተ ክርስቲያን ኢወአሕ፣ በርካታ ቤተ እምነቶችና ነባር መንፈሳዊ ድርጅቶች በቶሎዉ ይፋዊ እውቅና አልሰጧትም ነበር። ለዚህም ምክንያቱ ብዙ ነዉ። ሁለቱ ወገኖች ጉዳዩን የያዙበት አያያዝና የሂደቱ አፈጣጠን እንዲሁም ችግሩ ተጋንኖ መራገቡ ግር ማሰኘቱ አንዱ ነዉ። በሌላ በኩል ‹‹እኛም ቤት እሳት አለ›› እንዲሉ በወቅቱ በተመሳሳይ ችግር ዉስጥ የነበሩ ቤተ እምነቶች በርካታ እንደ መሆናቸዉ የመለያየት ዝንባሌዎች እንደ አማራጭ መፍትሔ እንዳይለመዱ ለመጠንቀቅም ሲሉ ይሆናል።

በቤተ ክርስቲያናቸው ይፋዊ እውቅና ከአለማግኘቷ ጋር በተያያዘም ዶ/ር ብርሃኑ ከአንዳንድ የብሔራዊና የዓለም አቀፍ አገልግሎቶች ወንበራቸው ላይ መነቀል ጀመሩ። ቤተ ክርስቲያናቸውን ወክለው ከሚሳተፉባቸው የኢ.ወ.አ.ሕ. ቦርዶች፣ ኮሚቴዎች ቀስ በቀስ ታገዱ። በተለይም በኢወክአሕ የወንጌል ሥርጭት ኮሚቴ ሰብሳቢነታቸው መታገዳቸውን የሚያበስረው ደብዳቤ የደረሳቸው ዕለት ውስጣቸው በሀዘን ተቆራምዶ እንደ ከረመ በግል ማስታወሻው ላይ መዝግበውታል።

ከሁሉም *የመነቀል ክስተቶች* ልባቸውን የሰበረው ግን ተግዳሮቱ በክርስቲያናዊ ምስክርነታቸዉ ላይ ጥቁር ነጥብ ጥሎ ከሃያ ዓመት በላይ የጸለዩበትን የወንጌል ጥሪ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ እማዳፈኑ ላይ ማነጣጠሩ ነበር።

በዚህ ጥልቅ የሃዘን ድባብ ዉስጥ ሆነዉ እስከ 1987 ዓ.ም አጋማሽ ድረስ ዘለቁ።

ከዚህ በተቃራኒ ግን የማንኛዉን ሥጋ ለባሽ ልብ ሊከፍል ወይም ሊያማልል በሚችል ደረጃ መንግሥት (ዓለማዊዉ አሰራር) በክብር ላይ ክብር እየደረበ፣ ከረዳት ፕሮፌሰርነት፣ ወደ ተባባሪ ፕሮፌሰርነት፣ ከዚያም ወደ ዲፓርትመንት ኃላፊነት እያሸጋገረ ዝነኞቹ ሐኪሞች ፕሮፌሰር አስራት ወልደየስ እና ፕሮፌሰር ጀማል የተቀመጡበት ወምበር ላይ ተቀምጠዉ አመራር ይሰጡ ዘንድ የሕክምና ፋኩሊቲው ኃላፊ አድርጎ ሾማቸው።

ሲስተር አልማዝ ባለቤታቸው ከቤተ ክርስቲያኑ ወገን ያጋጠማቸዉን መነቀል፣ ከመንግሥት ወገን ደግሞ ሹመቱ ተደራርቦ መምጣቱ አላደናገራቸዉም፤ እንዲያዉም ወደ አዲስ የልቦና መገለጥ መራቸው። ያንን ለባለቤታቸዉ እንዲህ በማለት አካፈሉአቸዉ:-

> *‹‹የመንግሥት ሥራ ከአለመልቀቅህ በስተቀር ሁለመናህን ለእግዚአብሔር እንደ ሰጠህ አውቃለሁ። በዚህ መልክ የምታገለግልበት ዘመን አበቃ!. . . ይኼው ከእያንዳንዱ ሥፍራ ተራ በተራ ተነቀልህ። አሁን ገና በልጅነትህ ለወንጌል ሥራ ለለየህ ጌታ ‹እነሆኝ› የምትልበት ጊዜ ይመስለኛል። አይዞህ እኔም የመንግሥት ሥራ ትቼ ከጎንህ እሆናለሁ። እኔ መቼም እግዚአብሔርን እየታዘዝን ብንራብ እመርጣለሁ››።*

ዶ/ር ብርሃኑም በባለቤታቸዉ ልዩ ማስተዋል እግዚአብሔርን አመስገኑና ወደ ረዥም የጾምና የጸሎት ምሽጋቸዉ ገቡ። ምን ሆነዉ፣ ምን ይዘዉ ይመጡ ይሆን?





# 11. ወደ ከበረዉ ሠረገላ

## *11.1. ነፍሴን መለሳት*

**...አይዞህ!**
**ተራራ እንዲ የተደፋብህ፣**
**ለጊዜው፣**
**የአንድዬ መዳፍ አይደለም!...**
**ተወው! . . .**
**በህውሉ - እስክታደቀው፣**
**ማዕበል - እስክትታጠቅ፣**
**ጋራ ገደሉን የሚያደቅ። . . .**
**ሲለኝ ለቅፅበት**
**በደረቀዉ ሌሊት - ለማሁት።**

(ካልታተመ ጥራዝ)


ይመሻል - ይነጋል፤ ይነጋል - ይመሻልም። የጊዜን ሂደት ማን ሊገታ ይቻለዋል? በጊዜ ሂደት ዉስጥ የአንድን ሥጋ ለባሽ ሕይወት የሚያስጨንቅ ከተራራ ናዳ በላይ ጨፍላቂ ሸክም ምን አለ? ከቀንበር በላይስ አንገት የሚያስደፋ ምን ይገኛል? እግዚአብሔር በምህረቱ ጎብኝቶት ከጎኑ ከቆመለትና የተጋረጡበትን ፈተናዎች እንደ አለፈ ክረምት የሚያስቆጥር ጸጋ ከተሰጠዉ ያ ሰው በስተቀር! ዶ/ር ብርሃኑም ‹‹የሆነባቸዉና የሆነላቸው›› ይኼንኑ ይመስላል። ነፍሳቸዉ ተመለሰች!

ከሁለት አሠርታት በላይ አብሯቸው ለከረመው ለወንጌል ሥራ የመለየት ጥሪ ምላሽ ፈጥነው እንዲሰጡ ውስጣቸው

እንደ ገና የተቀጣጠለበት አጋጣሚዎች ተከታትለዉ መጡላቸዉ። አንዱም ‹‹ፋየር ኮንፈረንስ›› ነበር። ወቅቱ ሚያዚያ 1987 ዓም ነበር። በኮንፈረንሱ በአስር ሺህዎች የሚቆጠሩ ምዕመናን ተካፍለው ነበር። የመጀመሪያውን መልእክት ለጉባዔዉ ያቀረቡት ወንጌላዊው ቦንኬ ሲሆኑ የሚናገሩበት መሪ ቃል ይህ ነበር።

> *‹‹ከዚያም የጌታ ድምፅ ማንን እልካለሁ? ማንስ ይሄድልናል ሲል ሰማሁት። እኔም ‹እነሆኝ እኔን ላከኝ አልሁ።›› (ኢሳ 6፡8)*

የመልእክቱ ይዘት ከሺህዎቹ የጉባዔው ተካፋዮች ይልቅ እግዚአብሔር ለራሳቸው በግል የላከላቸውና ከኃይለኛ ድምፅ የተነበበላቸው እስኪመስላቸው ድረስ ዘልቆ እንደ ተሰማቸውም ራሳቸዉ ለራሳቸዉ መሰከሩ። በዚህ መንፈሳዊ ዐውድ ውስጥ እያሉም እንኳ ‹‹እነሆኝ . . . ላከኝ›› የሚለዉን ውሳኔአቸውን ለልብ ሰዎቻቸው ለመናገር ለምን እንዳመነቱ የሚያውቁት እሳቸው ብቻ ናቸው።




ዓለም አቀፍ የወንጌል ስርጭት ጉባኤ ሴኡል-ኮሪያ





በጥቂት ቀናት ዉስጥ ሁለተኛዉ ዕድል ተከተለ። በፋየር ኮንፈረንስ ሰሞን በውስጣቸው የተፈጠረው የመንፈስ መቃተትና መወትወት ውስጥ እንዳሉ ግንቦት ወር መጀመሪያ ላይ ወደ ኮሪያ በረሩ። የጉዞው ዓላማ በኮሪያ ሴኡል ከተማ የሚካሄደውን ዓለም አቀፍ የወንጌል ስርጭት ጉባዔ ለመካፈል ነበር።

በጉባዔው ላይ በመጻሕፍትና በዜና ዝናቸውን በሩቅ የሚያውቋቸውን ታላለቅ የሚባሉ አገልጋዮችን ለመተዋወቅ ዕድል አግኝተዉ ነበር። አገልጋዮቹ እግረ መንገዳቸውን በሴኡል ከተማ ስታዲዩም የጀማ ስብከተ ወንጌል መልዕክት እንዲያቀርቡ ፕሮግራም ተይዞላቸው ነበር፤ የጉባዔው ተካፋዮች ጥርግ ብለው ወደ ስታዲዩም ሲሄዱ ዶ/ር ብርሃኑ ቀሩ። ምክንያት፡- የዕለቱን ዝናብ የሚጠለሉበት ጃንጥላ ስላልነበራቸው። የእግዚአብሔር ምክንያት ግን ሌላ! ይኼው ከዐውደ እለት ማስታወሻቸው፡-

> *የመጣንበት ስብሰባ ጊዜዉ በጣም የተጣበበ ነው፤ የጌታን ቃል በጥሞና ማንበብ አልቻልሁም። ፕሮግራሙ ላይ እስከ ዛሬ ድረስ የእግዚአብሔር ቃል ስብከት አልተደረገም። የተለያዩ የጥናት ውጤቶችና አስተሳሰቦች ናቸው መድረክ ላይ የቀረቡት። በተጨማሪም እንደ ልብ ተንበርክኮ መጸለይ አይቻልም፤ አመቺ ቦታም አላገኘሁም። ከዚህ ሁሉ የተነሳ ነፍሴ በጣም ተራበች።*
>
> *በዛሬው እለት ዝናብ ይዘንብ ስለ ነበርና ጃንጥላም ስለሌለኝ ስታዲዩም ይካሄድ ወደ ነበረው ፕሮግራም ሳልሄድ ቀረሁ። ጥቂት አካፍቶ ከአባራ በኋላ መጽሐፎቼን ይዤ መቀመጫ ወዳለበት ምግብ ቤት ሄድኩ። ምንም ሳልጣደፍ ቃሉን በስፋት ተመገብሁ። አቤት እንዴት ጥሞኝ ነበር! እያጣጣምኩ የተለያዩ*




ዓለም አቀፍ የወንጌል ስርጭት ጉባኤ ሴኡል-ኮሪያ

*ክፍሎችን አነበብሁ፤ ምግብ ቤቱ ዉስጥ ሁለት ሰዓት ያህል ተቀመጥሁ::*

*ንባቤን ከጨረስሁ በኋላ ወደ ጸሎት ቤት አመራሁ:: ከዚህ በፊት ወደ ጸለይሁበት ቦታ ለመጸለይ ስሄድ ግን ቁልፍ ሆኖ አገኘሁት::*

*አቤት እንዴት ተሳቀቅሁ! እንባ አነቀኝ፤ እዬዬ! ብዬ ለማልቀስ ዳዳኝ:: በዚህ ስሜት ሆኜ ከምድር ቤቱ አካባቢ የሚመጡ ሁለት ወንድሞች አየሁና የጸሎት ቦታ የት ላገኝ እንደምችል ጠየቅኋቸው:: የሆነ ሕንፃ አመለከቱኝ::*

*ሕንፃው የሚያስደንቅ ነው:: በሕንጻው አራት ፎቆች ጥግ ላይ ራሳቸውን የቻሉ ትናንሽ ክፍሎች ለጸሎት ብቻ ተዘጋጅተዋል:: ንፁህ ክፍሎች፣ በደንብ የሚዘጉ፣ በሩ ሲገጥም ከውጪ በኩል ትንሽ ቀይ መብራት ትበራለች:: ክፍሉ ውስጥ በጥሩ ሁኔታ የተሠራች የስፖንጅ መንበርከኪያ አለች፤ ሌላ ምንም ነገር የለም:: በሬን ዘግቼ በጌታዬ ፊት በናፍቆት ቀረብሁ፤*

*ከዚያም" የሕይወቴን ተልእኮ አሰብሁ:: ጻፍኩት፤ ለጌታም አስነበብኩት:: «ጌታ ሆይ አሁንስ በቃኝ፣ የፈለግሽውን አድርገኝ፣ በሕይወቴ የፈቀድከውን አድርግ!» አልኩት::*

*በሴት ልጅ ድምፅ የምናገር መሰለኝ:: ድንገትም እንደ ድንግል ልጃገረድ በሙሽራ ፊት ራሷን በሙሉ ፈቃደኝነት እንደ ምታቀርብ ሙሽሪት ሆኜ ራሴን እንደቀአረብሁ ተሰማኝ::. . .*

*ከዚህ በኋላ እንባዬ ደረቀ ተቀምጬ ቃሉን አነበብሁና እንደገና ተመልሼ ስለ ኢትዮጵያ የወንጌል ሥራ ዝግጅት ጸለይሁ:: እንዲሁም ስለ ሕፃናት ልጆች መዳን፣ ስለ ባለቤቴም ሥራ አጥብቄ ጸለይሁ::*





## 11.2. ‹‹ለአልማዝ ነገርኳት››

በቀን ማስታወሻቸው ያሰፈሩትን ቃላትና አገላለጾች ለእግዚአብሔር የጥሪ ድምፅ ምላሽ ለመስጠት የዘመኑ ክፋትና ጠቅላላው ማሕበራዊ ዐውድ (context) ምን ያህል ከብዷቸው እንደነበር መገመት አያዳግትም:: እስኪ እንደገና አንባቢ ያጢናቸው::

> *‹‹የሕይወቴን ተልዕኮ አሰብኩት፤ ጻፍኩት ለጌታም አስነበብኩት:: ጌታ ሆይ አሁንስ በቃኝ! የፈለከውን አድርገኝ፤ በሕይወቴ የፈለከውን አድርግ!. . .ከዚህ በኋላ እምባዬ ደረቀ::››*

ከአፍላ ወጣትነት እስከ ጉልምስናቸው ድረስ ሲከታተላቸው ለነበረው የጌታ ድምፅ ሁለንተናዋን በፈቃዷ እንደምታስረክብ ሙሽራ ተምሳሌት ምላሽ ሰጡ አይደል!? እምባቸው ደረቀላቸው አይደል? . . . አሁን የጥሪዉን ምስጢር ከነ ሙሉ ታሪኩ ሊሰሙ ለተገባቸው ለሌሎች የሚያውጁበት ጊዜ ተራ ሆነላቸው:: ዐዋጁን ለመስማት ፊተኛ ሆነው የተገኙት ባለቤታቸው ሲስተር አልማዝ ነበሩ:: በዕለቱ ይህንን ማስታወሻ ላይ አሰፈሩ::

> *‹‹የደረስኩበትን (ውሳኔ) ለባለቤቴ ለአልማዝ ነገርኳት:: ምንም አልተደነቀችም:: ጉዳዩን የምትጠብቀው ስለ ነበር ጌታን አመሰገነች:: ቀደም ሲልም ደጋግማ ተናግራኝ ነበር (እንድወስን):: የምሠራውም የሕክምና ሥራ እንዲሁ ማባከን እንደ ሆነ ሊሰማት ከጀመረ ሰንብቷል::*
>
> *እግዚአብሔር በሕይወት ጠብቆ አቆይቷት እኔን በጸሎት ለመደገፍና በኋላም ይህንን ታላቅ ኃላፊነት አብሮ ሆኖ ለማገልገል እንድትወስን ዕድል ስላገኘች ጌታን አመሰገነች::››*

‹‹. . . በሕይወት ጠብቆ አቆይቷት›› የሚለው ሐረግ ሲስተር አልማዝ የተረማመዷቸዉን የሞት ወጥመዶች ብዛትና ዓይነት የእግዚአብሔርንም የማዳን ኃይል ምስክርነት የመስማት ጉጉት ሳይለኩስብን አይቀርም። ግንቦት 30 ቀን 1987 ማታ ላይ ቆመው፣ በዓይነ ልቡናቸው ወደ ኋላ ለዓመታት ተጉዘውና የትዝታ ማህደራቸው ያቀበላቸውን እንዲህ አርገው መዝግበውታል።

> *‹‹አልማዝ እግዚአብሔር ደጋግሞ ከሞት እንደ ነጠቃት አስታወሰች። ፈፅሞ ረስታቸው የነበሩትን አንዳንዶቹን ለመጀመሪያ ጊዜ ያስታወሰቻቸው ዛሬ (30/9/87) ነው።*
>
> *. . .(ለምሣሌ) በልነጅቷ አዳባ (ከቤተሰብ ጋ) በሚኖሩበት ጊዜ ------ ከቤት ከእትዬ ---- ልታስኮበልላት ወደ እነርሱ ቤት ጠራቻት። መሽትሽት ሲል ከቤት ወጥታ መንገድ ጀመረች። ርቃ ሳትሄድ ጅቦች መጮህ ጀመሩ። የመንደሩ ውሾችም ሁሉ መጯጯህ ጀመሩ። የውሾቹ ጩኸት ሲጋጋል ፈርታ ወደ ቤቷ መመለስ ጀመረች።*
>
> *የአካባቢው ውሾች መጯጯህ ያሳሰባቸው ጋሽ ... ጠብመንጃቸዉን አቀባብለው ከቤት ወጥተዉ አደፈጡ። አልማዝ ወደ ቤቷ እየተቃረበች ስትመጣ ጠብመንጃቸውን ወደ እሷ አነጣጥረው ሊተኩሱ ሲሉ ‹‹ተዉ!›› የሚል ድምፅ ሰሙና መተኮሱን አቆሙ። ከዚያም እሳቸው ወደ አሉበት አቅጣጫ እየተጠጋ የመጣው ነገር ምን እንደሆነ ለማጣራት ለትንፋሽ ያህል ጠበቁ። ከዚያም እሷ መሆኗን ሲያውቁ ራሳቸውን ይዘው መጮህ ቀጠሉ።. . .*
>
> *ሁለተኛው ከሞት የተረፈችበት አጋጣሚ የተፈፀመው በሕፃንነት ዕድሜዋ ነው። በዕለቱ ከባድ ዝናም ዘንቦ አካባቢዉ በጎርፍ ተጥለቅልቆ ነበር። አልማዝ ወደ ማዶ መንደር ለመሻገር ወደ ዚያው እየሄደች ነበረች። ወንዙ አጠገብ ደርሳ እግሯን ወደ ውኃው ለማጥለቅ ጥቂት ርምጃዎች ብቻ ነበሩ የቀሯት።*





> *ልክ በዚህ ሁኔታ እያለች አንዲት ወፍ ወንዙ ዳርቻ ከሚገኝ ዛፍ ቅርንጫፍ ላይ ሆና በኃይል ስታዜም አየች። በወፏ ዜማ ተገርማ አንጋጣ ቆማ ታዳምጥ ጀመረች። እያዳመጠችም ሳታውቀው ጥቂት ደቂቃዎች አሳለፈች።*
>
> *እንዲህ በወፏ ዜማ ተመስጣ በነበረችነት ሰዓት አንዲት ሴት ከሩቅ አይታት እየሮጠች መጥታ ወደ ቤቷ አደረሰቻት።*
>
> *ከባለቤቴ ጋር እንዲህ ስንነጋር አመሸን። ገናም ብዙ ታላላቅ ወንዞች በአንድነት እንደ ምንሻገር ጌታ ያሳያትን መልእክት ነገረችኝ። በታላቅ ሃሴት ውስጥ ሁኜ ሌሊቱን አሳለፍሁ።*

## 11.3. ከቤት ወደ ዉጭ

ዶ/ር ብርሃኑ ጥሪያቸውን በተለመከተ በመጀመሪያ የባለቤታቸውን ስምምነትና ድጋፍ የማግኘቱም ጉዳይ ትልቅ ከበሬታ ሰጥተውት ነበር። ለሲስተር አልማዝ ደግሞ ጉዳዩ እንግዳ አልነበረም። እንዲያውም ባለቤታቸው ለወንጌል ሥራ ገና የሚወጡበትን ጊዜ ሳይሆን ዘመናቸውን ሁሉ እንደ ሉቃስ ድንኪን እየሰሩ ***መንግሥት በሚቆርጥላቸዉ ቀለብ ለወንጌል አገልግሎት የተሠማሩ*** አድርገው ነበር የሚቆጥሯቸው። በሌላ አገላለፅ ሲስተር አልማዝ የባለቤታቸውን የሕክምና ሥራ ከሐዋርያው ጳውሎስ የድንኳን ሰፊነት ሥራ ለይተው አያዩትም። ይህ መቸም ለሁለቱም እጅግ መታደል ነው። ዶ/ር ብርሃኑ እንዲህ የቤት ሥራቸውን ከጨረሱ በኋላ ስለ ጥሪያቸው ማወቅ ይገባቸዋል

ብለው ለአስቧቸው ወገኖች ቀጠሮ እያስያዙ። ሥራዬ ብለው ማከፈልን ቀጠሉ።

ተረኛዋ ባለማዕረግ የክርስቶስ አካል የሆነችው ቤተ ክርስቲያን ነች።

ሰኔ 12 ቀን 1987 ዓም በተደረገው የብርሃነ ወንጌል ቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ስብሰባ ተገኝተው በእርጋታ፣ በተቀናጀ የሀሳብ ቅደም ተከተልና በትሕትና የደረሱበትን ውሳኔ አስረዱ።



የቤተክርስቲያን ሽማግሌዎች ሲጸልዩላቸው

ከወቅቱ የውስጥ ችግሮች የተነሣ የአንዳንዶቹን ቅን ድጋፍ ስለ ማግኘታቸው ጥርጥር ሳይገባቸው አልቀረም። የአገኙት ምላሽ ግን ቀደም ሲል ሲስተር አልማዝ በቤታቸው





ከነገሩአቸውም ይልቅ ፍሬ ነገሩ በጣም የተብራራ ነበር። ሁኔታውን በዐውደ ዕለት ማስታወሻቸው እንዲህ ሲሉ መዘገቡት።

*«. . .ሽማግሌዎች ጉዳዩን በልባቸው ይጠብቁት ስለነበር ምንም አላስደነቃቸውም፤ እግዚአብሔርን አመሰገኑ። እንዲያውም ራሳቸው አስቀድመው ሊያናግሩኝ ተመካክረው እንደነበር ገለጹልኝ።»*

ከእሉ በኋላ በዕለቱ ሽማግሌዎች ከሰጡት አስተያየቶች ዋና ዋናዎቹን እንደሚከተለው አሰፈሩ።


- *«ወንድም ንጉሤ ከዚህ በፊት ሌሎች ሰዎች ስለእኔ የአገልግሎት ጥሪ ያዩትን አስደናቂ ራዕይ አስታወሰኝ።*
- *ገብርዬ፦ ገንቦ በሚያክል እቃ ችቦ ለሰዎች ስታከፋፍል ለእኔም እንደ ደረሰኝ አይቼ (ራዕይ). . . እንደነበር የነገርኩህን ታስታውሰዋለህ? አለኝ።*
- *ካፕቴን ወጋየሁ፦ ባለቤቱ በሕልሟ ያየችውን ነገረኝ። በህልሟ ውስጥ «ዶ/ር ብርሃኑ ብላ መጥራት እየፈለገች «ፓስተር ብርሃኑ» ለማለት እንደ ተገደደች የነገረችውን መሰከረ።*
- *በመጨረሻም «ሁሉም እንኳን ደስ አለህ» እያሉ አቅፈው ሳሙኝ፤ ጌታ የተባረከ ይሁን።*

ይህ ዕለት ለዶ/ር ብርሃኑ ልዩ የምስጋና ቀን ነበር። እግዚአብሔር በቤቱ ከሾማቸው ሰዎች ይህን መሰል የመንፈስ ቅዱስ ምስክርነት ከመስማት የበለጠ ምንስ ሊያስደስታቸው ይችላል!?



የቤተክርስቲያን ሽማግሌዎች ሲጸልዩላቸው

ከዚህ በኋላ ለቤተ ክርስቲያናት ተቋማትም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ጉዳዩን ለመግለፅ ውስጣዊ ነፃነት ተሰማቸው፡፡ ይሁን እንጂ ከሰውም ሰው አለ፤ እግዚአብሔር የውስጡንና የውጩን የአሰማመረለት፡፡ ከወንድምም ወንድም አለ፤ የልቡና የአንደበቱ ህብር የሰመረለት፡፡



ለወንጌል አገልግሎት ለመለየታቸውን
ከቤተክርስቲያናቸው የተሰጣቸው የምስክር ወረቀት






እነዚህን ወገኖች በጥንቃቄ እየመረጡ ለወንጌል ሥራ መለየታቸውን አዋዩአቸው፡፡ በእውነቱ ሁሉም ወገኖቻቸዉ ጉዳዩ አዲስ አልሆነባቸውም፡፡ ይሁን እንጂ በዓለም ፊት የከበረና የዚህ ዓለም ተድላ እጅግ ማትረፊያ የሆነውን ሙያቸውን ለመተው መወሰናቸው ብዙዎችን ሳያስገርማቸው አልቀረም፡፡ ከፊሎቹ ደግሞ ‹‹ሳሱላቸው››፡፡ የዘመኗ ቤተ ክርስቲያንና ልጆቿ የዚህን ሰው መስጠት የምር ይገነዘቡለት ይሆን? እያሉ፡፡ ሌሎች ደግሞ ስጋትና ስስት በተቀላቀለበት ስሜት እንደገና በጥልቀት ሊያስቡባቸውና ሊጠነቀቁባቸው የሚገባቸዉን ጉዳዮች እየመዘዙ መከሩአቸው፡፡ ከምክሮች ይጥቂቶቹን እንመልከት፡-

- *‹‹የሙሴን ጥሪና ተልዕኮ አስታውስ፤ ሙሴ የተልዕኮውን የመጀመሪያ እርምጃ በወሰደበት ጊዜ የተፈጠረውን ችግር አስታውስ!*

- *የሥራ መልቀቂያ ማመልከቻ ከማስገባትህ በፊት በቆይታ አስብበት፤ ጸልይበትም፡፡*

- *በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት የነበሩት ሃያ አራት ሽግሌዎች አክሊላቸውን በእግሩ ስር እንዳስቀመጡ፣ አንተም የሕክምና ሙያህንና የተሰጠህን ሹመት በጌታ እግር ሥር ጥለህ፣ በምትኩ ዘላዓለማዊ ዋጋ ላለው ለመንግሥቱ ሥራ የሚስፈልገውን ጸጋ እንድትቀበል እጸልያለሁ፡፡*

- *ቀድሞም ቢሆን ከሥራህ ይልቅ ይበልጡን የምትጨነቀው ለጌታ ሥራ ነበር፡፡ የደረስክበት ውሳኔ ምንም አያስደንቀኝም. . .፡፡*



ለወንጌል አገልግሎት ለመለየታቸውን ከቤተክርስቲያናቸው የተሰጣቸው የምስክር ወረቀት

- *ጌታ ሆይ! ከአሁን ወዲያ በዚህ ሰው አማካኝነት የምትሠራውን ታላቅ ሥራ እጠብቃለሁ።. . .*
- *ወንድሜን ተቀብዬዋለሁ፤ አጠገቡም እቆማለሁ››*

‹‹ . . . ስምህን . . . አውጃለሁ›› ሲል ለሙሴ እንደተናገረለት ሆነና ዓመቱ ከመገባደዱ በፊት ለመንግሥቱ ሥራ የመለየታቸው ዜና ከሞላ ጎደል በሁሉም ወንጌላውያን ቤተ ክርስቲያናት ማሕረሰብ ዘንድ ተሰማ።

## *11. 4. ‹‹ደህና ሁኚ ሹመቴ››*

*‹‹ነገ መስከረም 1 ቀን 1988 ዓ.ም ነው። የሥራ መልቀቂያ ማመልከቻ ለዩኒቨርሲቲ እንዳቀርብ ከአልማዝ ጋር ተነጋገርን።...*

*ማለዳ አንድ ህልም እያየሁ ነቃሁ። የነቃሁትም ‹እየሱስ ክርስቶስ አይለወጥም› የሚለውን መዝሙር እየዘመርኩ ነበር። እንቅልፌን ጨርሼ በ11:00 እንደ ተነሳሁ አጭር ጸሎት አድርጌ የጌታን ቃል ማንበብ ቀጠልሁ። መዝሙሩ የተወሰደበትን ዕብራ.13 በሙሉ ልቤን ከፍቼ አነበብኩ።. . .*

*እንደገናም መንፈስ ቅዱስ ወደ ሌላ የቃሉ ተመስጦ ወሰደኝ ‹‹አምላኬም ወሰን ከሌለው ብልጥግናው የሚያስፈልጋችሁን ሁሉ በክርስቶስ ኢየሱስ በክብር ይሞላችኋል›› (ፍሊፕ4:19) ይላል ቃሉ።*

*. . .በአዲስ ዓመት ዋዜማ ጌታ በዚህ ድንቅ ሁኔታ ተናገረኝ። እጅግ አባርከዋለሁ።*

*ንግግሩ ግልፅ ነው፤ ልወስደው ስላልኩትም እርምጃ እርግጠኛ ሆኛለሁ።*





ዶ/ር ብርሃኑ ሀብቴ በባህርያቸው ጥንቁቅ ናቸው። የለብለብ ሥራ አይወዱም። የሥራ ስንብት ለመጠየቅ እርግጠኝነት ተሰምቶኛል ከአሉ በኂላ እንኳን ለአንድ ወር ያህል ዙሪያ ገባውን ሲፈትሹ ከረሙ። የድካም ነፋስ የሚያሾልክ ምንም ቀዳዳ አለመኖሩን ለማረጋገጥ ባለቤታቸው ለአንድ ዙር የምክክርና የጸሎት ጊዜ እንዲገያኙ ዕድሉን አመቻቹላቸው። ጥንቃቄአቸው ይደነቃል። ግን ተቀድመው ነበር።

> *‹‹. . .ይገርማል በትናንትናው ምሽት ቀድማ ውሳኔ አድርጋለች። የወሰነችውም የወንድም ዳንኤልን መጽሐፍ አንብባ ነው። ወንድም ዳንኤል የጌታ ጥሪ ደርሶት ውሳኔ አድርጎ ነበር። ከሥራው ለመለየት ግን ሦስት ዓመት እንደ ፈጀበት ያም ጊዜ ራሱን ለማዘጋጀት እንደ ተጠቀመበት ያነበበችውን ነገረችኝ። በመቀጠልም* ከዚህ ምስክርነት ውስጥ እግዚአብሔር ያስተማራት ነገር ‹ብርሃኑ አስቀድሞ ዝግጅቱን ስለ ጨረሰ ለጥሪው ታዝዞ አሁኑኑ ቢወጣም እግዚአብሔር ለቤተሰባችን ኃላፊነት እንደሚወስድ እርግጠኝነት እንደ *ተሰማት ነገረችኝ።›› (29/1/88)*


በዚሁ ዕለት ሌሊቱን የማመልከቻውን ረቂቅ አዘጋጁ።

> *‹‹የሕክምና መስክ ሥራዬን ሙሉ በሙሉ በመተው የአገሬን ሕዝብ ማሕበራዊና መንፈሣዊ ሕይወት መሠረታዊ በሆነ መንገድ ለመለወጥ ወደሚያስችለኝ አገልግሎት ለመሰማራት ወስኛለሁ. . .፤ የሚል ነበር የደብዳቤው ይዘት።*

በማግሥቱ መስከረም 30 ቀን 1988 ዓም ደብዳቤአቸውን ለዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት አቀረቡ።

በመሠረቱ ዶ/ር ብርሃኑ ተወዳጅ ባለሙያ፣ መምህርና የተቀናጀ ተክለ ሰውነት (ሰብዕና) ያላቸው የሥራ መሪም ናቸው።

የፋኩሊቲው ዲን ሆነው በቆዩባቸው ዓመታት በቅንነትና ሁሉን በእኩል ዓይን እያዩ በመምራታቸው የተዝረከረኩ ዙር ድምሮች እንዲስተካከሉ አድርገው ነበር።



በሕክምና ፋኩሊቲ በሚያስተምሩበት ወቅት

በመሆኑም የዩኒቨርሲቲው ፕሬዝዳንት ደብዳቤው ሲደርሳቸው እንደ ዘበት አላዩትም። ወዲያው ስልክ ደወሉላቸውና፡-





*«It is sad but I understand you! አሳዛኝ ጉዳይ ነው፤ ግን እኔ በደንብ እረዳሃለሁ፤»* አሏቸው።

ከአንድ ወር ተኩል በኋላ ዶ/ር ብርሃኑ ከፕሬዘዳንቱ ጋር በሌላ ጉዳይ ተገናኝተው ነበር። አጋጣሚውን በመጠቀም ስለ መልቀቂያው አነሱባቸው። ሁሉም ነገር በጥሩ ሂደት ላይ መሆኑን አረጋገጡላቸውና የሆነ ቃል ጣል አረጉላቸው።

*«ምንም እንኳን አንተ ወደ ምትሔድበት ዓለም ዓይነት ባይሆንም እንኳን እኔም . . .»*

ነገሩን ሳይቋጩ ተዉት። በአጭሩ ግን በጀመርከው ምርጫና ውሳኔ ቀጥል ለማለት ያነሱት ንግግር ነበር።

ፕሬዘዳንቱ መልቀቂያውን ከመፈረማቸው በፊትና ባላሰቡበት ወቅት ሌላ የዩንቨርሲቲ ፕሬዘዳንት ተሾመ። አዲሱ ሹም ጉዳዩን «ሀ» ብለው ጀመሩት። 6ኛው ወር ላይ ሥራቸውን እንደሚለቁም በስልክ ጠየቋቸውና በቂ ማብራሪያ ሰጧቸው።

«እሺ አንተ ካልክ። እኔ እንኳን ቅር የተሰኘሁበት ጉዳይ ከአለ ተቀምጠን እንነጋገር ልልህ ነበር። ምክንያትህ ግን ይህ የነገርከኝ ጉዳይ ከሆነ እኔም ልደግፍህ ይገባኛል። . . . I will not stand on your way! (በመንገድህ ፊት ጋሬጣ አልሆንብህም) አሏቸው። እንዳሉትም አደረጉ።

በቀናት ልዩነት መልቀቂያቸውን ፈረሙላቸው። እነሆ መጋቢት 7 ቀን 1988 ዓም የሐኪሙ፣ የመምህሩና የፋኩልቲው ዲን ዶ/ር ብርሃኑ የመጨረሻ የመንግሥት



በሕክምና ፋኩሊቲ በሚያስተምሩበት ወቅት

መ/ቤት ሥራ ውሎ ሆነላቸው። ነጭ ጋውናቸውን ሰቅለው የግል ሰነዶቻቸውን ሸክፈው ወደ ቤታቸው ገቡ።

## 11.5. ሽኝት

‹‹ሰው የዘራውን ያንኑ ያጭዳል›› እንደሚባለው ዶ/ር ብርሃኑ በሕክምና ፋኩልቲና በዲፓርትመንቱ የዘሩትን ፍቅር፣ ትህትና፣ ቅንነት፣ ትጋትና ችሮታ. . .ወዘተ የዚያኛው ዓለም ሰዎች መሰከሩ። የሽኝቱ ሥርዓት የተከናወነው በሁለት ዙር ነበር ሰኔ 4 እና 13 ቀን 1988 ዓም። የፋኩሊቲው ሠራተኞች አክብሮታቸዉን የገለጹበት ሁኔታ ከዚያ ቀደም ታይቶ አይታወቅም። የአዘጋጁላቸዉ ስጦታ ብቻ ብር 1110.00 (አንድ ሺህ አንድ መቶ አስር ብር) የሚወጣ ትልቅ ባለመስቀል ሀብል እና ትልቅ የጣት ቀለበት ነበር።

ይሁን እንጂ የዶ/ር ብርሃኑን ሥራ መልቀቅ በተመለከተ የበርካቶች ግንዛቤ የደበዘዘ ነበር። ‹‹ሰው እንዴት ለሃይማኖት ብሎ ይህንን በዓለም ፊት የከበረ ሥራና ሹመት መሥዋዕት ያደርጋል?›› የሚሉም ከመካከላቸው ነበሩ። ሌሎች ደግሞ ሆድ በሚያባባ ድምፀት ‹‹አጎደልከን!›› ይሉ ነበር።

በሥነ ሥርዓቱ መጨረሻ አንድ ሕንዳዊ የሥራ ባልደረባቸው የተነገራቸውን ግን በልዩ ሁኔታ ልባቸውን ነክቶት ነበር።

> *‹‹ሰዎች ሲሰናበቱኝ አንድ ሕንዳዊ ፕሮፌሰር ሰውን ሁሉ አቁሞ እጄን ጨበጠ። እንዲህም አለኝ፤ ሥራህን የምትተወው ስለ ሃይማኖት እንደሆነ ጭምጭምታ ሰምቻለሁ። በአገሬ ተመሳሳይ ታሪክ አውቃለሁ። እንግሊዝ አገር የተማረና በኢንጂነሪንግ PPHD ድግሪ የተቀበለ አንድ የሂንዱ ሃይማኖት ተከታይ ሰው ነበር። ይህ ሰው ሙያውንና ያለውን ሁሉ ትቶ በሂማሊያ ተራራ ላይ ወደ ሚገኙት ገዳሞች ገብቶ ካገኝና የሂንዱ ቅዱስ ሰው ለመሆን በቃ። አንተም የወሰድከውን እርምጃ የሚተካከል ምንም ነገር እንደሌለ ይገባኛል።*
>
> *በመካከላችን ሳለህ በሠራኸው ሥራ እንከራብሃለን። ትልቅ ምሳሌነት ትተህልን ነው የአለፍከው፤ ብሎ ተሰናብቶኝ ሄደ። የእግዚአብሔር ስም የተባረከ ይሁን!››*

***

ሌሎችም እንዲሁ የመሰላቸዉን ተናገሩ፦

- *‹‹ነገሩን ለመቀበል ያስቸግረኛል፤ አስደንጋጭ ውሳኔ ነው።››* (ተባባሪ ዲን)
- *‹‹አንድ ጥሩ ዲን አገኘን ስንል ይተወን?!››* (አንዲት የኮሚዩኒቲ ሄልዝ ክፍል ጸሐፊ)
- ‹‹መልቀቂያህ እጅህ ሳይገባ ብደርስበት ኖሮ ምናልባት ጥያቄ አስነሣ ነበር።›› (ዶ/ር ከበደ ታደሰ)
- *‹‹ደንቡን ተከትሎ ስለ አመለከተ ምንም ማድረግ አልቻልንም፤ አመለጠን።››* (ፕሮፌሰር ሞገሴ አሸናፊ)
- *‹‹ወፍራም ዶላር አግኝተህ ነው አሉ!››* . . . (አንዱ ጎበዝ)
- *እሰይ! . . .ጥቁር አንበሣን ረግጠኸው ወጣህ አይደል?!››* (የወንጌል አማኞች)

# 12. ራእይና አድማሱ

**ያጥቢያ ኮከብ ተስፋ - ምሽት የሚያነጋ፣**
**ዕድሜ የሰጣችሁ፣**
**ማዕረግ ያደላችሁ፣**
**ለነገ እንድንሆራ - እጃችሁን ስጡን፣**
**ባ'ሳማው መገስጥ - በፍቅሩ አበጃጁን፡፡**
**ማለዳን አብሣሪ - ምሽት የሚያነጋ፣**
**ጨለማን የሚሽር - ቃል አለ ከኛ ጋ'፡፡**

*(ከኮመፓሽን - ኢትዮጵያ ህፃናት ህብረ ዝማሬ የተወሰደ)*

## *12.1. ፕሪዉ - እንደ ባርናባስ*

*አንድ ያልገባኝ ምስጢር ነበር፤ እንደገና፣ እንደገናም ደጋግሞ እንዲያብራራልኝ የምፈልገው ጥያቄ...! ለመሆኑ የሰዎችን ሕይወት ከማዳን የበለጠ ምን መንፈሣዊ ተግባር ይገኛል? የስንት ወገኖቹን ሕይወት የሚታደግበት የሕክምና ሥራዉን ለቆ እንዴት ወደ ሌላ መስክ ይሰማራል? ገና ያልተረዳሁት ምስጢር ነው? ስለዚህም መርዶውን ስሰማ መቀበል አቃተኝ፤ እስከአሁንም መሞቱን መቀበል እንደ አዳገተኝ አለሁ፡፡ (ፕ/ር ከበደ ያሌ፣ ቃለነምልልስ)*

የፕሮፌሰር ከበደ ጥያቄ የብዙ የሙያ አጋሮቻቸዉ፣ የባለ አእምሮዎችና በቅርብ የሚያዉቃቸዉ ሕዝበ ክርስቲያን ጥያቄ ነበር፡፡ ዶ/ር ብርሃኑ ስለ ተጠየቁ ብቻ ወይንም ለመናገር ዕድልና ጊዜ ስላገኙ ሁሉን ዝርግፍ አድረገዉ የሚያወሩ ሰዉ አይደሉም፡፡ ይልቁንም ለማን? መቼ? እንዴት? መናገር እንደ ሚገባቸዉ ማብላላቱ ከማዉራቱ በላይ የሚያስጨንቀቸዉ

ይመስላል፡፡ መናገር ካለባቸዉ በሃሳብ የተጠቀጠቁ ጥቂት ቃላትን ይጥሉና ቀሪዉን ሰዎች ከተግባራቸዉና ከሕይወታቸዉ እንዲረዱ ሰተዉን ይመርጣሉ፡፡ ከአንደበተ ቁጥብ ባህርያቸዉ ጋ በተያያዘ በአንድ ወቅት ሰዎች የፕሮፌሰሩን መሰል ጥያቄ አንስተዉባቸዉ የመለሱትን መልስ ደቀ መዝሙራቸዉ የሆነ አገልጋይ መስክሮላቸዋል፡-

> *‹‹ዶ/ር ብርሃኑ ያንን ትልቅ ሥፍራ ትቶ እንዴት ወደ ሙሉ ጊዜ የወንጌል ሥራ ሊሠማራ ቻለ? ብለዉ ሲጠይቁት፡- በዚያ ወንበር ላይ ተቀምጠዉ፣ ያንን ሥራ ለማከናወን የሚመኙ፣ የሚሠሩም ብዙ ሰዎች አሉ፤ ተጨማሪ ባለሙያዎችንም ማፍራት ይቻላል፤ ይህንኛውን ሥራ ግን በመለኮታዊ ጥሪ የተመረጡት ብቻ ናቸው የሚሠሩት›› የምትል ምላሽ ይሰጣል፡፡*

ለሙሉ ጊዜ አገልግሎት ራሳቸዉን ለመስጠት በወሰኑ ሰሞን ተመሳሳይ ጥያቄ ከአቀረቡላቸዉ ሰዎች መካከል የትዳር ጓደኛቸዉ ሲስተር አልማዝ ናቸዉ፡፡ ከባለቤት የበለጠ ምንም የቅርብ ሰዉ ባይኖርም የማሣዉ ባለቤት ከሆነዉ ከጌታ እግዚአብሔር ዘንድ ግልጽና የተብራራ ፈቃድ ሳያገኙ ይህንን - ያንን ለማለት እንዴት ተቆጥበዉ እንደ ነበረ ዐዉደ ዕለታቸዉ ይመሰክራል፡-

> *‹‹በትናንትናው ዕለት ባለቤቴ ስለ ጥሪው ነገር ምን ልታደርግ አስበሃል? ስትል ጠየቀችኝ፡፡ ይህንን ዕቅዴን አካፈልኳት፡-*
>
> *. . .በፊቴ የምጓዘውን መንገድ በትክክል እንዳውቅ የዝግጅት እርምጃዎች እንድወስድ በልቤ ተቀምጧል፡፡*
>
> *. . .በቅርቡ የ3 ቀን የጾምና የጸሎት ፕሮግራም ይኖረኛል፡፡ . . .ዝግጅት ማድረግ እንድ ጀምርም እጸልያለሁ፡፡. . .*





> *በመጋቢት ወር የ21 ቀን የጾምና ጸሎት ለመውሰድ የዓመት ፈቃድ እወስዳለሁ፡፡ በዚህ ፕሮግራም የአገልግሎቴን ዝርዝር አቅጣጫዎችና ግቦችን ከጌታ እቀበላለሁ፡፡. . .*
>
> *ለአገልግሎቱም የሚያስፈልገኝን ቅባት ጌታ ይሰጠኛል ብዬ አምናለሁ፡፡›› (ዐውደ ዕለት ጥቅምት 20 ቀን 1988)*

በመሠረቱ የወንጌል አገልግሎት ለዶ/ር ብርሃኑ አዲስ ጉዳይ አይደለም፡፡ ይህኛውን ዝግጅት አዲስ የሚያደርገው ነገር ቢኖር ሙሉ ጊዜአቸዉን መስጠታቸዉና መሥዋዕትነቱ መጨመሩ ነው፡፡ ‹‹አሁን ዝግጅቴን መጀመር አለብኝ›› በሚሉበት በዚያ ወቅት እንኳን ለኢትዮጰያ የወንጌል ስርጭት ስልት በተመለከተ አንድ የጥናት ጽሑፍ እያዘጋጁ ነበር፡፡

የጥናት ጽሁፉን የአቀረቡት ለወርልድ ቪዥን መማክርት (ኮንሰልቴሽን) ጉባዔ ሲሆን በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ ትኩረት ያደርጋል፡-

- ሁሉም አብያተ ክርስቲያናት ባለ ድርሻ የሚሆኑበት ብሔራዊ የወንጌል ስርጭ ስልት መንደፍ፣
- የወርልድ ቪዥን መንፈሣዊ ዘርፍና የኢወአሕ-ን በመጠቀም የማስተባበርና የማትጋት ኃላፊነቱን እንዲወስድ፣

በዚህም፡-

- የቤተ ክርስቲያናት ሕብረቶች በየገጠሩ እንዲስፋፋ ማድረግ
- የጸሎት ሕብረቶችን ማቋቋም፣
- ገጠሮችን በተለይም የአርብቶ አደር አካባቢዎችን ወንጌል አገልጋዮች ማሠልጠን፣ ማነቃቃትና ማበረታት፤ ወዘተ..

ይህንን መሰሉን ጥናት በሚያቀነባብሩበት ወቅት÷ በአንድ ማለዳ ጸሎት በተንበረከኩበት ቅጽበት የሚሰማሩበትን የአገልግሎት መስክና ˙መልክዓ ምድራዊ ገጽታ የሚያሳያቸውን ራዕይ ተቀብሉ። የሁኔታውን ሙሉ ሥዕል የሚያሳየንን ይህንን ማስታወሻ ትተውናል።

> *‹‹ከጸልይኩ በኋላ የጌታን ቃል ለማንበብ ተቀመጥሁ። ወዲያውኑ የበርናባስ አገልግሎት ወደ ፊቴ መጣልኝ። ሳስተውለው ይኼ ሰው ለካንስ ፕሮሞተር (Promoter) ሆኖ ነበር የሚያገለግለው።. . .*
>
> *በቆጵሮስ የሚኖር ዮሴፍ የሚባል አንድ ሌዋዊ ነበር። ሐዋርያትም በርናባስ ብለው ጠሩት። ትርጉሙም የመፅናናት ልጅ (Son of Encouragement) ማለት ነዉ። ገንዘቡን አምጥቶ በሐዋርያት እግር ስር አስቀመጠ (የሐዋ 4:36—37)። ሐዋርያት በርናባስ የሚለዉን ስም የአወጡለት አገልግሎቱን አይተው ነበር። በርናባስ፦ እንደ ስሙ እንዲሁ የሆነለት ሰው ነው።*

- *ጳውሉስን Promote አደረገ። ጳውሉስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ለመቀላቀል ሲሞክር ሁሉም ፈርተው አግልለውት ነበር። በርናባስ ግን በግል ሄዶ አገኘው፣ አምጥቶ ከሐዋርያት ጋር አስተዋውቆ ቀላቀለው። (ሐዋ 9:27)*

- *በአንጾኪያ የነበረውን የጌታ ሥራ ፕሮሞት ያደረገው በርናባስ ነው። በጳውሉስና በበርናባስ አገልግሎት ምክንያት የአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን ለነብኚዎችና ለነቢያት ክፍት ነበረች።*

- *ነቢያቱ የተናገሩት ተፈጽሞ ረሐብ በተከሰተ ጊዜ ርዳታ በማሰባሰብ ምላሽ ለማድረግ ቀዳሚ የሆነቺው የአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን ነች።*

- *በበርናባስና በጳውሉስ አገልግሎት ዓለም አቀፍ የወንጌል ሥራ መሠረት ተጥሏል።*





- *ሀሳቡ ግልጽ ነው። የእኔም አገልግሎት ፕሮሞተርነት ነዉ። እግዚአብሔር መንገዴን እየቀደመ ፈቃዱን በሕይወቴ ይፈጽም፤ አሜን! (መስከረም 1 ቀን 1988)*

‹‹ሁላችንም የእግዚብሔር የእጅ ጽሑፎች ነን›› ያለው ማን ነበር?! አዎ! የዶ/ር ብርሃኑ ወደ ፊት የሚሠማሩበት አገልግሎት ተምሳሌታዊ መገለጫ እንዲሆን የእግዚአብሔር እጅ ጽሑፍ የበርናባስ ሰብዕና እና የአገልግሎት ሕይወት ሆኖ ተገኘ። በሌላ አገላለፅ የዶ/ር ብርሃኑ የአገልግሎት ጥሪ ልክ እንደ ባርናባስ፦

- ጳውሎሶችንና እግዚአብሔር በጳውሎሶች ዉስጥ የአስቀመጠዉን ጸጋ መረዳት፣ ተረድቶም ወደ ፊት ማምጣት፣ ጸጋቸውን መጠቀም፤ ፕሮሞት ማድረግ፤
- ቤተ ክርስቲያናት ለወንጌል ሠራተኞች፣ ለመንፈስ ቅዱስ ድምፅ ክፍት እንዲሆኑ ማነቃቃት፤

- ደቀ መዛሙርትን በማፍራት ቤተ ክርስቲያናትን፣ አገልጋዮችን ማነሣሣት፣ ማነቃቃት፣ ማዘጋጀት ለክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን በዓለም አቀፍ የወንጌል ሥራ ማሰማራት፣
- ሙሉውን ሰው ለማገልገል ፍላጎቱን ለማሟላት አስፈላጊዉን ምላሽ ፈጥኖ ማቅረብ . .

(በነገራችን ላይ በኤክሴሺያ ተነሺ አገልግሎት የያዙት ኃላፊነት የሚታወቀው ‹‹ፕሮሞተር›› በመባል ነው። ስያሜዉ ግን ለብዙዎቻችን ፓስተር፣ ወንጌላዊ ማለቱ የሚቀለንን ያህል ገና የተዋሃደን አይመስልም፡)።

## 12.2. የአገልግሎት አድማስ

አገልግሎታዊ ማንነታቸው፣ አጠቃላይ ይዘቱና ባህርይዉ ታወቀ:: ሥፍራውስ? ድምፀሩስ? አንዳንድ ጊዜ አንዳንድ እውነቶች በሁለተኛ መደብ አገላለፅ ለመተረክ አይመቹም:: ሆን ተብለው የተጋነኑ ያስመስላቸዋልና!:: ስለሆነም ጸሐፊዉ የባለ ታሪኩን የብዕር ቅርስ መጠቀሙን መረጠ::

> *‹‹ሌሊት ሕልም አየሁ:: በሕልሙ ውስጥ ከአንድ ሰው ጋር እነጋገር ነበር:: ‹ሰውዬውንም ፕሮሞተር ሆኜ እንደ ማገለግል አውቃለሁ፤ ነገር ግን የት እንደማገለግል አላውቅም› እያልኩ ሳነጋግረው በፊቴ የአፍሪካ ካርታ ብልጭ! ድርግም! እያለ ታየኝ:: እግዚአብሔር ስሙ ይባረክ! ወደዚያ ደረጃ እንዴት እንደምሻገር መንገዱ ይታየኛል:: (ዐውደ ዕለት መስከረም 19 ቀን 1988 ዓም)*

በለጋ ዕድሜያቸው የኢትዮጵያን ካርታ እያሳዩ ‹‹ብሔራዊ ጥሪ አለብህ፣ ከበደል ራቅ›› ሲል የመጣላቸዉ ጥሪ ወደ አህጉር ደረጃ ከፍ አለ ማለት ነዉ:: በጥቂቱ የታመነ በብዙ ይሾማልና:: ሹመቱን ለማወጅ ግን አልቸኮሉም:: ይበልጡን ይብራራላቸዉ ዘንድ የጌታን ፊት ለመፈለግ የሰባት ቀናት ጾምና ጸሎት ወሰዱ:: አራተኛው ቀን ላይ ከላይ የተጠቀሰውን መገለጥ የሚያፀና ሌላ መገለጥ መጣላቸው::

> *‹‹በትናንትናው ዕለት አራተኛውን የጾምና ጸሎት ቀን አሣልፌዋለሁ:: በዚህ ማለዳ ከእንቅልፌ ነቅቼ ሳለሁ ‹GONDWANALAND› የሚለውን ቃል በውስጤ ሰማሁ:: ይህን ቃል ከዚህ በፊት ሰምቼዋለሁ፤ ትርጉሙን ግን አላስታውስም:: ተነስቼ መዝገበ ቃላት ተመለከትኩ:: አልተመዘገበም:: ቀጥሎም አንድ የጅኦግራፊ መጽሐፍ አንስቼ በትዕግሥት ስፈልግ አንድ ቦታ ላይ ተጠቅሶ አገኘሁት::*





> *ቃሉ የቀድሞ የዓለም ካርታ አዘጋጆች የሚጠቀሙበት ቃል ነው:: Gondwanaland የክፍለ-ዓለም ስም መሆኑን ተረዳሁ:: የGondwanaland ክፍለ ዓለም አፍሪካን ዋና ማዕከል አድርጎ የዐረብ ሰላጤን፣ ሕንድን፣ አውስትራሊያን፣ አንታርክቲክን፣ ደቡባዊ ምሥራቅ አሜሪካን፣ የሚያካትት አከላል ነው::*
>
> *ከዚህ ያገኘሁት መልዕክት ያው የአፍሪካ ጥሪዬን የሚያረጋግጥ ነው:: ምናልባትም የዐረብ ሰላጤ አገሮችን ይጨምር ይሆናል:: Gondwanaland በሚል ቃል መነገሩም ከራሴ አዕምሮ የመነጨ ሳይሆን ከመንፈስ ቅዱስ መሆኑን እግዚአብሔር ሊያረጋግጥልኝ ወዶ እንደሆነም ተረድቻለሁ::*
>
> *ጌታ ስሙ ይባረክ! እርሱ ወደ ፈቀደው ሥፍራ ሁሉ እንደሚያደርሰኝ አምናለሁ::›› (ዐውደ ዕለት መስከረም 13 ቀን 1988)*

እንግዲህ ለብዙዎች ግርታን የፈጠረዉና ሙሉ ጊዜአቸዉን ለመስጠት የቆረጡበት ዉሳኔ ምስጢሩ ይህ ነበር፡-

- ከቶም ቸል ሊሉት ላልተገባቸዉ መለኮታዊ ጥሪ ምላሽ ለመስጠት፣
- የነፍስ ደዌ የመፈወስን ያህል የወንጌል ባለ አደራነትን ሸክም ለመወጣት፣
- አንድ የዚህ ዓለም የሥልጣን ወንበር ከሚያካልለዉ ኃላፊነት እጅግ የሰፋ የወንጌል ማሣ ውስጥ ለመስማራት፤

## 12.3. የመድረሻው መነሻ

የዶ/ር ብርሃኑ የአገልግሎት ጥሪ ፕሮሞተር፤ ግልጥ መልክዓ ምድራዊ አድማሱም በአፍሪካ ደረጃ እንደሆነ ተረድተናል::

የአፍሪካው ጉዳይ በተገለጸላቸው ወቅት *‹‹ወደዚያ ደረጃ እንዴት እንደምደርስ መንገዱ ይታየኛል፤››* ብለውን ነበር። ምን ይሆን መንገዱ? ከመጨረሻው ብጀምር፦

- በAD-2000 movement በኩል ከዓለም አቀፍ *መድረክ መነሣት ይቀል ይሆን?*
- ወርልድቪዥን ዉስጥ *መጀመሪያም* የኢትዮጵያ፣ በኋላም የአፍሪካ የቦርድ አባል እንደ መሆናቸዉ መጠን፦ የብሔራዊና ዓለም አቀፍ የመንፈሣዊ ዘርፍ አማራጭ መነሻ ይሆናቸዉ ይሆንንን?
- በወቅቱ ተሳትፏቸው ደብዝዞ የነበረ ቢሆንም ኢወአሕን መጠቀም ይቻል ይሆን?
- በብርሃነ ወንጌል መጥመቃውያን ቤተ ክርስቲያን በቤተ እምነቱ ዋና ጽሐፈት ቤት በኩልስ?

በእውነቱ እንደ ባለ አዕምሮ ሲታሰብ በዶ/ር ብርሃኑ ፊት የተዘረጉት አማራጮች ተቆጥረው አያልቁም። እሳቸው ግን ወደ ላይ ከፍ ከፍ ለማለት ትሑትና ብቸኛው መንገድ ራስን ዝቅ ማድረግ እንደሆነ ያምናሉ። እናም ወደ ጥሪያቸውም ሆነ ወደ አገልግሎት ሥፍራቸው ለመድረስ መነሻቸው እንድትሆን የመረጡት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናቸውን ነበር።

ስለዚህም ነው፣ ቀደም ሲል እንደ ተገለጸው ራሳቸውን በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያናቸው ሽማግሌዎቻቸው እግር ስር የጣሉት - (እንደ በርናባስ)። ራሳቸውን ሲሰጡ ግን አጥቢያቸው ቀለብ እንድትሠፍርላቸው አልወደዱም። ለምን?

> *‹‹ቀደም ሲል በመንግሥት ቤት የሚከፈለኝን የደመወዝ ደረጃና ጥቅማጥቅሞች ሽማግሌዎች ማወቃቸው አይቀርም። ከዚህም የተነሣ ቀለብ ለመወሰን እንዲጨነቁብን አልወደድኩም። አጥቢያ ቤተ ክርስቲያኔ ላይ እንድከብድባትም አልፈለግኹም፤››*





ይላል የዐውደ ዕለት ማስታወሻቸው። በሌላ አገላለፅ ለቤተ ክርስቲያን የሰጡት *ሽክሙ የወረደለት ሌጣ ማንነታቸውን* ነው። ሆኖም አልከሠሩም። የኤልያስ አምላክ በተለያዩ ‹‹ቁራዎቹ›› ጓዳቸውን በበረከቱ *መሙላት* የጀመረው ቤተሰባቸዉ ‹‹በምን እንሁን›› አጣብቂኝ ውስጥ ገና ሳይወድቁ ነበር።

ሃሳባችን ሳንወደው እየተለጠጠ ከዋናው ርዕሰ ጉዳያችን እንዳያርቀን እንጂ እግዚአብሔር በበረከቱ እንዴት እንደ ጎበኛቸው በመደነቅ ከያዙት ማስታወሻ መጥቀሱ በተመሳሳይ የሕይወት ጉዞ ውስጥ ላሉት እምነት ይሆንላቸዋል። ለምሣሌ ያህል ጥቂቶቹን እነሆ፦

*‹‹በረከቱ መምጣት ጀምሯል፤. . .*

- *እህት -------- 4 ሊትር ዘይት አመጣች፣*
- *ወንድም -------- ብር 1000.00 ሰጠኝ፣*
- *አቶ -------- ጌታን አመሰግነናል ብሎ ብርሃን መጽሔት ገዛልኝ፣*
- *እህት -------- ለአልማዝ 30.00 ብር ሰጠቻት። (ዐውደ ዕለት 16/10/88 እስከ 11.5.89)*

አንባቢው ልብ ይበል። የመጣላቸውን በረከት በዘረዘሩበት ገፅ ላይ የሃያ ያህል ሰዎችና ተቋማት ስም ሰፍሮበታል። የስጦታው መጠን ከብር 3.00 (የመጽሔት ዋጋ) እስከ 900.00 ዶላር ይደርሳል። እስቲ ይታያችሁ! አንድ የፋኩሊቲ ዲን የነበረ ሰዉ ወገኖቹ ባቀረቡለት ዘይትና መጽሔት ስጦታ ተደስቶ ማስታወሻው ላይ ሲመዘግብ! ይህ ነው - የዶ/ር

ብርሃኑ ሕይወት፤ እምነትና ቁም ነገር፣ ምስጋናና ትህትና የተሞላ፤ እንዲሁም የእግዚአብሔርንና የሰዎችን ውለታ የማይረሣ ሕይወት፡፡ አንድ ተጨማሪ ምሣሌ መጥቀሱ አባባሉን የበለጠ ተጨባጭም ያደርገዋል፡፡

> *‹‹. . ከባለቤቴ ተለይቼ ወደ ሳሎን መጣሁ፡፡ ማለዳ የመጣልኝን አንድ ኤንቬሎፕ (ፖስታ) ከፍቼ ለማንበብ ቃጣኝ፡፡ ወዲያው ግን ራሴን አረምኩኝና አስቀድሜ የጌታዬን መልእክት ላንብብ ብዬ የመጽሐፍ ቅዱስ ዕለታዊ ንባቤን አነበብኩ፡፡ ከዚያም ኤንቬሎፖቹን ከፈትኩ፡፡*
>
> *ከእንግሊዝ አገር የተላኩ ደብዳቤዎች ነበሩ፡፡ አንዱ የሚያበረታታ አንድ ገፅ መልእክትና በውስጡ 150.00 የእንግሊዝ ፓውንድ ይዟል፡፡ ሁለተኛውን ደብዳቤ ስከፍተው የተጻፈ ነገር አልነበረውም፡፡ ነገር ግን በውስጡ 300.00 ፓውንድ ይዟል፡፡*
>
> *በጣም ልቤ ተነካ፤ ለባለቤቴም አሳየኋት፡፡ አለቀሰች፡፡ አብረን ተንበረከክን እያለቀስን ጌታን አመሰገንን፡፡. . .*
>
> *የኛ ድርሻ ይህ ነው፡፡. . . እኛ በሥፍራችን ከተገኘን አዎ! እርሱ ታማኝ ነው! . . .›› (ዐውደ ዕለት 9/11/88)*

ሳንወድ ከተወሰድንበት ‹‹የቀለብ›› ነገር እንመለስ፡፡ ዶ/ር ብርሃኑ ለብሔራዊና ዓለም አቀፍ የአገልግሎት ጥሪያቸውን ለመጀመር ከአጥቢያ ቤተ ክርስቲያናቸው መነሣት እንደ መረጡ ይታወሳል፡፡ ምርጫቸው ሁለት አብይት ነጥቦችን ያገናዘበ ሲሆን ሦስተኛዉ ግን እግዚአብሔር የብርሃነ ወንጌልን ስብራት ለመጠገን የተጠቀመበት መንገድ ነው ማለቱ ይቀላል፡፡





አንደኛ፡- ‹‹ሕይወት ያለበት አገልግሎት የሚካሄደው የክርስቶስ አካል በሆነችው አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ነው፤›› የሚል ጠንካራ እምነት ነበራቸው፡፡ እምነቶቻቸውም ጥልቅ በሆነ የእግዚአብሔር ቃል አስተምህሮ ላይ የተመሠረ ነው፡፡ ይህንንም በተለያዩ ጊዜያት፣ ለተለያዩ ቤተ ክርስቲያናትና አገልጋዮች አስተምረውታል፡፡ ሥልጠናም ሰጥታውበታል፡፡ መጻሕፍትና ማነዋሎችም አሳትመዋል፡፡

ሁለተኛ፡- የአፍሪካውያን የአገልግሎት መስክ እስኪደራጅና አስፈላጊ ቅድመ ሁኔታዎች እስኪሟሉ ድረስ የሙሉ ጊዜ አገልጋይነት በኩር አቅማቸውን ለአጥቢያ ቤተ ክርስቲያኔ መስጠት ይገባኛል የሚል እምነት ነበራቸው፡፡

ሦስተኛም፡- የአገልግሎት ራዕያቸውን በቤተ ክርስቲያናቸው ሥር ሆነው መተርጎም በመጀመራቸው ‹‹እየሩሣሌም በጭንቅ ዘመን ትሠራለች›› እንዲል ቅዱስ ቃሉ ብርሃነ ወንጌልም በአጣብቂኝ ዘመን እንድትሠራ እግዚአብሔር የተጠቀመበት መንገድ ሆነ፡፡

የቤተ እምነቱ ምክትል ዋና ጸሐፊ የሆኑት አቶ ከበደ ጎንፋ እንደሚሉት ዶ/ር ብርሃኑ ሙሉ ጊዜአቸዉን እንደሰጡ ቤተክርስቲያን ስታዉጅ ‹‹ፓስተር›› በሆነልን ብለዉ የተመኙ ብዙዎች ነበሩ፡፡ ቤተ ክርስቲያን ግን የአገልጋዩን ራእይ በማገናዘብና እንደ ራሷ ራእይ አድርጋ በመቀበል በዚህ የመጨረሻዉ ዘመን ለተሃድሶና ደቀ መዛሙርትን ማፍራት ይችሉ ዘንድ መላዉን አብያተ ክርስቲያናት የማነሣሣትና የማስታጠቅ ብሔራዊና ዓለም አቀፋዊ ተልዕኮ ላነገበዉ ‹‹ኤክሌሺያ ተነሺ አገልግሎት›› ለየቻቸዉ፡፡ ከቤተሰባቸዉና

በብርቱ የጸሎት ተጋድሎ *ከደጆናቸዉ* ሕብረት ጋር ሆነዉ ወደ ወንጌል ማሣዉ ተሰማሩ፤ ከአጥቢያቸዉም ጀመሩ::

የኤክሌሺያ ተነሺ አገልግሎት በአጥቢያና በቤተ እምነት ደረጃ የነበረዉ ቆይታ ባለ ራእዩ በመጨረሻዎቹ ጥቂት ዓመታት እንደ አለፉበት ዓይነት አታካችና ልብ የሚያዝል አልነበረም:: ስለሆነም *ኤክሌሺያ ተነሺ የወንጌል አገልግሎት* ሰዎች በሚረዱት መንገድ ተገልጦ የብርሃነ ወንጌልን ድምበር ተሻግሮ አንድ ዓመት ባልሞላ ጊዜ ወደ ሌሎች አብያተክርስቲያናትና ወደ ዓለም አቀፉ መድረክ ዘለቀ:: በመልክዓ ምድር ደረጃ ከምዕራብ ወለጋ እስከ ጅጅጋ ከሞያሌ/በረና እስከ መቀሌ ማካለል ጀመረ:: ከዚሁ ጎን ለጎን በአንድ ሰሞን ተነቅለው ከነበሩበት ብሔራዊና ዓለም አቀፋዊ የአገልግሎት መንበሮቻቸው ቀስ በቀስ ተመልሰው ተተከሉ:: በእርግጥ ተፈላጊነታቸው አንሠራራ::

ከሚደርሷቸዉ የአገልግሎት ጥሪዎች መካከል አንዳንዶቹ በሰዉ አእምሮ ሲመዘኑ በይዘትም በቅርፅም ከቀድሞዎቹ በጣም የተለዩ፣ የላቁም ይመስላሉ:: ለዶ/ር ብርሃኑ ግን ይህ ምንም ትርጉም የለዉም:: ከተጠሩበትና ቤተ ክርስቲያናቸዉ ከለየችዉ የራዕያቸው አስኳል ከሆነው ‹‹ኤክሌሺያ ተነሺ›› የወንጌል አገልግሎት ጋር የሚጣጣም ካልሆነ ገሸሽ ማለቱን ይመርጣሉ:: ቀድሞዉንም ‹‹አንደኛ ከመሆን እውነትን ማገልገል ይበልጣል›› ብለዉ አልነበር!

ለመሆኑ ኤክሌሺያ ተነሺ የወንጌል የአገልግሎት ራዕይ፣ ዓላማና ግብ ምንድነው? ዳርቻውስ የት ድረስ ይሆን?





# 13. ኤክሌሺያ ተነሺ:-

*‹‹ለክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን የተሰጠ ራዕይ››*

## *13.1. አነሣሥ እና መስፋፋት*

*የኤክሌሺያ ተነሺ አገልግሎት* ራዕይ በዶ/ር ብርሃኑ ልቦና ዉስጥ ሲጠነሰስ ቤተ ክርስቲያን፦ ከነፃነት *ማግሥት* ጀምሮ በተከፈቱላት ምቹ ዕድል በመጠቀም በርካቶች የክርስቶስ ኢየሱስ የማዳኑ ዜና እና የእግዚብሔር ኃይል የሆነውን ወንጌል እንዲሰሙ በማድረግ ወደ ጌታ ቤት እንዲጨመሩ የአደረገችበት ወቅት ነበር:: በየአካባቢው በብዛት የተከፈቱት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት ለዚህ እውነት ቋሚ ምስክሮች ናቸው::

ሆኖም እንደ ተከፈተው ምቹ የአገልግሎት በር መጠን የወንጌሉን አዝመራ የመሰብሰቡና አዝመራውም ከተሰበሰበ በኋላ ሊከናወን የተገባው ‹በጠንካራ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እዉነት ያመኑትን ደቀ መዛሙርት የማድረግ› ሥራ የሚገባዉን ያህል ተሠርቷል ለማለት የማያስደፍሩ አስደንጋጭ ክስተቶች ጎን ለጎን የተገለጡበት ወቅት ነበር:: በምዕራፍ አምስት በጥቅሉ እንዲሁም በአሥረኛዉ ምዕራፍ ላይ በአንደምታ መልክ እንደ ተብራራዉ እነዚያ ክስተቶች *‹‹የነፃነት ማግሥት ግርሻ››* ሆኑባትና ቤተ ክርስቲያን በነዉጥና በዉዥንብር ነፋስ ዉስጥ በመንገዋለል አቅሟን ማባከን ዕድል ፈንታዋ ሆነባት:: ምዕመኑም በግልም ሆነ በቡድን ደረጃ የውዥንብሩ ሰለባ ሆነ:: አንዳንዱም ራሳቸዉ ባለ ራእዩ ናቸዉ:: በደሙ የዋጀዉን ሕዝቡን ፊፅም የማይረሳዉ

ጌታ እግዚአብሔር ዐውሎዉን አሳለፈዉ። ቤተ ክርስቲያን ግን በኃይለኛ እንቅልፍ ውስጥ ነበረች። ‹‹*ተነሺ*›› መባል ነበረባት።

በዶ/ር ብርሃኑ እምነት የዉዥንብሩም ሆነ የእንቅልፏ ምክንያት ቅዱስ መጽሐፍ ‹‹የሚለውን ሁሉ›› በተግባር የማክናወን ብቃቷን በአንድ ወይም በሌላ መንገድ ስለ ተዘረፈች ነው። ዋነኛው ጉድለቷም አብይ ተልዕኮዋ የሆነዉን የምሥራቹን ቃል መስበክና ደቀ መዛሙርት የማድረግ ኃላፊነቷን መዘንጋቷ ወይም ትኩረቷን ወደ ሌሎች ተለጣፊ ጉዳዮች በማዞሯ ነው። ይንንም በኤክሌሺያ መግለጫ ሰነድ ላይ ፊት ለፊት ብለዉታል፡-

*በዘመናችን በወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ አሳሳቢ አዝማሚያዎች እያየን ነው።*

- *የምዕመናንም ሆነ የአገልጋዮች የሕይወት ቅድስና በመጉደሉ በዓለማውያን ፊት እንኳን የሚያሳፍሩን ድርጊቶች ይሰማሉ፤*
- *የአምልኮ ዘይቤአችን እንግዶችን የሚያሸሽ ሆኗል፤*
- *ወንጌልን የሚመሰክሩ አማኞች እጅግ ከማነሳቸው የተነሳ በአምልኮ ስብሰባዎች ጌታን የሚቀበሉ በጣም ጥቂቶች ናቸው፤*
- *የጸጋ ስጦታዎች አጠቃቀም ስሜታዊና ከቃሉ ውጪ ከመሆኑ የተነሳ ለበረከት ከመሆኑ ይልቅ ግራ ለመጋባት ለቅሬታ ስጦታዎችንም ለማቃለል ምክንያት እየሆነ ነው፤*
- *በጌታ ቃል ካለመመሥረት የተነሳ ብዙዎች በቀላሉ በስህተት ትምህርቶች ይወሰዳሉ፤*
- *ለግል ጥቅም ሲሉ የሙሉ ጊዜ አገልጋዮች ቤተ ክርስቲያንን መክፈል ወይም ማፍረስ አይከብዳቸውም፤*
- *እግዚአብሔርን መፍራት እየጠፋ በቤተክርስቲያን ውስጥ የሚፈጠሩ ግጭቶች በዓለም ፍርድ ቤቶችና በዜና ማሰራጫዎች እየቀረቡ መሳለቂያ መሆን ጀምረናል።*





እነዚህን የመሳሰሉ በየቤተ ክርስቲያኑ የምናያቸው ድክመቶች ምክንያት ምን እንደሆነ ብንመረምር በአዲስ ኪዳን ትምህርት መሠረት ለጌታ የተገባ ሕይወት ያላቸው ደቀመዛሙርት በብዛት አለመኖራቸው መሆኑን እንረዳለን። ለዚህም መሠረታዊ የሆነው ምክንያት የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አገልግሎት አደረጃጀትና አፈጻጸም የአዲስ ኪዳንን ፈለግ ሙሉ በሙሉ አለመከተሉ ይሆናል ብለን ማመን እንገደዳለን። ስለሆነም ተሃድሶ ማድረግና እዉነተኛ ደቀ መዛሙርትን ወደ ማፍራቱ የወንጌል ሥራ ልንመለስ ይገባናል ነዉ የባለራዕዩ ፅኑ እምነት። ደግሞም ይላሉ ዶ/ር ብርሃኑ፡-

*ቤተ ክርስቲያን ደቀ መዛሙርት አላፈራችም ማለት፡-*

- *መሪ የላትም - አይኖራትምም፤*
- አገልጋይ የላትም፤ ባለአደራም የሚሆን የላትም፤ አይኖራትምም፤
- የጸጋ ስጦታዎች በውስጥዋ በሙላት አይገለጥም፤ ...
- ስለዚህም ዓለምን ለክርስቶስ ለመማረክና የእግዜአብሔርን መንግሥት መምጣት መናፈቅ አትችልም።
- ስለሆነም በዚህ የዘመን ማሚጠጫ ቤተ ክርስቲያን በድል የምትገሠግሥ የክርስቶስ ሠራዊት አካል ለመሆን ትችል ዘንድ ልትነቃ፤ ልትታጠቅም ይገባታል። ኤክሌሺያ ተነሺ!!! ...

እዉነትም ቆም ብሎ ላሰበዉ የኤክሌሺያ ተነሺ ራእይ እንግዳ መገለጥ ወይም ትምህርት አይደለም። እግዚአብሔር በቃሉ ‹‹... የገሃነም ደጆች አይችሏትም›› ’ሲል ወደ ሰጣት

ዘለዓለማዊ ዋስትና ዉስጥ ለመገኘት በሚያበቃት ተሃድሶ ለመታደስ ማልዳ ትነሣ ዘንድ የጊዜዉ ቀስቃሽ ተልዕኮ መሆኑ በአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ የተመሰከረለት ዉሎ ሳያድር ካስገኘዉ ፍሬ ነዉ ይላሉ - አቶ እሸቴ በለጠ፡፡

አንድ የባለአደራዉ ቦርድ አባል የሆኑ አገልጋይ ደግሞ የኤክሌሺያ ተነሺ አገልግሎት አጀማመርና አስተዳደግ በተክል ምሣሌ ሲገለፅ ይችላል ይላሉ፡፡ እንደ ዉስጠኛ ሰዉ ሆኜ ስመረምረዉ የችግኙን ዘር ባለአደራ አድርጎ በቆጠረው በዶ/ር ብርሃኑ ልቡና ውስጥ የአበቀለው ጌታ መንፈስ ቅዱስ እንደሆነ እረዳለሁ፤ ሲሉም አክሉ፡፡

እናም፡- ባለአደራው ከልጅነት እስከ ጉልምስና ድረስ ከአሳለፉት የሕይወት ልምምድ፣ የአገልግሎት ይዘት፣ ብዛትና ቅርፅ፣ ... ትጋት፣ የሕይወት ንጽህና እና በመንፈስ ቅዱስ ምሪት... በልፅጎ፣ ተከርክሞ ልቡናቸዉን ወርሶ ለዓመታት ያህል ከረመ፡፡ የእግዚአብሔርን ጥሪ በመታዘዝ ሙሉ ጊዜያቸዉን ከመስጠት ጎን ለጎን ኤክሌሺያ ተነሺ አገልግሎትን ሚያዚያ 6 ቀን 1988 ዓ.ም በእምነት መሰረቱ፡፡ እግዚአብሔር አላሳፈራቸዉም፤ አገልግሎቱን በጸሎት፣ በሥራ፣ በምክር፣ እንዲሁም በገንዘብ የሚደግፉ ሰዎችን አስነሳላቸዉ፡፡ አገልግሎቱ ለመጀመሪያ ጊዜ በተግባር የተፈተሸው በ1989 ሦስተኛ ሩብ ዓመት በብርሃን ወንጌል ቤተ ክርስቲያናት ዙሪያ ነው፡፡ በሕይወት ለዋጭ አቀራረቡ በአጭር ጊዜ እዉቅናን አተረፈ፡፡ ሰኔ ወር 1989 አራተኛዉ ሩብ ዓመት መጨረሻ አንስቶም ወደ ቅርብ ሩቅ ክልሎች ለሚገኙ ቤተ እምነቶች ማካፈል ተጀመረ፡፡





ራዕይ የማካፈሉና የተግባር ፍተሻ እንቅስቃሴአቸው የእግዚአብሔር ርዳታ ታክለበትና ‹‹ከተነቀሉባቸው አገልግሎቶች - እንደገና መተከል›› ጋር ተገጣጠመ፤ ጊዜዉም 1990 ዓ.ም አጋማሽ ነበር፡፡ ከዚህም የተነሣ ለአገልግሎት እየተጋበዙ ወደ ውጪ አገሮች የሚመላለሱበት አጋጣሚ በረከተ፡፡ አጋጣሚውንም በመጠቀም ራዕዩን ከባህር ማዶ ለሚገኙ ቤተ ክርስቲያናት ማካፈልና ትምህርቱንም ማስተላለፍ ቻሉ፡፡

ከመጀመሪያዎቹ 3 ዓመታት ስኬታማ የአገልግሎት እቅስቃሴ በኃላ እናት ቤተ ክርስቲያንን ሙሉሴል ተቀብላ ኮሚሽን እንድታደርገዉ ጠየቁ፡፡ እናት ቤተ ክርስቲያን ደግሞ ***የኤክሌሺያ ተነሺ አገልግሎት*** በአንድ አጥቢያ፣ ቤተ እምነት ወይም ዲኖሚኔሽን ሳይወስን የሁሉም አብያተ ክርስቲያናትና መንፈሳዊ ድርጅቶች ተልእኮ አጋዥ አገልግሎት እንዲሆን ለየችዉ፡፡ የመለየቱ ሥነ ሥርዓት ሰኔ 13 ቀን 1991 ዓ.ም እንዲፈጸም አደረገች፡፡

ከዚያ በኋላ አገልግሎቱ ለእናት ቤተ ክርስቲያንን ተጠያቂ ሆኖ በሐዋርያት ሥራ13፡ 2-3 መንፈስ መሠረት መንፈስ ቅዱስ በሚመራዉ መንገድ ሁሉ መንቀሳቀሱን ቀጠለ፡፡ አሁን ከአሥር ዓመት በኋላ የኤክሌሺያ ተነሺ አገልግሎት ስም ከኢትዮጵያ ናይጀሪያ ኬኒያ ዩጋንዳ ደቡብ አፍሪካን ጨምሮ በብዙ የአፍሪካ አገሮች፣ በአሜሪካና በአዉሮፓ ዙሪያ በተለይም በኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ሁሉ እንግዳ ስም አይደለም፡፡

## 3.2. የአገልግሎት ስልትና ጥረት


የራእዩ ምንጭ ‹‹ውኃ ' ባሕርን እንደሚከድን ምድር እግዚአብሔርን በማወቅ ትሞላለችና›› የሚለዉ ከነብዩ ኢሳያስ የተወሰደዉ ትንቢታዊ ቃል ኪዳን እንደሆነ ተደጋግሞ ተገልጧል (ኢሳ 11፡ 9)። ከዚህም በመነሣት፡- ውኃ ባህርን እንደሚከድን ምድር እግዚአብሔርን በማወቅ ልትሞላ የምትችለዉ አብያተ ክርስቲያናት መንፈሳዊ ተሃድሶ ሲያደርጉ፣ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ወንጌልን ሲያሰራጩና የዳኑትን በደቀ መዝሙርነት ሕይወት ሲሳያድጉ ብቻ መሆኑን አገልግሎቱ ያምናል።

ራእዩን ለማሳካትም ላለፉት አሥር ዓመታት ሦስት ተመጋጋቢ ስልቶችን በመጠቀም ቤተ ክርስቲያንና አገልጋዮቿን በመድረስ ስኬታማ ጥረት አድርጓል። የአራተኛዉ ስልት በሚያስጎመኘ ጅማሬ ላይ ይገኛል። ተራ በተራ እንያቸዉ።

*አንደኛዉ፡-* ሰብዓዊ /ሰዉ ለሰዉ/ የተግባቦት ዘዴ *(Inter Personal Communication) አገልግሎት* ስልት ዉስጥ ሊካተት ይችላል። ይህም ለሞነኛ የመድረክ አገልግሎትን ሳይጨምር መጋቢዎችን፣ ሽማግሌዎችን፣ ነባር አባላትን እና ሌሎች ቁልፍ አባላትን ማሰልጠን ላይ ያነጣጠረ ነዉ። ሥልጠናዉ በዉይይትና በሌሎችም ‹አሳታፊ› ተብለዉ በሚታወቁ ዘዴዎች ዐዉደ ጥናት ማዘጋጀት፣ በጥናት ላይ የተደገፉ ጠቋሚ ሪፖርቶችን ወይም መረጃዎችን እንደ አስፈላጊነቱ ማካፈልና የመሳሰሉትን ያጠቃልላል።








*ዶ/ር ብርሀኑ በፈረስና በበቅሎ ጭምር እየተጓዙ ያገለግሉ ነበር*

ይህ ስልት የመጀመሪያዎቹ ዓመታት እንቅስቃሴ ዋነኛ ስልት ነበር። አገልጋዮቹ በመኪና፣ በበቅሎ፣ በእግር፣ በአይሮፕላን በመዘዋወር በሺህ የሚቆጠሩ ሥልጠናዎችና የመድረክ አገልግሎቶችን አበረከቱ።



በፎቶ ግራፉ ላይ እንደ ሚታየዉ የመኪና መገልበጥና



ዶ/ር ብርሀኑ በፈረስና በበቅሎ ጭምር እየተጓጓዙ ያገለግ
ነበር

ሎት የመጀመሪያዎቹ ዓመታት እንቅስቃሴ ዋ
፣ አገልጋዮቹ በመኪና፣ በበቅሎ፣ በእግር፣ በአ
ዋወር በሺህ የሚቆጠሩ ሥልጠናዎችና
ግሎቶችን አበረከቱ።



ግራሩ ላይ እንደ ሚታየው የመኪና መ

ከመሳሰሉት አደጋዎችም ከተአምር በሚቆጠር ሁኔታ አምልጠዋል።

**ጉርሻ**

*አገር ዉስጥ ሆኖ ከአዲስ አበባ 500 ኪ.ሜ ርቀት በላይ ከአልሆነ በስተቀር አይሮፕላን ለምን እንደማይጠቀሙ ዶ/ር አታላይ ይናገራሉ*

*በ1990ዎቹ መጀመሪያ ዶ./ር ብርሃኑ ጅማ ላይ በተዘጋጀ የኤክሌሺያ ተነሺ ሥልጠና ላይ እንዲያገግሉ ዶ/ር አታላይ ዓለምን ጋበዙአቸው። (ዶ/ር አታላይ የኤክሌሺያ ተነሺ የቦርድ ሊቀመንበር መሆናቸውን ልብ ይበሉ።) በጉዞው ዋዜማ ዶ/ር ብርሃኑ ደወሉና መርካቶ አውቶብስ ተራ በማለዳ እንዲደርሱ አስታወቋቸው። ዶ/ር አታላይ ደንገጥ አሉ - ለምን አውቶብስ ተራ? በማለት።*

*በቀጠሮአቸው ተገናኙ። ተጋፍተው ትኬት ገዙ። የደረሳቸው ወንበር ከበስተኋላ የመጨረሻው ነበር። ጉዞ ጀመሩ። መኪናው ከከተማ ወጣ እንዳለ ዶ/ር ብርሃኑ የወረቀት ቦርሳቸውን ከፈቱ! ማስታወሻ እያያዙ ማንበብና ማጥናት ቀጠሉ። ዶ/ር አታላይ በፅሞና እየታዘቧቸውና የአውቶብሱ መንገጫገጭ የፈጠረባቸውን «የቁም - የቅምጥ›› ስቃይ ጋር ታገሱ። ትክክለኛ ሰዓት በመሰላቸው ጊዜ ግን አንድ ጥያቄ ሰነዘሩ።*

*ዶ/ር አታላይ፡- ምነው ብርሃኑ የአውሮፕላን ትኬት አጣህ እንዴ?.ማለት ቀደም ብለህ ቦታ አላስያዝክም ነበር?*

*ዶ/ር ብርሃኑ፡- አይ! አይደለም።*

*ዶ/ር አታላይ፡- ታዲያ ካልሆነ እንዲህ መሰቃየት ነበረብን?*

*ዶ/ር ብርሃኑ፡- ለወንጌል ሥራ አገልግሎት ሙሉ ጊዜዬን ሰጥቼ ስወጣ ለጌታ ቃል ገብቻለው።ዶ/ር አታላይ፡- ፡- ምን ዓይነት ቃል ኪዳን?*

*ዶ/ር ብርሃኑ፡- ከ500 ኪ.ሜትር በላይ የሆነ መንገድ ካልተጓዝኩ በስተቀር በአውሮፕላን ላለመብረር ቃል ገብቻለሁ። ይህም ለገዛ ምቾቴ ብዬ ጌታ ለሥራው የሰጠኝን ገንዘብ ላላማባክን ብዬ ነው።*





በመጀመሪያዎቹ ሰባት ዓመታት ብቻ በአገር ዉስጥ፡-

- በ247 ከተሞች ተዘዋውረዉ
- 580 አብያተ ክርስቲያናትን ደርሰዉ
- 18,115 መሪ አገልጋዮችን (መጋቢዎች፣ መሪዎች፣ ታሳቢ አገልጋዮች ቁልፍ አባላትና ሌሎችም) አሠልጥነዋል።

በዉጭ ሃገራት ደግሞ፡-

- በ10 አገራትና በ27 ከተሞች በመዘዋወር
- 86 አብያተ ክርስቲያናትን በመድረስ
- 2725 ሰዎችን አሠልጥነዋል።

*ሁለተኛ፡-*

**ጢራኖስ የደቀ መዝሙር ትምህርት ቤትን መጠቀም።** የጢራኖስ ራእይ የተወለደዉ በጣት የሚቆጠሩት ኤክሌሺያ ተነሺ አገልጋዮች በመላዉ ኢትዮጵያ የቆዳ ስፋት የተበተኑትን አብያተ ክርስቲያናት በአካል ደርሰዉ ለማገልገልና ለማንቀሳቀስ የማቱሳላ ዕድሜ ቢሰጣቸዉም እንኳ ከአቅማቸዉ በላይ እንደሚሆንባቸዉ ተገንዝበዉ በእግዚአብሔር ፊት ከቀረቡ በኋላ ይመስላል።

ትምህርት ቤቱ ተንቀሳቃሽ ከመሆኑም በተጨማሪ ሠልጣኞቹ ልባቸዉን ከሚሰርቁቸዉ የኑሮም ሆነ የአገልግሎት ጉዳዮች ርቀዉ፣ አርፈዉ ቃሉን እንዲማሩ፣ እርስ በርሳቸዉ ሕብረት እንዲያደርጉና የቀሰሙትን ደቀ መዝሙራዊ ሕይወት እንዲለማመዱ በሚያደርግ ረቀቅ ያለ ስልት ነዉ።



የውጭ አገር ሠልጣኞች

አቶ እሸቱ በለጠ እንዲህ ይመሰክሩለታል፡-

*‹‹ዶ/ር ብርሃኑ ጢራኖስ የደቀ መዝሙር ትምህርት ቤትን ሲጠነስስ በልቡ ገብቶ የነበረውን መሻትና ምሪት፣ ከተረዱለትና ፍሬዉንም ከሚመሰክሩለት ሰዎች መካከል አንዱ ነኝ ብዬ አምናለሁ፡፡*

*ቅዱሳን ለትምህርት ካላቸዉ ናፍቆት የተነሣ ልባቸው በደጅ ባለው ሥራ ቆም፣ ሃሳባቸዉ እየሮጠ ግን ያለ ቅንጣት ግብዓት ክፍል ውስጥ በአካል ብቻ ተቀምጠው ይከርማሉ፡፡ ለወጉ ያህል ‹ጨርሼ ተመርቄ ወጣሁ›፣ ማለታቸዉም እንደ ማይቀር ይታወቃል፡፡*

*ዶ/ር ብርሃኑ ግን ከመደበኛዉ የአሠለጣጠን ልማድ ባሻገር በእዉነት ጥማቱ ያላቸዉን ከተለያዩ ቦታዎችና ቤተ እምነቶች አንድ ቦታ አሰባስቦ፣ በአካልም በመንፈስም ዕርፍ ብለው ለአንድ ወር በአንድ የእግዚአብሔር መንግሥት አጀንዳ ዙሪያ ተቀምጣው፡- ከመምህራን እውቀትን፣ እርስ በርስ የወንድማማች ሕብረት ደግሞ ሕይወትን የሚካፈሉበትና ደቀ*





*መዝሙራዊ ለዉጥ በሕይወታቸዉ እንዲገለጥ የሚያግዘዉን የጢራኖስ የደቀ መዝሙር ትምህርት ቤት ጠነሰሰ፡፡*

*የሥልጠና ዘይቤዉ ከፊደል ባለፈ ከደቀ መዝሙር ሕይወት ትምህርት የሚቀስሙበት ዓይነት ነዉ፡፡ አስገዳጅ የሆነ ልዩ ምክንያት ካልተፈጠረ በቀር ማናቸዉም፣ የትም ሳይንቀሳቀሱ በአንድ ወር ቆይታ የቀሰሙትን ሁሉ ወደ የመጡበት ሲመለሱ በእዉቀትና በመንፈስ ሆነዉ እንዴት እንደሚያባዙት ማስታጠቅም አንዱ የሥልጠናዉ አካል ነዉ፡፡ የተገኘዉም ዉጤት እጅግ አስደሳች ነዉ፡፡››*

*ሦስተኛ፡-*

**የሕትመት ዉጤቶችን መጠቀም ነዉ፡-**




ዶ/ር ብርሃኑ የኤክሌሺያ ተነሺ አገልግሎትን ሲጀምሩ በዓመት ቢያንስ አንድ መጽሐፍ የማዘጋጀትና የማሳተም እቅድ ነበራቸው፡፡ እስከ 2ሺህ ዓ.ም ድረስ በጠቅላላዉ ከአሥር በላይ የሕትመት ዉጤቶች በአገልግሎቱና በዶ/ር ብርሃኑ ስም መታተማቸዉ ስኬታማነትን ለመመስከር በራሳቸዉ በቂ ናቸዉ፡፡

የሕትመቱ ውጤቶች በዋነኝነት ሥልጠናውን ለማገዝ የተዘጋጁ ሲሆን ከፊሎቹ ደግሞ አስተምህሯቸውን ቀጥተኛ በሆነ መንገድ ለአንባቢ ለማስተላለፍ የታለሙ ናቸዉ፡፡ በሠልጣኞችና በአንባቢያን እጅ ከገቡት መካከል፡-

- በዘመኑ መጨረሻ በድል የምትገሰግሰው ቤተ ክርስቲያን፣ 1989 (ሦስት ጊዜ የታተመ)፤

*ሦስተኛ:-*

## የሕትመት ዉጤቶችን መጠቀም ነዉ፡




ዶ/ር ብርሃ
አገልግሎትን
አንድ መጽሐ
እቅድ ነበራቸ
በጠቅላላዉ ከ
ዉጤቶች በአ
ስም መታ
ለመመስከር በ



የውጭ አገር ሠልጣኞች

- ከግብዝነት ክርስቶስን ወደ መምሰል፣ ቅጽ 1 1996፣ እና ቅጽ 2 1999፤
- የእግዚአብሔር ሙሉ ምክር (2000)፣
- ልጅነት 1996፣(አራት ጊዜ የታተመ)፣
- የመቅደሱ ሕግ፣ 1998፣
- መንፈሣዊ ውጊያ፣ 1998 (ሁለት ጊዜ የታተመ)፣
- ባጠቃቀም ብልሹነት የምንቸገርባቸው የጸጋ ስጦታዎች፣

ከዚህ በላይ የተጠቀሱት መጻሕፍት አብዛኛዎቹ ራሳቸውን የቻሉ የሥልጠና መምሪያ (ማኑዋል) መጻሕፍት ተዘጋጅቶላቸዋል፤ ጥቂቶቹ ደግሞ በአንድ ጥራዝ በተካተተ መምሪያ ይታገዛሉ።

*አራት፡-*

**ስድኾች የምሥራች አገልግሎት**

*ኢክሌሺያ ለድኾች የምሥራች* አገልግሎት ራእይ ከ1987 ዓ.ም አንስቶ በሲስተር አልማዝ ልቡና ለረዥም ጊዜ ሲብላላ የቆየና ነሐሴ 28 ቀን 1998 ዓ.ም ‹የተገባቸዉ ሰዎች› በተገኙበት ጉባዔ በምክር ደረጃ ይፋ የተደረገ ራእይ ነዉ። ተልዕኮዎቹ የሚከተሉት ናቸዉ፡-

- ፍቅርን ማዕከላዊ ባደረገ መልኩ ለማኞችንና ድኾችን በተለያዩ ሙያዎች በማሠልጠንና በማቋቋም ራስን ማስቻል፤
- በሚፈጠር የፍቅር ድባብ ውስጥ የምሥራቹን ወንጌል በጥበብ ለመመስከር ድኾች የዘላለም ሕይወት ተስፋ ባለቤት እንዲሆኑ ማድረግ፤





- ድኅነትን ያገኙት ክርስቶስን የሚመስሉ ደቀ መዛሙርት ሆነው የሚያድጉበትን ሞዴል ቤተ ክርስቲያን በማቋቋም የእግዚአብሔርን መንግሥት ለማስፋትና የክርስቶስን ሙሽሪት ለማዘጋጀት፤

ተግባራዊ መነሻዉና መድረሻዉ ደግሞ፡-

- አቅምና ጤናቸው የፈቀደውን ያህል ባሉት ሙያዎች ሁሉ እየሠለጠኑ ይሰማራሉ፤ ግብርና በየዘርፉ፣ የቴክኒክ ሥራዎች፣ ዕደ ጥበባት፣ ባልትና፣ በከተማ ቆሻሻ ማዳበሪያ ማምረት ወ.ዘ.ተ፤
- መዋዕለ ሕፃናትና አንደኛ ደረጃ ት/ቤት እንዲሁም ክሊኒክ በማዕከሉ ይኖራሉ፤ መምህራኑ ከችግረኞቹ መካከል የተማሩት ይሆናሉ፤
- የሚገኘው ምርት ከችግረኞቹ ተርፎ ለገበያ ይቀርባል
- ለ3 ዓመታት የሠለጠኑ ችግረኞች ከማዕከሉ ወጥተው በመኖሪያ መንደር ውስጥ እየኖሩ በተመላላሽት ተቀጣሪ ሆነው የልማቱን ሥራ ይሠራሉ፤
- የመጀመሪያው የልማት ማዕከል በሚገባ ሲደራጅ ተመሳሳይ ማዕከል በሌላ ቦታ ይቋቋማል፤
- መንፈሣዊ አገልግሎት በጥሩ ሁኔታ በማዕከሉ ይካሄዳል። የሚቀጣጠል የክርስትና ሕይወት በሰዎች ላይ ይታያል። ከመካከላቸው አንዳንዶቹ በወንጌል ሥራ ይሠለጥናሉ። የሠለጠኑት ለሌሎች ድኾች ወንጌል ይሰብካሉ፤
- በአካባቢ ቤተ ክርስቲያን ትተከላለች፤ ያመኑ ችግረኞችን በእውነተኛ ደቀ መዝሙርነት ለማሳደግ መሣሪያ ትሆናለች፤

ሥራው እየሰፋ ሲሄድ ሞዴል ቤተ ክርስቲያኖችም ይበረክቱና፣ ለአብያተ ክርስቲያናት የምናቀርባቸውን ልዩ ልዩ ሥልጠናዎች በምሳሌነት በመደገፍ የቤተ ክርስቲያን ተሃድሶ ይቀጣጠላል፤ የእግዚአብሔር መንግሥት በጤናማ መልኩ ይሰፋል፣ የክርስቶስ ሙሽሪትም ትዘጋጃለች።

ራእዩን ወደ ተግባር ለመለወጥ ከተጣሉለት መሠረቶች መካከል ፕሮጀክት መንደፍና በሚመለከተዉ ባለሥልጣን መስሪያ ቤት ሕጋዊ እውቅና ማሰጠት እንዲሁም የሥራ ፈቃድ ማግኘትና የፕሮጀክት ስምምነት መፈራረም ዋና ዋናዎቹ ናቸዉ።

ዶ/ር ብርሃኑና ሲስተር አልማዝ አገልግሎቱን በሕግ ሲያስመዘግቡ ስሙን «ኤክሌሺያ ለድኾች የምሥራች» እንዲባል መወሰናቸዉ «የኤክሌሺያ ተነሺ» አጋዥ እንዲሆን የአሰቡበት ይመስላል። ምክንያቱም ሰው በእንጀራ ብቻ አይኖርም፤ የሚለው አባባል የማይነቃነቅ እውነት ቢሆንም የራበው፣ የጠማው፣ ያለ ጧሪ የተጣለው፣ በደዌ የአልጋ ቁራኛ የሆነዉ የምስራቹን ቃል ለመስማት ሰምቶም ለመለወጥ አቅም አይኖረውምና!!

ስለሆነም ቤተ ክርስቲያን የሰውን ሁለንተና ማለትም አካሉን፣ አእምሮዉን፣ መንፈሱን፣ ነፍሱን ማገልገል ይጠበቅባታል። ለዚህም «ሙሉ ኃይል ለብሰሽ ተነሺ!» መባል ይገባታል። እንደ ኢትዮጵያ ላለች አብዛኛው ሕዝቧ ከድህነት ወለል በታች በሚኖሩባት አገር ደግሞ «የገዛ እንጀራን ለድሃ ሳይቆርሱ» በቃል ብቻ ለማገልገል መሞከር በራሱ የወንጌሉን ቃል ጎዶሎ ማድረግ ነውና!! ***የኤክሌሺያ ለድኾች የምሥራች***






እና ***የኤክሌሺያ ተነሺ*** አገልግሎቶችን አስመልክቶ የተዘጋጁት የተለያዩ ሰነዶች የሚመሰክሩት ይህንኑ ነበር።


የዚችን አገር መልካምነትን ለሚናፍቁ ሁሉ የሚያስጎመዥ ራእይ ነዉ። ዳሩ ግን የሁለቱ አገልግሎቶች የተመጋጋቢነት ቅንብር በሙላት የሚገለጠዉ የራእይ ቅብብሎሹ ሲሰምር ገና ወደ ፊት ነዉ፤ በእግዚአብሔር ርዳታ።

## 13.3. አስተምህሮ

ከማንኛዉም ሰዉ ወይም ተቋም ድርጊት ጀርባ በሕይወት ሂደት የተቋጠረ እዉነት፣ እምነት፣ አመለካከት፣ ወዘተ አለ። የዶ/ር ብርሃኑንም ሆነ የኤክሌሺያን አስተምህሮ ለመረዳት የሥልጠና ርዕሶችንና የሕትመት ዉጤቶቹን በፅሞና መመርመር አስፈላጊ ይሆናል። የመጻሕፍቱ ዝርዝር ከሞላ ጎደል ከላይ ተጠቅሰዋል። ዋና ዋና የሥልጠና ርዕሶቹ ደግሞ የሚከተሉት ናቸዉ።

- በዘመኑ መጨረሻ በድል የምትገሠግሠው ቤተ ክርስቲያን፣
- ልጅነት፣
- የቤተ ክርስቲያን አመራር፣
- ጤናማ ቤተ ክርስቲያን መትከል፣
- መንፈሣዊ ውጊያ፣
- የጸጋ ስጦታዎችና አጠቃቀማቸዉ፤




ወደ አዲስ ኪዳን እንመለስ

የሥልጠናዎቹንም ሆነ የመጻሕፍቱን ይዘት ረጋ ብሎ ስገመግመ ሰዉ ከተያያዥነታቸዉም በላይ ሁሉም በአንድ ቀስት ወደ አንድ ዒላማ ማነጣጠራቸዉን ይገነዘባል። ይኼዉም በዘመኑ መጨረሻ በድል የምትገሠግሠዉ ቤተ ክርስቲያን ምን መሆን እንደሚገባት በዉል እማስጨበጡ ላይ ማተኮራቸዉ ነዉ።

እነዚህን አስተምህሮዎች ለመቅረፅ ከሥራቸውና ከአገልግሎታቸው ጎን ለጎን በተልዕኮ ፕሮግራም በዲግሪ ደረጃ የወሰዷቸው የሥነ መለኮት ትምህርት እንደጠቀማቸው አያጠራጥርም።


በነገራችን ላይ ከስኮትላንድ መልስ ከሥራቸዉ ጎን ለጎን በዉስጥ ደዌ ሕክምና ሌላ የስፔሺያላይዜሽን ዲግሪ እንደ ወሰዱ ያስታውሷል።

## በዘመኑ መጨረሻ በድል የምትገሠግሠው ቤተ ክርስቲያን

‹‹ዶ/ር ብርሃኑ ‹በዘመኑ መጨረሻ በድል የምትገሠግሠው ቤተ ክርስቲያን› በሚል ርዕስ ትምህርት ሲያዘጋጅ የታየው ታላቁን ትዕዛዝና ታላቁን ተልዕኮ አጣምራ የያዘች፣ በደቀ መዛሙርነት ሕብረት ደምቃ የተሞላች፣ በአገልግሎት ፍሬ የተትረፈረፈች፣ .... ደቀ መዝሙር በሆኑና በተሰጣቸው መክሊት እንደ አካል ተጋጠመዉ ከግብዝነት የፀዳና ክርስቶስን በሚወክል ሕይወት የሚመላለስ የቅዱሳን ጉባዔ ነዉ የሚታየዉ፤›› ይላሉ በማሠልጠኑ ሥራ ተካፋይ የነበሩ አገልጋዮች።








የቤተ ክርስቲያን ቋሚ ተግባራት ታላቁ ትዕዛዝ (ማር. 12፡ 29 - 31) እና ታላቁ ተልዕኮ (ማቴ. 28፡ 19 - 20) ናቸዉ በማለት ከሁለቱ ታላላቅ ክፍሎች የተፈለቀቁና ቤተ ክርስቲያን ልጽፈትመዉ የሚገባት አምስት ተግባራትንም ይጠቅሳሉ፤

እነሱም፦

- እግዚአብሔርን ማምለክ (ጌታ አምላክህን ዉደድ)፤
- ወንጌልን ማሰራጨት (ሂዱ)፤
- ሕብረትን ማድረግ (አጥምቁ)፣
- ሕይወትን ማሳደግ (ደቀመዝሙር አድርጓቸዉ)፣
- ለአገልግሎት ማሰማራት (ባልንጀራህን ዉደድ) ናቸዉ።

በአንድ ዓረፍተ ነገር ተጠቃለዉ ሲገለጹ፦ የቤተ ክርስቲያን ተግባር *‹‹እግዚአብሔርን በመንፈስና በእዉነት እያመለከች፣ በእርሱ ኃይል ሰዎችን በወንጌል ማርካ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሕብረት በመጨመርና ሕይወታቸዉን በመገንባት ለአገልግሎት ማሰማራት ነዉ።››* ይህ ነዉ የባለ ራእዩ እምነት።

ተልዕኮዋን በተመለከተ ሌላ ቁልፍ ነጥብ ይጨምራሉ፤ በአጭር ቃል *የቤተ ክርስቲያን ተልዕኮ የእግዚአብሔር መንግሥት በምድር ላይ እንዲሠለጥን የማድረግ ተልዕኮ ነው። ጌታችን ኢየሱስ ይነበረው የእደባባይ መልዕክት*



*የእግዚአብሔር መንግሥት መምጣት ስለ ነበረ ቤተ ክርስቲያን ይህንኑ ተልዕኮ ማራመድ ይገባታል* (ማቴ 4፡17፤ 10፡7)፡፡

የእግዚአብሔር *መንግሥት* በምድር ላይ ለመሠልጠኑ የመጨረሻውና ዋነኛው ማስረጃ በአካባቢው ሕበረተሰብ ውስጥ የእግዚአብሔር *መንግሥት* መሠልጠኑ ነው፡፡ ክርስቶስን የሚመስሉ አማኞች በሕብረተሰቡ ውስጥ ሲበዙ በሕዝቡ ላይ የጽድቅ ጫና እያደረጉ ሰዎች ለእግዚአብሔር ነገር አክብሮት እንዲኖራቸው ያደርጋሉ፡፡ አማኞችም እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ አንዳንዶቹ በመንግሥትና በማሕበራዊ ተቋሞች ውስጥ የመሪነት ስፍራ እየያዙ ሕዝቡን በጽድቅ ያስተዳድራሉ፡፡ በእነርሱም በኩል የእግዚአብሔር *መንግሥት* ትሠለጥናለች፡፡

አክለዉም እንዲህ ይላሉ፡- ‹‹የቤተ ክርስቲያንን ተልዕኮ በዚህ መልክ ስንገነዘበው፣ *ልንኖርበት፣ ቢያስፈልገን ደግሞ ልንሞትለት የሚገባ ትልቅ ራዕይ ሆኖ እናየዋለን፡፡* ... ራዕዩን በዚህ መልኩ ከተቀበልነው ደግሞ የራዕዩ ተግባራዊነት የሚጠይቀውን ዋጋ ተግቶ በመስራት ለመክፈል የተዘጋጀን ልንሆን ያስፈልጋል፤ ሲሉ ለዚሁ መጠራታቸዉንና መስዋዕትነት ለመክፈል መዘጋጀታቸዉን በሰያፍ ይገልጻሉ፡፡

ዶ/ር ብርሃኑ፡- *የቤተ ክርስቲያን ተልዕኮ ልብ ደቀ መዝሙርነት ነዉ፤ ዓለምን በወንጌል ለመድረስ ቁልፍ የሆነዉ ስልትም ደቀ መዝሙርነት ነዉ፡፡ ይህም ጌታ ያስተማረን ከሁሉም ፍቱን የሆነው 1፣ 30፣ 60 እና 100*





*እጥፍ የሚያስገኘዉ ደቀመዛሙርትን በማፍራት ዓለምን በወንጌል የመድረስ ዘዴ ነው፤* ይላሉ፡፡

ዘዴዉን በምሣሌ ያብራሩት በሚከተለዉ መንገድ ነበር፡- አንድ ከበርቴ ተነሥቶ ሁለት አማራጮችን ሰጠ እንበል፡፡ አማራጮቹም፡- ዛሬ በአንድ ጊዜ 1 ሚሊዮን ብር ብሰጥህ ይሻልሃል? ወይስ ከዛሬ ጀምሬ በሚቀጥሉት 30 ቀናት ውስጥ በመጀመሪያው ቀን 2 ሣንቲም በሁለተኛው ቀን 4 ሣንቲም በሶስተኛው ቀን 6 ሣንቲም ወዘተ እያደረግሁ ብሰጥህ ይሻላል? ከሁለቱ የትኛውን ትመርጣለህ? ቢል የትኛውን እንመርጣለን?

መቼም በአንድ ጊዜ ለመክበር የሚፈልግ ሰው ሂሳቡን ለማስላት እንኳ ሳያስብና የሚያዋጣውን ሳይመዝን ዛሬውኑ 1 ሚሊዮን ብር እንደሚል የታወቀ ነው፡፡ ነገር ግን በውልና በእርጋታ አስቦበት ስሌቱን የሠራ ሰው ሁለተኛውን ይመርጣል፡፡ በጣም የሚገርመዉ ነገር ግን የሁለተኛውን አማራጭ ስናሰላው 10,737,418.00 ብር ሆኖ መበኘቱ ነዉ፡፡

ምክኒያቱም፡- ስሌቱ የማባዛት ነዋ! ይህች አነስተኛ ምሳሌ ደቀመዛሙርትን የማፍራትን ጠቀሜታ በትልቅ ሁኔታ ታሳያለች፡፡ ደቀ መዛሙርት በማፍራት ለማደግ ሲወሰን በመጀመሪያዎቹ ወራትና ዓመታት ጠቀሜታ ያለው ሥራ እየተሠራ አይምስልም፡፡ ሆኖም ግን ወደ ጌታ የሚመጡት ሁሉ ስለሚፀኑና ሌሎችንም ወደ ጌታ ስለሚያመጡ የማባዛቱ ሂሣብ የሚራባው በጠንካራ ቁጥሮች ነው፡፡ በትዕግስት ተሰርቶ የተወሰኑ የደቀመዛሙርት ቁጥር ላይ ሲደረስ በፍጥነት እያደገ አስደናቂ ደረጃ ላይ ይደርሣል፡፡

በመጀመሪያ ቀን አንድ ሚሊዮን ብር የመቀበል አማራጭ በጀማ ስብከተ ወንጌል (Crusade) ለማደግ መሞከርን ይመስላል። በብዙ ጥረትና በብዙ ወጪ የሚካሄድ የጀማ ስብከተ ወንጌል በርከት ያሉ ሰዎች ክርስቶስን ለመቀበል በአደባባይ እጃቸውን ሊያነሱ ይችላሉ። ሆኖም ግን በተደጋጋሚ የተካሄዱት ጥናቶች እንዳሳዩት ከዓመት በኋላ በቤተ ክርስቲያን የሚገኙት ከ3% እስከ 15% ብቻ ናቸው።

የጀማ ስብከተ ወንጌል በጭራሽ መደረግ የለበትም ማለታችን አይደለም። እያልን ያለነው ደቀመዛሙርትን በማፍራት ወንጌልን ማሰራጨት እጅግ ፍቱን የሆነ ዘዴ መሆኑን ነው። በተለይም ትንንሽ ቤተ ክርስቲያናት የጀማ ስብከተ ወንጌል በማዘጋጀት ዉስን ጥሪታቸዉን ማባከን የለባቸዉም። አንዲት ቤተ ክርስቲያን በርከት ያሉ ደቀመዛሙርትን ካፈራች በኋላ ከጥሩ ዝግጅትና ጸሎት ጋር ጀማ ስብከተ ወንጌል ልታካሂድ ትችላለች። ይህ ዓይነቱ ይፋዊ እንቅስቃሴ መደበኛ ለሆነው የግል የወንጌል ስርጭት የሕዝቡን ልብ ለማዘጋጀትም ይጠቅማል።

እንግዲህ በሐዋርያትና በነብያት ትምህርት ላይ መሥርተን የምንገነባት ቤተ ክርስቲያን፦

- በሕበረት - ሞቅ ያለች፣
- በደቀ መዝሙርነት - ጥልቅ የሆነች፣
- በአምልኮ - የበረታች፣
- በአገልግሎት የሰፋች፣
- በወንጌል ስርጭት - የበዛች፣

በጥቅሉ ታላቅ የሆነች ቤተ ክርስቲያን ትሆናለች። ይህችም ቤተ ክርስቲያን በዚህ በመጨረሻዉ ዘመን በድል የምትገሠግሥ ቤተ ክርስቲያን ትሆናለች።

ይህንን አመለካከታቸዉን ለማገዝ ያዘጋጁት መጽሐፍ «ከግብዝነት ክርስቶስን ወደ መምሰል» የሚል ርዕስ ያለዉ ሲሆን የሥልጠና ጹሑፍና የመጽሐፍ ቅዱስ ማጥኛ የሚሆኑ ሁለት መድብሎች አሉት። በተለይ የማጥኛ ጽሑፉ አዲስ ኪዳንን የዳሰሰና ሰው ከግብዝነት ወጥቶ ክርስቶስን ሊመስልባቸው የሚገቡ የሕይወት ፈርጆች የተዳሰሱበት፣ በውል ያልተለወጠና ‹ያልሞተ› ሰው በቀላሉ ሊዘልቃቸው የማይችሉ ጥልቅ፣ ሞጋችና ፈታኝ መልእክቶችን ያዘለ ነዉ።

### በተልዕኮ አኳያ ቤተ ክርስቲያንን ማደራጀት

በተልዕኮ አኳያ ቤተ ክርስቲያንን ማደራጀት በተመለከተም አመራሩን ከማደላደል ጀምሮ ሚዛኑን የጠበቀ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል አደረጃጀት የማስረፅ አስፈላጊነትን ይጠቁማሉ - ዶ/ር ብርሃኑ፦

አይሁድ የኢየሱስ ትምህርት እንደቀደሙት ነቢያት ዓይነት መስሏቸው ነበር። ስለዚህ ደቀመዛሙርቱ በአይሁድ ሥርዓት እንዲመላለሱ ጠበቁ። ጌታ ግን ያመጣው ትምህርት ፍፁም አዲስ ስለሆነ፣ አዲስ የወይን ጠጅ አዲስ አቁማዳ እንደሚፈልግ ሁሉ የተለመደውን አሠራር መቀየር እንደሚያስፈልገው ከተጠቀሰው ክፍል እንማራለን። ዛሬም መንፈስ ቅዱስ ለቤተ ክርስቲያን አዲስ ራዕይ ሲሰጥ የቀደመውን አሠራራችንን መለወጥ ሊያስፈልገን ይችላል።

በ18ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በትልቅ ሁኔታ ወንጌልን የሰበኩ George Whitefield እና Jonhn Wesely የተባሉ አገልጋዮች ነበሩ። Whitefield ወንጌል በትልቅ ሁኔታ እየሰበከ ተዘዋወረ፣ Wesely ግን ትምህርቱ ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፍበትን መዋቅር እያደራጀ ይዞር ነበር። የGeorge Whitefield የሥራ ዘዴ በታሪክ ካለሆነ በስተቀር በአሁኑ ወቅት አይታወቅም። የJonhn Wesely ሥራ ግን በአሁኑ ዘመን በዓለም ዙሪያ ብዙ ሚሊዮን አባላት ባሉት በMethodist ቤተ ክርስቲያን እየቀጠለ ነው።

ከነዚህ ግንዛቤዎች የምንረዳው፣ የቤተ ክርስቲያን ተልዕኮ ምን እንደሆነ ጥርት አድርጎ ማወቁ አስፈላጊ ቢሆንም፣ የተቀበልነውን ራዕይ ተግባራዊ የሚያደርግ አስተማማኝ አሠራር ካልተዋቀረ፣ አልፎ አልፎም ደግሞ የሚዘጋጀው መዋቅር አምስቱን የቤተ ክርስቲያን ቋሚ ተግባሮች በሙሉ የሚያቅፍና በሚዛን የሚይዛቸው ካልሆነ ወደሚያመረቃ ግብ መድረስ እንደማይቻል ነው።

በሚዛን የሚሠራ መዋቅር በማይኖርበት ጊዜ የቤተ ክርስቲያን እንቅስቃሴና ሥራ እንደ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ዝንባሌ በአንድ ወይም በሁለት አቅጣጫዎች ብቻ ያጋደለ ይሆናል።

ለምሳሌ ያህል:-

- ሰዎችን በወንጌል በመድረስ ላይ ብቻ የምትቆም ቤተ ክርስቲያን ትምህርቷም፣ ስብከቷም ይህ ብቻ ይሆናል፤





- እግዚአብሔርን በማምለክ ላይ ብቻ የምታተኩር ቤተ ክርስቲያን ለአምልኮ ስፊ ዝግጅት ታደርጋለች፣ በጣም ውድና ዘመናዊ የሙዚቃ መሣሪያዎች ይገዛሉ፣ መጋቢውም የመዝሙር ሰው ይሆናል፤
- በቤተሰባዊነት ላይ ብቻ የምታተኩር ቤተ ክርስቲያን ደግሞ ብዙ ሕብረቶች ይኖሯታል፣ ማሕበራዊ ግንኙነት ይበዛሉ፣ ሩጫዋም ትኩረቷ በዚሁ ዙሪያ ይሆናል፤
- በትምህርት ላይ ብቻ የምታተኩር ቤተ ክርስቲያን ብዙ የትምህርት ፕሮግራሞች ይኖሯታል፣ አገልጋዮቿንም በከፍተኛ ትምህርት በማሠልጠን ላይ ትተጋለች፤
- በሕብረተሰብ ችግር ላይ ብቻ የምታተኩር ቤተ ክርስቲያን ፖለቲካውንና የማሕበረሰቡን እንቅስቃሴ በቅርብ ትከታተላለች፣ የልማት ስራዎችን በመሥራት ይህንን ችግር ለመቅረፍ ትተጋለች፤


እንደነዚህ ዓይነት ቤተ ክርስቲያኖች በአግባቡ አያድጉም፣ ደግሞም አይዘልቁም። ምክንያቱም አገልግሎትን ለመፈጸም በተደላደለ መሠረት ላይ ስላይደሉ እግዚአብሔር እነዚህን አገልግሎቶች በሙላት ስለማይባርክ ነው። ስናጠቃልለው አምስቱን የቤተክርስቲያን ቋሚ ተግባሮች ሚዛናዊነት በጠበቀ ሁኔታ የሚይዝ አወቃቀር (አደረጃጀት):-

- አመራሩን ያስተካክላል
- ምዕመኑን ሙሉ በሙሉ ያንቀሳቅሳል፣ ያሳትፋል

- አገልግሎቶችን በቋሚ ተግባሮች መሠረት ማደራጀት ያካትታል።

## ልጅነት

የቀጣዩ ትምህርት ርዕስ «ልጅነት» ነዉ። ልጅነት በወንጌል አምነዉ ላልዳኑ ብቻ ሳይሆን በጌታ ቤት ለዓመታት ቆይተዉ



የልጅነት ምስጢር ገና ላልገባቸዉም ጭምር ዓይነ ልቡናቸዉን ወደ ውስጥ መልሰዉ ማንነታቸዉን እንዲፈትሹ ሙጥኝ በሚል መጽሐፍ ቅዱሳዊ ንድፈ ሃሳብ የተጠቀጠቀ መጽሐፍ ነዉ።

በሌላ አገላለጽ ከበርካታ ዓመታት የክርስትና እና የአገልግሎት ሕይወት በኋላ «ዛሬ ልጅነቴን እንደገና መቀበል አለብኝ» ወደ ሚል ውሳኔ የተማሩትን ሁሉ የሚያደርስ ትምህርት ነው።

ይህ ትምህርት የክርስትና ሕይወት ደመ ነፍሳዊ በሆነ ልማዳዊ መመላለስ ሳይሆን ሰዎች ሁሉ ከእግዚአብር ዘንድ በተቀበሉት ወይም ሊቀበሉት በሚገባ *በልጅነት መንፈስ* መከናወን አለበት የሚል ዋና መልእክት የአዘለ ነዉ። በአቀራረብ ረገድ የክርስትና የሕይወትን ፈርጆችን ሁሉ በሚዳስስ መልኩ የተቀናበረና ተማሪዉ /አንባቢዉ አውቆም ሆነ ሳያውቅ በእያንዳንዱ ምዕራፉ ጥናት ራሱን እንዲበረብር የሚያደርግ ኃይል አለዉ።






ራስን መበርበሩ ደግሞ፡- በንስሐ ወይም በምስጋና ሆኖ ወደ እግዚአብሔር መገኘት ውስጥ እንዲገባ ያደርገዋል። በእግዚአብሔር ኀልዎት ውስጥ ራሱን ሲያገኘዉ፡- የተደረገለትንና የሚደረግለትን ይረዳል፤ የተፈለገበትንና የሚፈለግበትን ተገንዝቦ ወደተግባር ለማከናወን የሚያስችለዉን መንፈሳዊ ግፊት (motive) በዉስጡ እንዲያዘረዝር የሚያስችለዉን ጸጋ ለመልበስ ይጣጣራል።

የመልእክቶቹን ተያያዥነት መልሶ ለማያያዝ ያህል፡- በዘመኑ መጨረሻ በድል የምትገሰግስ ቤተ ክርስቲያን ልትኖር የምትችለወው ከግብዝነት ጸድተው ክርስቶስን የሚመስሉ ደቀ መዛሙርት ሲኖሩ ብቻ ነው ክርስቶስን ለመምሰል ደግሞ «ልጅ» መሆን ይገባል እግዜአብሔር «ልጁ በብዙ ወንድሞች መካከል በኩር ይሆን ዘንድ ወስኗልና»።

## ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር

መቸም ልጅ አባቱ እንዳለለትና እንዳሰበለት እንዲኖር ከተፈለገ በፅኑ ምግባር የታነፀ ሊሆን ይገባዋል። ዶ/ር ብርሃኑ ይህንን ነጥብ ለማስገንዘብ *«ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር»* በሚል ርዕስ አንድ ትምህርታዊ መጽሐፍ አዘጋጅተዋል። «ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር» ከግል ሕይወት አመራር እስከ መንግሥታዊና ሐገራዊ ኃላፊነት ያለውን የክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር ፅንሰ ሃሳብ በመጽሐፍ ቅዱሳዊ ሚዛን የተተነተነበት መጽሐፍ ነዉ። አተናተኑም ክርስቲያን በግሉ፣ በቤተሰቡ፣ በሚኖርበት ቦታና ማሕበረሰብ እንዲሁም በተሠማራበት መስክ ሁሉ ምን መምሰል አለበት? ምግባሩስ የማንን ምሳሌነት ማሳየትና ማንፀባረቅ አለበት? የሚለውን




የ
ለ
ፊ
ሰ
በ
ካ
በ
የ
ለ
እ

ሚል ውሳኔ የተማሩትን ሁ

*አጠቃላይ አስተምህሮና ‹እዉነት› ያለማመቻመች ለመግለጽ ወደ ኋላ በማይል ስልት የቀረበ* ነው።

ከተገጸዉ እዉነት በመነሣት እንደ እግዚአብሔር ቃል የመኖር ለዛ ሲጠፋ በክርስቲያናዊ ሕይወታችን በተለይም በእግዚአብሔር ቤት ዉስጥ ዓይናቸዉን አፍጥጠዉ የሚከሰቱት ሁኔታዎችና መዘዛቸዉም የሚያስከትዉ ፍዳና የእግዚአብሔር ቁጣ ምን እንደሆነ መጽሐፉ ያስረዳል።

**የመቅደሱ ሕግ**

የመቅደሱ ሕግ በነቢዩ ሕዝቅኤል መጽሐፍ ላይ ተመሥርቶ የተቀናበረዉ ሌላዉ የዶ/ር ብርሃኑ የብዕር ምርት ነው። ዶ/ር ብርሃኑ ርዕሰ ጉዳዩን በተመለከተ ለማስተላለፍ የፈለጉትን መልእክት፡-


- ለእስራኤል በጠላት እጅ መዉደቅ፣ ለሕዝቧ መበተን፣ ለመቅደሱ መፍረስ ... የሆኑትን ምክንያቶች እንደ ምሣሌ በመጥቀስ፤
- እግዚአብሔር በልቡ ያሰበዉን የመቅደስ ንድፍና የመቅደሱን አገነባብ በሥዕላዊ መግለጫ በማቅረብ፣
- አዲስ ኪዳናዊ የሆነው የእግዚአብሔር መቅደስ ግንባታ ‹የሰውን ልብ የመቅረፅና የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ አድርጎ የማዘጋጀቱ ትልቅ ሥራ መሆኑን ለማመልከት ጥንቃቄ የተሞላዉ ጥረት አድርገዋል፡

ይህ ትምህርት የዘመናችን ቤተ ክርስቲያ ያለችበትን ገጽታ የሚያሳይ ዓይን ከፋች እንደሆነ መጽሐፉን ያነበቡና ኮርሱን የወሰዱ ሰዎች የመሰከሩለት ትምህርት ነው።





**ኤክሲሺያ ተነሺ ስለ መንፈሳዊ ዉጊያ**




*የሰው ሕይወት በምድር ብርቱ ሰልፍ የመሆኑ ጉዳይ* በክርስቶስ ተከታዮች ዘንድ ተደጋግሞ የሚወሳ ቢሆንም ለሰልፉ ተገቢውን ዝግጅት አድርጎ ለዘላቂ ድል የመዋጋቱ ትጋት ግን እምብዛም አይስተዋልም።

በዘመናችን መንፈሳዊ ውጊያን አስመልክቶ ከሚንጸባረቁ አመለካከቶች መካከል በጥቂቱ ብንጠቅስ፡-
ክርስቶስ ውጊያችንን ተዋግቶ ስለጨረሰልን እኛ መዋጋት አያስፈልገንም ከሚሉት ጀምሮ፡-

- በሕይወት የሚገጥሙ ልዩ ልዩ ፈተናዎች ሁሉ የሰይጣን ጥቃቶች እንደሆኑ በመቁጠር ነፃነትን ማጣት ነዉ፤
- የክርስትና ሕይወት ዕረፍትም ሰልፍም ነው። ስለዚህ ቃሉ በግልጽ በሚነግረን መሠረት ለጠላት ሥራ ንቁ በመሆን አስፈላጊውንም መንፈሣዊ የጦር ዕቃ በመልበስ የክፉውን ሥራ መዋጋት በእጁ ያስገባቸውን ምርኮኞች ነፃ ማውጣትና የእግዚአብሔርን መንግሥት ማስፋት አለብን የሚሉት ዋነኞቹ ናቸው።

የኤክሌሺያ ተነሺ አገልግሎት ሦስተኛውን ነጥብ መሠረት በማድረግ ነበር ይህንን የማሰልጠኛ መጽሐፍ የአዘጋጀዉ።



ከጠለፋው በኋላ ጉባዔው ላይ ደርሰው ንግግር ሲያደርጉ ያደርጉ

መጽሐፉ በዓለም አቀፍ ደረጃ እየተከናወነ ያለውን የክፉዉ *ሥራ ማዕከል የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ ወላጅ የሆነው «የፍሪ ሜሶነሪ /free masonary»* እንቅስቃሴን ስዉር ደባ የተጋለጠበት ዝግጅት ነዉ። ቤተ ክርስቲያን በድል እንዳትገሠግሥ እንቅፋት የሆነባትን ይህንን የሰይጣናዊ አሠራር መረብ በአእምሮና በመንፈስ አዉቆ መዋጋት ይገባል የሚሉት ዶ/ር ብርሃኑ የደባዉን አሳሳቢነት የገለጹት እንደሚከተለዉ ነበር።

> *ዘመናትን የሚሸጋገር ዓለም አቀፍ ሰይጣናዊ ቅንጅት መኖሩን ማመን ለብዙዎቹ ያስቸግራል። ስለዚህ ይህንን የመሰለው ሰይጣናዊ እንቅስቃሴ ተከታትሎ ለክርስቲያኑ ማኅበረሰብ የማቅረብ አስፈላጊነቱ አይታያቸውም። እውነታው ግን ሌላ ነው። ዛሬ «የፍሪ ሜሶነሪ» የሚባለው ስውር/ግልፅ ድርጅት ከአዳም ዘመን ጀምሮ የነበረውን ሰይጣናዊ ስውር እንቅስቃሴ በተዋረድ ተቀብሎ «አዲስ የዓለም ሥርዓት» ለማስፈን እየተንቀሳቀሰ ነው። እንቅስቃሴው፦ የፍጥረተ ዓለሙን ፖለቲካ፣ ኢኮኖሚ፣ ማህበራዊ ኑሮ፣ ሃይማኖትን... ለመቆጣጠር ጥረት እያደረገ ነዉ።*

ታሪካዊ አመጣጡ ቀጥሎ ያለዉን ይመስላል፦

- ፍሪ ሜሶነሪ በ1700 ገደማ ቀደም ሲል ሮሲክሩሲያንስ በሚባል ስም የሚታወቅ ስውር ሰይጣናዊ ማሕበር ሲጋለጥ መልኩን ቀይሮ የተፈጠረ ድርጅት ነው።
- የበጎ አድራጎት ሥራ ጥሩ መሸፈኛ እንደሚሆንላቸው በመረዳት አውቀው በዚህ የታወቀ ነባር ድርጀት ውስጥ ገብተው በስውር ድርጅቱን ለመገልበጥ እንቅስቃሴ ጀመሩ።
- በዚያን ጊዜ የነበረው ማሶናዊ ማሕበረሰብ የካቴድራል ግንባታ ሥራ እየቀዘቀዘ ስለ ነበረ የመፍረስ ስጋት





ላይ ነበሩ። በዚህ ስጋት ላይ እያሉም የሰይጣን ጭፍሮች ይጠጉአቸውና፦ «እናንተ፡ "Operative Mason" ናችሁ እኛ "Speculative Mason" ነን፤ አንድ ብንሆንስ? ብለው ጠየቋቸው። ይህ ጋብቻ የሚተርፉቸው መስሎአቸው ሃሳቡን ተቀበሉት።
*በጥቂት አሥርት ዓመታት ውስጥ ነገሮቹን ገልብጠው Speculative Mason" ብቻቸውን ቀሩ፤ በ*1717 *Grand lodge* London ተቋቋመ።
- በ1700 መጨረሻ አካባቢ ወደ አሜሪካ ተሻገረ።
- በ1870 አሁን የዓለም አቀፉን ሰይጣናዊ ሥራ በጥብቅ ምስጢር እየመራ ያለው አዲስ ድርጅት (ሱፐር ራይት /super-right) ተመሠረተ።

አሜሪካዊው አልበርት ፒክ ጣሊያኒያዊው ጁሴፒ ማዚኒ መሪዎች ሆነው ተሸሙ። ሹመቱ Pike, The Sovereign Pontif of Lucifer for Universal Free masonary) ይባላል።

- በ1776 Illuminati የተባለው ድርጅት የfree masonary አስኳል ሆኖ በጀርመን በAdam Wieshaupt ተቋቋመ።
- ከጅማሬዉ ጀምሮ በበጎ አድራጎት ሥራ ሰበብ ብዙ ባለጠጎችን ባለሥልጣኖችንና ታዋቂ የሃይማኖት ሰዎችንም ጭምር ማሰባሰብ ጀመሩ።

ፍሪማሶነሬ የምስጢርና የሥልጣን ተዋረዶች አሉት። እስከ 33ኛው ያሉት ቀለል ያሉ ሆነው ሴጣናዊ አሠራራቸዉ ከአባላቱ የተሰወሩ ናቸው። ከዚህም የተነሣ ብዙ ሚሊዮን

የዋሆች ሳያውቁት ይሳተፉበታል። 33ኛ ውስጥ የሚገቡት ግን ታማኝነታቸው የተጣራ ነው። ከዚያ በኋላ ሉሲፈር ይመስካል። "The divinity is dual and that Lucifer is the equal adonai" በማለት።

መሪዎቹ መንፈስ መራን ገለጠልን ነው የሚሉት፦

- ሰይጣን የክርስቶስ ታላቅ ወንድም መሆኑን፣
- ዓለምን መቆጣጠር እንደሚገባው፣
- በሪ ኢንካርኒቲን ሰው መለኮት እንደሚሆን፣
- መናፍስት የበለጠ የረቀቀ ጥበብ ይዘው ወደ መለኮት እንድናድግ እንደሚመሩን፣.

እንግዲህ 20ኛውና እና በ21ኛው ክፍለ ዘመን የዓለምን የኢኮኖሚ አውታሮች (የባንክ፣ የነዳጅ ማጣሪያ፣ የማዕድን ኢንዱስትሪዎችን፣ እንዲሁም የፊልምና የዓለም ደም ሥር የሆነዉን የመገናኛ ብዙኃን ተቋማትን... ወዘተ) በመቆጣጠር፤ በአገራት የፖለቲካ ሥርዓት ላይ ተፅዕኖ በማድረግ ወይም ጣልቃ በመግባት፣ የሚፈልጉትን በማንገሥ፣ የማይፈልጉትን በማስገልበጥ፣በዓለም አቀፍ ጉዳዮች ላይ የሚመክሩ ቡድኖችን በማቋቋምና የዓለም አቀፉን ማሕበረሰብ የጋራ ውሳኔዎች ወደ ሚፈልጉት አቅጣጫ በማስጠምዘዝ እየሠሩ ይገኛሉ። ለምሳሌ፦ በ1902 አጠቃላይ የትምህርት ቦርድ (Genereal Education Board) በማቋቋም የትምህርት ፖሊሲዎችን በማጣመምና የመምህራን ማሠልጠኛዎችን በመቆጣጠር

- ክርስትና መታሰቢያዉ እንዲጠፋ
- የክህደት አመለካከቶች እንዲሰፍኑ





- ዘማዊነት ልቅ እንዲሆን የሚያግዙ ጥናቶች እንዲጠኑ ገንዘብ በማፍሰስና ዉሳኔዎች እንዲደረጉ በመገፋፋትና በመሳሰሉት ስዉር ደባቸዉን በማባባስ ላይ ይገኛሉ።

**መፍቴሔዉስ?**

በመጀመሪያ ደረጃ የፍሪማሶነሬን ዘመን ዘለል ታሪክ ማወቁ ክርስቲያኖች ያሉበትን መንፈሳዊ ዓለም እንዲገነዘቡ ያደርጋቸዋል። የጠላትን ሃሳብ ሲያውቁ አይታለሉም (2ኛ ቆሮ. 2፡-5-11)። ሁለተኛም፦ የጠላትን ስልፍ ማወቅ ለዉጊያዉ ጥሩ ዝግጅት ለማድረግ ያስችላል። የክፉን አሠራር ለመመከትም ዋናዉ አማራጭ ለመንፈሣዊ ውጊያ የሚመጥን የሕይወት ዝግጅት ማድረግ ነዉ ይላሉ ዶ/ር ብርሃኑ።

*ወታደር ወደ ጦር ሜዳ ከመሄዱ በፊት ከፍተኛ የአካልና የአዕምሮ ዝግጅት ያደርጋል፦ ስልፍ ዲሲፕሊን ይማራል፣ በሸካራ ሁኔታዎች ዉስጥ ሳይቀር ብርቱ የስፖርት ልምምድ ያደርጋል፣ ምራሉ ተገንብቶለት በንቁ መንፈስ ሆኖ ድል እንደ ሚያደርግ አምኖ እና በአዝማቹ ተማመኖ እንዲሁም አዝማቹን ያለ ምንም ማንገራገር ታዝዞ ወደ ወደ ዐዉደ ዉጊያዉ ይወጣል።*

በመጨረሻም ለመንፈሣዊ ውጊያ የሕይወት ለእግዚአብሔር መገዛት፣ ወደ እግዚአብሔር መቅረብ፣ እጅንና ልብን ማንጻት ቁልፍ ነጥቦች መሆናቸዉን እጅግ ዘርዝር ባለ ሁኔታ በመግለጽና የዉጊያ ደረጃዎችን በማመላከት ይደመድማሉ።

**ቤሎች**

እነዚህና ሌሎችም ለምሳሌ ጥሪና አገልግሎት በስፋት የተዳሰሰበት፣ የተጠራው ካልተጠራው የሚለይበት የጸጋ ስጦታዎች አጠቃቀማቸው፣ የእግዚአብሔር ሙሉ ምክር፣ ክርስቶስ ሁሉም ነገር በሁሉም ነው (ተጀምሮ ያላለቀ)

የሴቶች ሚና በቤተ ክርስቲያን፣ አዲስ ኪዳናዊ የቤተ ክርስቲያን አመራር፣ የቤተ ክርስቲያን ተከላ መመሪያዎች ወዘተ በሚል ርዕስ በርካታ ሥልጠናዎች ተሰጥተዋል፤ የሥልጠና ጽሑፎች፣ መጽሐፎችና መምሪያዎች ተዘጋጅተዋል።

ሁሉም ዓላማቸው ያመኑት ሁሉ ደቀ መዝሙርና ባለ አደራ ሆነው በዚህ የዘመን መጨረሻ ክፋትን እየጣሉ ገስጋሽ ይሁኑ! የሚል ነው። ለመሆኑ ብርሃን ፈንጣቂ ምላሾች አስገኝቶ ይሆን? የአንባቢዉ ቆይታ በአሃዞች ሠንጠረዥ እንዳይደርቅበት ከማሰብ ጭምር እንደሚከተለዉ ቀርበዋል። በመጀመሪያዎቹ ሰባት ዓመታት አገልግሎቱ የደረሰበትን የሚያሳዩ አህዛዊ ዝርዝር መገለጫዎች:-

**በአር ዉስጥ የተሰጡ ሥልጠናዎች** **ሰንጠረዥ 1**

| | ርዕስ | የከተሞች ብዛት | የቤተ ክርስቲያን ብዛት | የሠልጣኞች ብዛት |
|---|---|---|---|---|
| 1. | በድል የምትገሰግሰዉ ቤተ ክርስቲያን | 90 | 308 | 5670 |
| 2. | ልጅነት | 28 | 103 | 1270 |
| 3. | የቤተ ክርስቲያን አመራር | 23 | 52 | 2360 |
| 4. | መንፈሳዊ ዉጊያ | 31 | 39 | 1195 |
| 5. | ጤናማ ቤተ ክርስቲያን መትከል | 29 | 52 | 695 |
| 6. | የጸጋ ስጦታዎች | 8 | 17 | 1920 |
| 7. | ሌሎች | 38 | 109 | 5005 |
| | ጠቅላላ | 247 | 680 | 18115 |





**ከአገር ዉጭ የተሰጡ ስልጠናዎች** **ሰንጠረዥ 2**

| ርዕስ | አገር | የከተሞች ብዛት | የቤተ ክርስቲያኖች ብዛት | የሠልጣኞች ብዛት |
|---|---|---|---|---|
| በድል የምትገሰግሰው ቤተ ክርስቲያን | ታንዛኒያ | 1 | 4 | 80 |
| | ኬኒያ<br>ዩጋንዳ<br>ናይጀሪያ | 7<br>1<br>1 | 45<br>2<br>1 | 299<br>96<br>500 |
| ድምር | 4 | 10 | 32 | 975 |
| | ኬኒያ<br>ዩጋንዳ<br>ደቡብ አፍሪካ<br>ናይጀሪያ<br>አሜሪካ | 4<br>1<br>2<br>1<br>9 | 17<br>1<br>2<br>1<br>12 | 735<br>65<br>110<br>80<br>760 |
| ንዑስ ድምር | 95 | 17 | 33 | 1750 |
| ጠቅላላ | | 338 | 85 | 2725 |

## በድል የምትገሰግሰው ቤተ ክርስቲያን ትምህርት ተግባራዊ ፍሬ

‹‹በድል የምትገሰግሰው ቤተ ክርስቲያን›› በሚል ርዕስ የተሰጡት ተከታታይ ትምህርቶችን ተግባራዊነት ለመመዘን የሚያስችል መጠይቅ 85 ለሚያህሉ ቤተ ክርስቲያናት ተልኮ ምላሽ ከሰጡት ቤተ ክርስቲያናት የተገኘዉ አጠቃላይ ውጤት የሚያበረታታ ነበር።

**የአገልግሎቱ ተጠቃሚዎች አስተያየት** **ሰንጠረዥ 3**

| ተ.ቁ | የአገልግሎት ዘርፍ | የተተገበረ | የተሰጠ ግምገማ | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | አልጠቀመም | ጠቅሟል | በጣም ጠቅሟል |
| 1. | የሽማግሌዎች-እረኛ የጋራ አመራር | 13 | 1 | 3 | 9 |
| 2. | አገልግሎቶችን በ5 ዘርፎች ማደራጀት | 9 | 2 | 4 | 3 |
| 3. | የአምልኮ አገልግሎቶች | 13 | 0 | 2 | 11 |
| 4. | በየእሁዱ ወንጌል መስበክ | 12 | 0 | 6 | 6 |
| 5. | ለአማኞች ተጨማሪ የአምልኮ ፕሮግራም | 9 | 3 | 2 | 4 |
| 6. | በቶሎ ማጥመቅ | 14 | 3 | 4 | 7 |
| 7. | በሕብረት አገልግሎት | 14 | 0 | 4 | 10 |
| 8. | ደቀመዛሙርት ማሠልጠን | 14 | 0 | 5 | 9 |
| 9. | አገልጋዮች ማዘጋጀት | 16 | 0 | 5 | 11 |
| | ጠቅላላ | | 9 | 35 | 70 |





# 14. አጭር ምዕራፍ፡ የአጭር ዕድሜ መቋጫ


## *14.1. ‹‹ሃይጃክ!››*

ጊዜው 1977 ዓም ነበር። በሥራ ቦታ፣ በቤት፣ በጸሎት፣ በእንቅልፍ ሰመመን ... የሆነ እንግዳ ድምፅ ይመጣባቸው ነበር። *‹‹ሃይጃክ! ሃይጃክ! ...››* ይላቸዋል - ድምፁ እየደጋገመ። ነገሩን በልባቸው ይዘው መረመሩት። ይህ ድምፅ ከሰይጣን ከሆነ ይጠፋ ዘንድ ‹በኢየሱስ ስም› ገሰፁት። እንዲያዉም ሙሉ ዓረፍተ ነገር ሰርቶ፡- *‹‹አይሮፕላኑ ይጠለፋል››* ሲል ድምፁ በጆሯቸዉ፣ በልባቸዉም አስተጋባ።

በወቅቱ የኢትዮጵያ መጥመቃውያን ቤተክርስቲያናት ቦርድ ሰብሳቢነታቸው በዓለም አቀፉ የመጥመቃውያን አሊያንስ ጉባኤ ለመካፈል ወደ አሜሪካ ለመሄድ እየተዘጋጁ ነበር። ከሰሙት ድምፅ ጋር በተያያዘ ጉዞውን በራሳቸው ለመሰረዝ አልፈለጉም። ሁልጊዜም የሚደገፉበት ጌታ መንፈስ ቅዱስም ለመቅረት የሚያበቃ ግልፅ ምሪት አልሰጣቸውም።

በስደት የተወጠረች ቤተ ክርስቲያን መሪ እንደ መሆናቸው አገሪቱም ሆነች የክርስቲያኑ ማሕበረሰብ የአለበትን ፈታኝ ሁኔታ ጉባኤዉ ከእሳቸው መስማት ይፈልጋል። ንግግር እንዲያደርጉም ጊዜና ሥፍራ ተይዞላቸዋል፤ ‹‹እንግዲህ ፈቃድህን ፈፅም ብለው ተሳፈሩ። አይሮፕላኑ አንድ የአሜሪካን አገር አየር መንገድ ኩባንያ ነበር።

እውነትም አይሮፕላኑ በመካከለኛዉ ምሥራቅ አየር ላይ ሲበር ተጠለፈ። የጠለፉት የሊባኖስ ሒዝቦላ አባላት ነበሩ። ጠላፊዎቹ በቤይሩት ሰማይ ዙሪያ አይሮፕላኑን እያንከራተቱ እንዲሆንላቸው የሚፈልጉትን ጥያቄዎች ለዓለም አቀፉ ህብረተሰብ አሳወቁ። ጥያቄአቸው ካልተሟላም አይሮፕላኑን እንደሚያፈነዱት ዛቱ።



ከጠለፋው በኋላ ጉባዔው ላይ ደርሰው ንግግር ሲያደርጉ የደርጉ

በዚያ ዘመን አይሮፕላን ጠለፋ የተለያዩ ድርጅቶች የትግል ስልት ቢሆንም እነዚህኞቹ ግን የመንገደኞቹን ገንዘብ ወርቅ






ጌጣጌጥ ወዘተ. . . እስከ መዝረፍ ድረስ መዝቀጣቸዉ ያልተለመደ ክስተት ነበር።

ድርድሩና ዘረፋው ጎን ለጎን ቀጠለ፤ የአይሮፕላኑ ነዳጅም ሊሟጠጥ ጥቂት ደቂቃዎች ቀሩ። ከብዙ ተማፅኖ በኋላ ቤይሩት አይሮፕላን ጣቢያ ለማረፍ ሲስማሙ የመንገደኞቹ ነፍስ ተመለሰች። አይሮፕላኑ የቤይሩትን ምድር ረገጠ፣ ከአድካሚ ድርድር በኋላ መንገደኞች ተለቀቁ። ሻንጣቸዉን ከአይሮፕላኑ ሆድ ዕቃ አራግፎ ለመያዝ ግን አልተፈቀደላቸውም ነበር። ስለሆነም የአየር መንገዱ ባለሥልጣኖች የመንገደኞችን የዕለት መገልገያና አልባሳትን መልሰው ለመተካት የጠፋባቸውን ዕቃዎች እንዲያስመዘግቡ አደረጉ። የቻሉትን ያህል ተኩላቸዉና በሌላ አውሮፕላን ወደ እየመድረሻቸው አደረሱአቸው።

ዶ/ር ብርሃኑም ስብሰባው እየተካሄደ ሳለ በጉባዔው መካከል ደረሱ፤ ንግግርም አደረጉ። ስብሰባው ሲያልቅ ወደ አገራቸው ተመለሱ።

ነገር ግን ሁለት በዋጋ የማይተኩ ንብረቶችን ተነጥቀው ነበር። አንዱ ‹የአልማዜ› የቃል ኪዳን ቀለበት፤ ሌላው የልባቸውን ምስጢር በትኩሱ የሚያሰፍሩበት ዐውደ ዕለት ማስታወሻቸው ነበር።

ቤተሰባቸው ይህንን እጅግ የሚያስቅቅ ዜና የሰማው ዘግይቶ ነበር። ዓይናችንን ከዕምባ፣ ልባችንን ከሀዘን የጠበቀ እግዚአብሔር ይመስገን ብለው ወደ ዘወትሩ አኗኗራቸው ተመለሱ።



ከጠለፋው በኋላ ጉባኤው ላይ ደርሰው ንግግር
ሲየደርጉ የደርጉ

# 14.2. የበረከት ጉድጓድ

‹‹በዋል ድባም ይዘፈናል›› እንዲሉ አባቶች በዚህ ‹‹ኑሮው አገልግሎቱ እግዚአብሔርን ማገልገልም የመኖሩ ምክንያት›› አድርጎ በሚቆጥረው ቤተሰብ መካከል አልፎ አልፎም ቢሆን ላላ ያለ ጭውውት አይጠፋም። ሲስተር አልማዝ ሁለተኛ ልጃቸውን ቤርሣቤህን ነፍሰ ጡር ሳሉ ዶ/ር ብርሃኑ መኪና አልነበራቸውም። ነፍሰ ጡሯ ባለቤታቸዉ በየቀኑ ከመኖሪያ ቤታቸዉ እስከ ኡራኤል ድረስ በእግራቸዉ መጥተው፣ ከዚያም ታክሲ ተጋፍተው፣ ጳውሎስ ሆስፒታል በሥነ ሥርዓት መድረሱ አታካች ሆኖባቸው ነበር።

እና በቤተሰቡ ጭውውት መካከል በቀልድ አዋዝተው ከእንግልታቸው ጋር የተያያዘ አንድ ጥያቄ ጣል አረጉላቸው - ሚስት።

> *‹‹ብርሃኑ! ለመሆኑ አሥር ዓመት የሠራና በአንተ ደረጃ ያለ ሐኪም፣ መኪና የሌለው ሰው ታውቃለህ!?››*

በመምህሩ ፊት ፈተና እንደ ተቀመጠ ተማሪ ለደቂቃዎች ያህል አሰቡ - አሰቡና መልሱን ሲያገኙት አንገታቸውን ቀና አድርገው፡

> *‹‹አዎ! አንድ ሰው አውቃለሁ ዶ/ር -------- ይባላል››*

ሲሉ መለሰላቸው፤ በፈገግታ። ይህ የጠሩት ሐኪም ደግሞ ከመሸታዉም ከምኑም የተወዳጀ ሰዉ በመሆኑ እንጂ ገንዘብ ያልቋጠረዉ በምንም በምንም ከሳቸዉ ጋር ለንፅፅር በሚበቃ ልዩ የሕይወት ተልዕኮ ምክንያት በፈቃዱ ድህነትን ስለ መረጠ አልነበረም። ሲስተሯ ሣቃቸዉን ተቆጣጥረዉ ወደ





ባለቤታቸዉ የምር የሆነ ምላሽ አሰጣጥ ስሜት ጋር ራሳቸዉን አመሳሰሉ።

ሰባት ዓመት በሥራ ላይ፣ ሁለት ዓመት በስኮላርሺፕ ውጪ አገር የኖረ ሐኪም መኪና የለውም ቢባል ማን ያምናል። ኢኮኖሚያዊው መነሻው (ዳራው) ደካማ እንኳ ቢሆን ከሙያው ተፈላጊነት የተነሣ ትርፍ ሰዓት፣ ሠርቶ፣ መንግሥታዊ ላልሆኑ ድርጅቶች አማክሮ፣ ከግል የሕክምና ተቋማት ጋር በጋራ ሠርቶና አትርፎ መኪና የማይገዛ ሐኪም አልነበረም፤ በተለይም በዚያን ጊዜ።
ዶ/ር ብርሃኑ ግን ትርፍ ጊዜያቸውን ሁሉ በቤተ ክርስቲያን ሥራ ላይ ስለሚያሳልፉ ከደመወዛቸው ውጪ ሽራፊ ሳንቲም የሚያስገኝ የጎንዮሽ ሥራ ሠርተው አያውቁም። እናም መኪና አልነበራቸውም። ስላልነበራቸውም ተከፍተው ወይም አጉረምርመው አያውቁም።

***

የአውሮፕላን ጠለፋው ትዕይንት የዓለም አቀፉ ማሕበረሰብ መነጋገሪያ እንደሆነ ሳምንታት - ወራት አለፉ። በወቅቱ ከኢትዮጵያ ለእረፍት ወደ አገራቸው አሜሪካ ሄደው የነበሩ መጥመቃዉያን ሚሲዮናውያን ከጠለፋዉ ጋር የተያያዙ ዝርዝር ጉዳዮችን ለመከታተል ዕድል አግኝተው ነበር። አንዱ ያገኙት መረጃ በጠለፋው ምክንያት ለተጉላሉት መንገደኞች አየር መንገዱ ካሣ መክፈል መጀመሩን ነበር።

ሚሲዮናውያኑ መረጃውን እንደ ሰሙ የአየር መንገዱን ባለሥልጣናት አነጋገሩ። እውነትም መንገደኞች እንደ ተጉላሉባቸው ቀናት ብዛት ካሣ እየተከፈለ ነበር። ዶ/ር

ብርሃኑ የተጉላሉት 3 ቀናት ብቻ ነበር። ስለዚያም ሃያ ሺህ ዶላር ሊከፈላቸው ይገባ ነበር። ሚሲዮናውያኑ ይህንን አሳምነው በዶ/ር ብርሃኑ ስም የሃያ ሺህ ዶላር ቼክ ይዘው ወደ ኢትዮጵያ ተመለሱ። ይህ ሁሉ ሲሆን ዶ/ር ብርሃኑ የሚያውቁት ነገር አልነበረም።

ከዕረፍት መልስ ሚሲዮናውያኑ የዶ/ር ብርሃኑን ቤተሰብ ለመጎብኘት ቤታቸው ድረስ መጡ። የተለመደው ክርስቲያናዊ መስተንግዶ ቀጠለ። ራታቸውንም ተጋበዙ። ከዚያም ድንገት ቤተሰቡን ያስደነቀ ‹ስጦታ› አበረከቱ። የሃያ ሺህ ዶላር ቼክ!

በወቅቱ የአንድ ዶላር ዋጋ ሁለት ብር ከዜሮ ሰባት ሳንቲም አካባቢ ነበር። ነገር ግን አገሪቱ በከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ እጥረት ውስጥ የነበረችበት ጊዜ በመሆኑ በጥቁር ገበያ ከሃምሣ ከመቶ የአላነሰ ዋጋ አትርፎ መሸጥ የሚቻልበት ጊዜ ነበር። አንዳንድ ሰዎችም ይህንኑ እንዲያደርጉ መክረዋቸው ነበር። ፈፅሞ አልተበገሩም። በትክክለኛው ምንዛሬ ሸጡት። በአንድ ጊዜ የአርባ ሺህ ብር ጌታ ሆኑ።

ትዳራቸዉን የመሠረቱበት መኖሪያ ቤታቸው ከአለመጠናቀቁም በላይ እያደር መጠኑ እየበዛ የሄደውን የህቡዕ ፕሮግራሞች ተካፋይ ለማስተናገድ አቅቶት ነበር። በካሣዉ ገንዘብ በጥሩ ሁኔታ ተስፋፋ። ቀለም ተቀባ፣ አማረ። ሁለተኛ ልጃቸው በዚያ ተወለደች። የቤተሰቡ የበረከት ጉድጓድ የተገለጠበት ጊዜ በመሆኑ «ቤርሳቤህ» ተባለች።





በቀሪው ሃያ ሦስት ሺህ ብር መኪና ተገዛበት። ከቤተሰቡ አባላት በበለጠ ስለ «ድሃው ዶክተር» ሲያወሩ ለከረሙት ሁሉ ከእግዚአብሔር የተሰጠች መልስ ሆነች።

## 14.3. ሰበብ

ይቺን ታሪካዊ መኪና ቤተሰቡ ለሃያ ሦስት ዓመት ተገለገለባት። ሁለቱ ባለ ትዳሮች ለሙሉ ጊዜ አገልግሎት ከወጡ በኋላ ደግሞ ከአዲስ አበባ ውጪ በቅርብ ርቀት የሚገኙ ሥፍራዎች ሁሉ የሚጓዙት በእዚቹ መኪና ነው።



የካቲት ሰባት ቀን ሁለት ሺህ ዓ.ም ዶ/ር ብርሃኑ ለአገልግሎት ወደ ቡታጅራ እየተጓዙ ነበር። ሲስተር አልማዝም በሌላ ጉዳይ ተጠምደው እንጂ የአያቶቻቸውንና የቅድመ አያቶቻቸውን አገር በእግረ መንገድ ለመጎብኘት አብሮ ለመጓዝ አስበው ነበር። (እንኳን የአልሄዱ!)



ባለቤታቸው ግን በቀጠሯቸዉ ሰዓት ለመድረስና ለማገልገል መንገድ ገቡ፤ ራሳቸው እየነዱ። ቡኢ የገጠር ከተማ ለመድረስ አራት ኪሎ. ሜትር ሲቀራቸው መኪናዋ ተገለበጠች። እሷው ሰበብ ሆነችና በተወለዱ በሃምሳ ስድስት ዓመታቸው ወደ እግዚአብሔር አምላካቸው ተሰበሰቡ።

መርዶው ተሰማ። ሀዘኑም የቤተሰባቸው፣ የቤተ ክርስቲያናቸው፣ የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት፣ በአፍሪካ ኤስያ፣ በአውሮፓ በአሜሪካ እየተዘዋወሩ የአገለገሏቸው የክርስቲያን ማሕበረሰቦች ሀዘን ሆነ። የሀዘን መግለጫ ከአራቱ ማዕዘናት ተላከ።

***

ከተላኩት የሀዘን መግለጫዎች ጥቂቶቹ የሚከተሉት ነበሩ፡-
የዶ/ር ብርሃኑን ዜና ዕረፍት በሰማሁ ጊዜ እ.ኤ.አ ሐምሌ 8 ቀን 2007 ዓ.ም ምሽት በሂዝሮው አውሮፕላን ማረፊያ ትከሻ ለትከሻ እየተቃቀፍን በእንባ ሆነን ወደ አደረግንለት ሽኝት በትዝታ ዞር ብዬ አሰብኩ። . . .

ብርሃኑ ይሰጠዉ የነበረዉን የወንጌል ትምህርት ሳስብ ልቤ ይዝላል። እስከ ዛሬ በወንጌል አገልግሎት ካወቅኋቸዉ ባልደረቦቼ እጅግ ታላቅ የሆነዉን ሰዉ ከጎኔ እንዳጣሁ ይሰማኛል። ትምህርቶቹን በተመለከተ ብርሃኑ በእርግጥ ከጳዉሎስ ጋር፡- ‹‹ለእኔም የተሰጠኝ ጸጋዉ ከንቱ አልነበረም፤ ከሁላቸዉ ይልቅ ግን ደከምሁ። ዳሩ ግን ከእኔ ጋር ያለዉ የእግዚአብሔር ጸጋ ነዉ እንጂ እኔ አይደለሁም›› (1ኛ ቆሮ





15-10) ማለት ይቻላል። አንድ ጥቅስ የሰዉን ማንነት የሚገልጽ ከሆነ ይሄ ጥቅስ ብርሃኑን ይገልጸዋል።

ዶ/ር ጆን ዋድ ሉንግ
በአሜሪካ ፐረስባይቴሪያን ቤ/ክ
የወርልድ ሀርቨስት ሚሽን ቸርች ሪሶርስ ቲም ሊደር
***

ባልደረባችንን፣ መሪያችን እና መምህራችን የነበረዉን የዶ/ር ብርሃኑን ኅልፈት የሰማነው በታላቅ ሃዘን ነው። በግል የሚያውቁት የማኅበራችን አባላት ሁሉ ለእሱ እጅግ ከፍ ያለ አክብሮትና ልባዊ ፍቅር ነበራቸው።

በጥቁር አንበሣ ሆስፒታልና በሕክምና ፋኩሊቲውም ከፍ ባለ አክብሮት የሚታይ ትጉህ፣ ቅንና አፍቃሪ ሐኪምና መምህር ነበር። በሙያዉ ሕዝባችንን ለመርዳት የነበረው የግል መርሆና የመሰጠት ባህርዩን በሙሉ ጊዜ የቤተክርስቲያን አገልጋይነት ከተሠማራም በኋላ ቀጥሎበት ነበር። ይህም ሁለንተናዉን ያለገደብ ፍጹም ለመስጠት የነበረዉን አቋም ይመሰክራል።

እኛ እዚህ በእንግሊዝ አገር የምንገኘዉ ባለሙያዎች የኢትዮጵያን የጤና እንክብካቤ አቅርቦት ማሻሻልን በተመለከተ የነበረንን ራዕይ ተግባራዊ ለማድረግ እንደ አንድ ማኅበር አጋር ሊረዳን የሚችል እና ዓምድ ሊሆልን የሚችል ሰው ነው ያጣነው።

ዶ/ር ዳንኤል ፍቃዱ ወልደ ጊዮርጊስ
የኢትዮጵያውን ሐኪሞች ማኅበር በብሪታኒያ ሰብሳቢ
***

ብዙዎቻችን እርሱን የምንመለከተው እንደ አንድ እውነተኛ የእግዚአብሔር አገልጋይ ምሳሌ እንደሆነ ሰዉ አድርገን ነው፡፡ ትሑት የዋህና በፍቅር የተሞላ ነው፡፡ የክርስቶስ አካልን ለማገልገል የነበረው መሰጠት ለሁላችንም የመነቃቃት ምክንያትና ለአገልግሎት የሚያነሳሳን ነው፡፡

በርጋና አታብዛው
ከዩጋንዳ

***

በትሕትናው፣ በታማኝነቱና ለእግዚአብሔር ሕዝብ ባሳየው መስዋዕታዊ ፍቅር እንዲሁም በሰጠው አገልግሎቱ ዶ/ር ብርሃኑ የብዙ ሰዎችን ሕይወት ነክቷል፡፡ በእግዚአብሔር መንግሥት አገልግሎት እየተጋገዝን ከእርሱ ጎን አብሬው ልንዝ እየናፈቅሁ ሳለሁ ነው የተለየኝ፡፡ እርሱ የራሱን ድርሻ አከናውኗል፡፡ አሁን ለእኛ የቀረልን በታማኝነት የራሳችንን ድርሻ በመወጣት የእርሱን ምሳሌነት መከተል ነው፡፡

ዲክሰን ኦግዋግ
በአፍሪካ የሰላምና የዕርቅ አገልግሎቶች ዳይሬክተር

***

ለዚህ ለእግዚአብሔር ሰው ያለኝን ግንዛቤ በሚከተሉት ቃላት ልግለጽ፡- ታዛዥ፣ ራሱን የካደ፣ ትሁትና በዓላማ የሚጓዝ ሰው ነበር፡፡ ሕይወቱ አጠያያቂ ባልሆነ ሁኔታ ሙሉ ለሙሉ ለእግዚአብሔር መንግሥት ጉዳይ የተሰጠ ነበር፡፡

ብዙዎች ብሩህ ተስፋ ያለዉ፣ አስተማማኝና የተከበረ ነው የሚሉትን የሕክምና ሙያ ገና በጎልማሳነቱ በመተው ሰዎችን ሁሉ ደቀመዛሙርት የምታደርገውን ጠንካራ የማትነቃነቅ





የክርስቶስን ቤ/ክ ለማነጽ ሕይወቱን ሰጠ፡፡ ከእኛ የተለየንን ሆኖም በእግዚብሔር ፊት የነበረውን የጌታ ባሪያ ያወቅሁትና ሆኖ ያገኘሁት እንደዚህ ነው፡፡

ቄስ ናታን ጋላቴራ
በወርልድ ቪዥን ኢንተርናሽናል፣ ሩዋንዳ ጽ/ቤት
ቤተ ክርስቲያንና የለጋሾች ግንኙነት ዳይሬክተር
የሩዋንዳ ብሔራዊ ኤች አይ ቪ ኤይድስ መቆጣጠሪያ ኮሚሽን
ፕሬዘዳንት

**የቀዳሚ አንባቢያን አስተያየት**

*‹‹ፈለገ ብርሃን››* የዶ/ር ብርሃኑ ሀብቴን አጠቃላይ የሕይወት ጉዞ፣ የሙያ ብቃትና አስተዋጽዖ፣ የመንፈሣዊ አገልግሎት ጥሪና ምላሽ ጥርት አድርጎ የሚያሳይ፣ ማንበብ ከጀመሩ ለማቆም የሚያዳግት እጅግ በሚጥምና በሚመስጥ አተራረክ የቀረበ መጽሐፍ በመሆኑ በጣም ወድጄዋለሁ፣ ተባርኬበታለሁም፡፡

ዶ/ር ብርሃኑ ክህሎቱን ሙያዊ ብቃቱን ለእግዚአብሔር ክብር፣ ለቤተክርስቲያንና ለሕዝብ ጥቅም ብቻ ለማዋል የቆረጠ፣ ለዚያ ብቻ የኖረ አገልጋይ መሪ እንደነበርና ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን ግንኙነት በምን ያህል ጥንቃቄ፣ አክብሮትና ትህትና እንደያዘው የሚያሳይ፣ መንፈሣዊ ሕይወት ሁሌም፣ የትም፣ በማንም ፊት አንድ ዓይነት መሆን እንዳለበት የሚገልጽ ትልቅ ትምህርት ሰጪ የትውልድ ሀብት ስለሆነ ሁሉም ሊያነበዉ የሚገባ መጽሐፍ ነው፡፡

እግዚአብሔር የዶ/ር ብርሃኑን ፈለግ የሚከተሉ መሪዎችና አገልጋዮች ያብዛልን፡፡

(ተናኜ ለማ)

ይህ ልብ የሚነካ የዶ/ር ብርሃኑ የሕይወት ታሪክ በጥዑም አቀራረብ በመጽሐፍ መልክ ተዘጋጅቶ መቅረቡ፣ በርካታዎቻችን ብዙ የምንማርበት ሕይወታችንንም የምንመረምበት፣ የምንመዝንበት ጠቃሚነቱም የጎላ ነው፡፡ *‹‹ከሁሉም ጋር ሁሉን ነገር ሆንሁ፡፡ ይህን ሁሉ የማደርገው፣ ከወንጌል በረከት እካፈል ዘንድ፣ ስለወንጌል ብዬ ነው፤››* ተብሎ በቃሉ የተጻፈውን በዘመኑ የኖረን የተወደደ ወንድምን ታሪክ ያዘለች፣ የአኗኗር ዘይቤአችንን እንድንፈትሽ የምታደርግ መጽሐፍ ነች፡፡

(ዶ/ር ግርማ ተስፋዬ)

ዶ/ር ብርሃኑ ሀብቴ አምላኩን አክብሮ ለማስከበር ሲል ያለማመቻመች የተጓዘበት፡- ጥንቃቄ፤ እርጋታና ቁም ነገር በተሞላበት የተቀደሰ የሕይወት ጎዳና የተዋቸው አሻራዎች ቅመሱኝ፤ ኑሩብኝ ሊያሰብሉ የሚችሉ ናቸው፡፡





*‹‹ፈለገ ብርሃን››* በአክብሮትና በአድናቆት የሚነበብ፤ ለትውልድም ሊተላለፍ የሚችል ቅርስ ነው፡፡

(ሰሎሞን ሉሉ)

ዶ/ር ብርሃኑ የያዘውን አጥብቆ የሚይዝ፣ ላመነበት እውነት የተሰጠ፣ መሥዋዕት ለመክፈል ወደ ኋላ የማይል፣ ስመጥር የሙያ ሹመት ቢሰጠውም፣ ጥቅማ ጥቅም ቢሰፈርለትም፣ ከዘላለማዊ ዕሴት አንጻር እጅግ አናሳ መሆኑን አበክሮ የተገነዘበ፣ ለክንቱ ውዳሴ ያልተሸጠ የክርስቶስ ኢየሱስ በጎ ወታደር ነበር፡፡

አዝማች ጌታውን ደስ ለማሰኘት ራሱን በሥጋዊ ምቾትና ተድላ ከመጠላለፍ አርቆ በጥንቃቄ የተመላለሰ ክርስቲያን ነው፡፡ "የሚታየው ጊዜያዊ ነው፣ የማይታየው ግን ዘላለማዊ ነው" የሚለውን ቃል በሁለንተናዊ ሰውነቱ የተቀበለና በሚያልፈው ውስጥ የማያልፈውን ለመያዝና ለማስያዝ፣ ለማትረፍም የተጋደለ የወንጌል ሰዉ ነበር፡፡

ዶ/ር ብርሃኑ አኗኗሩ በተአማኒ ሕይወት የተቃኘ፣ በራስ ጉዳይ ከተዋጠ ማንነት ወጥቶ ሌሎችን በሁለንተናዊ አገልግሎት ለመጥቀም ጊዜን የሚሻማ ሰው ዕድሜው አለመርዘሙ ለብዙዎቻችን ‹‹ምነው?›› የሚያሰኝ ሆኗል፣ ለፈጣሪ አምላኩ ግን ይህ እንግዳ አይደለም፡፡

> *"ጻድቅ ይሞታል፣ ይህን ግን ማንም ልብ አይልም፣ ለእግዚአብሔር ያደሩ ሰዎች ይወሰዳሉ፣ ጻድቃን ከክፉ ይድኑ ዘንድ፣ መወሰዳቸውን ማንም አያስተውልም፡፡" (ኢሳ 57.1)*

*‹‹ፈለገ ብርሃን››* ይህንን እዉነት ብልሃት በተሞላ የአተራረክ ስልት የሚነግረን መጽሐፍ ነዉ፡፡

(ሰሎሞን ከበደ)

‹‹ፈለገ ብርሃኑ›› የዶ/ር ብርሃኑ ሀብቴን አጠቃላይ የሕይወት ጉዞ፣ የሙያ ብቃትና አስተዋጽዖ፣ የመንፈሣዊ አገልግሎት ጥሪና ምላሽ ጥርት አድርጎ የሚያሳይ፣ ማንበብ ከጀመሩ ለማቆም የሚያዳግት እጅግ በሚጥምና በሚመስጥ አተራረክ የቀረበ መጽሐፍ በመሆኑ በጣም ወድጄዋለሁ፣ ተባርኬበታለሁም። ...

እግዚአብሔር የዶ/ር ብርሃኑን ፈለግ የሚከተሉ መሪዎችና አገልጋዮች ያብዛልን።

ወ/ሮ ተናኜ ለማ
(የወርልድ ቪዥን ኢትዮጵያ ዳይሬክተር)

... ‹‹ከሁሉም ጋር ሁሉን ነገር ሆንሁ። ይህን ሁሉ የማደርገው፣ ከወንጌል በረከት እካፈል ዘንድ፣ ስለወንጌል ብዬ ነው፤›› ተብሎ በቃሉ የተጻፈውን በዘመኑ የኖረን የተወደደ ወንድምን ታሪክ ያዘለች፣ የአኗኗር ዘይቤአችንን እንድንፈትሽ የምታደርግ መጽሐፍ ነች።

ዶ/ር ግርማ ተስፋዬ
(የኢትዮጵያ ቀይ መስቀል የደምባንክ ዳይሬክተር)

... ‹‹ፈለገ ብርሃኑ›› በአክብሮትና በአድናቆት የሚነበብ፣ ለትውልድም ሊተላለፍ የሚችል ቅርስ ነው።

አቶ ሰሎሞን ሉሉ
(የኢትዮጵያ ወንጌላውያን ክርስቲያን ነጋዴዎች ህብረት ሰብሳቢ)

ዶ/ር ብርሃኑ ... አዝማች ጌታውን ደስ ለማሰኘት ራሱን በሥጋዊ ምቾትና ተድላ ከመጠላለፍ አርቆ በጥንቃቄ የተመላለሰ ክርስቲያን ነው። "የሚታየው ጊዜያዊ ነው፤ የማይታየው ግን ዘላለማዊ ነው" የሚለውን ቃል በሁለንተናዊ ሰውነቱ የተቀበለና በሚያልፈው ውስጥ የማያልፈውን ለመያዝና ለማስያዝ፣ ለማትረፍም የተጋደለ የወንጌል ሰዉ ነበር። ...

"ጻድቅ ይሞታል፣ ይህን ግን ማንም ልብ አይልም፣ ለእግዚአብሔር ያደሩ ሰዎች ይወሰዳሉ፣ ጻድቃን ከክፉ ይድኑ ዘንድ፣ መወሰዳቸውን ማንም አያስተውልም።" (ኢሳ 57.1)
‹‹ፈለገ ብርሃኑ›› ይህንን እዉነት ብልሃት በተሞላ የአተራረክ ስልት የሚነግረን መጽሐፍ ነዉ።

አቶ ሰሎሞን ከበደ
(የቀድሞ የአፍሪካ ባይብል ሶሳይቲ ዳይሬክተር-ከአሜሪካ)

ዋጋው የኢት.40 ብር

ር-ኖቦት አታሚዎች